የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

የ2013 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

ሚያዚያ/2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

የ2013 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የተመደበለትን በጀት በፋይናንስ አዋጅ፣ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሃብትና ንብረት ሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2013 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርቶች እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ/የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘዋል፡፡

- የተጠቃለለ የሂሣብ ማመዛዘኛ ሪፖርት

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀትና በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደርን አዋጅ ደንብና መመሪያ የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

ገቢ

1. የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ዓ.ም ክፍል አንድ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 አንድ ተቀጣሪ ከመቀጠር የሚያገኘው ገቢ በኢትዮጵያ የመነጨ ነው የሚባለው ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) ክፍያው የሚፈጸምበት ስፍራ ግምት ውስጥ ሳይገባ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚከናወን የቅጥር አገልግሎት የተገኘ ገቢ ወይም ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የቅጥር አገልግሎቱ የትም ቢከናወን በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሳዊ ሪፐብሊክ መንግስት ወይም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሳዊ ሪፐብሊክ መንግስት ስም ክፍያው ለተቀጠረው ከተፈጸመ ነው ይላል፡፡ ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተለያዩ የኢፌድሪ ኤምባሲዎች ለሚገኙ የሚሲዮን ኮንትራት ሰራተኞች ደመወዝ ብር **46,603,136.24** በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎችና የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣዎች በተለያዩ ቀናት ክፍያ የተፈፀመ ሲሆን፤ ከደመወዝ ተቀናሽ መደረግ የሚገባው፤

   - በኢፌዲሪ ፕሪቶሪያ ኤምባሲ ብር 2,394,641.97፤
   - በኢፌዲሪ ኒወርክ ኤምባሲ ብር 4,272,483.33፤
   - በኢፌዲሪ ለንደን ኤምባሲ ብር 5,919,774.00፤
   - በኢፌዲሪ በመስኮት ኦማን ኤምባሲ ብር 1,383,137.96 እንዲሁም
   - በኢፌዲሪ ናይሮቢ ኤምባሲ ብር 1,232,731.77

   በድምሩ ብር 15,202,769.03 የስራ ግብር ተቀናሽ ተደርጎ ለመንግስት ገቢ መደረግ ሲገባ ሳይቀነስ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰብሰብ የሚገባውን ገቢ ዝቅ እንዲል አድርጓል፡፡

2. የፌዴራል መንግሥት የግዢ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/4 (ሀ) እና (ለ) መሰረት አቅራቢው ሳይፈጽም በቀረው የውል መጠን ላይ ውል ሰጪ የመንግስት መ/ቤቶች በየቀኑ 0.1% ወይም 1/1000ኛ ከውሉ ዋጋ 10 በመቶ ሳይበልጥ የጉዳት ካሳ ሊሰበስቡ እንደሚገባ ያስቀምጣል፡፡ ይሁን እንጂ መ/ቤቱ የአገልግሎትና የዕቃዎች ግዥ በተገባው ውሉ መሰረት ገቢ ላልተደረገበት የጉዳት ካሳ በድምሩ ብር 236,104.50 ከድርጅቶች ክፍያ ላይ በመቀነስ ለመ/ቤቱ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል ፡፡

ወጪ፤

3. በአዋጅ ቁጥር 377/96 (ስለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ በወጣ አዋጅ) ዘርፍ ሦስት ስለ ስራ ስንብት ክፍያና ስለካሣ አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) ድርጅቱ በመክሰሩ ወይም በሌላ ምክንያት ለዘለቄታው በመዘጋቱ የስራ ውል ሲቋረጥ፤1(ለ) ህግ ከደነገገው ውጪ በአሰሪው አነሳሽነት የስራ ውል ሲቋረጥ፤1(ሐ) በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት ሰራተኛው ከስራ ሲቀነስ፤1(መ) አሰሪው በሰራተኛው ላይ ሰብዓዊ ክብሩንና ሞራሉን የሚነካ ወይም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሰረት የሚያስቀጣ አድራጎት በመፈጸሙ የተነሳ ሠራተኛው የስራ ውሉን ሲያቋራጥ፤ 1(ሠ) አሰሪው ለሰራተኛው ድኅንነት ወይም ጤንነት የሚያሰጋ አደጋ እንዳይደርስ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት እርምጃ ባለመወሰዱ የተነሳ ሠራተኛው የስራ ውሉ ሲቋረጥ፤ ወይም 1(ረ) ሙሉ ወይም ዘላቂ የአካል ጉዳት በመድረሱ ሠራተኛው ስራ ለመስራት አለመቻሉ በህክምና ተረጋግጦ የስራ ውሉ ሲቋረጥ በአሰሪው የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት እንዳለው ያስቀምጣል፡፡ ይሁን እንጂ

- **በዋናው መ/ቤት** ብር 39,301.08 የተከፈለ መሆኑ፤
- **በፕሪቶርያ ኢምባሲ ብር 32,863.71 /16,632.02 ራንድ/** የተከፈለ መሆኑ፤
- **በናይሮቢ ኢምባሲ** የአገልግሎት ካሳ ክፍያ በሚል ብር **90,623.45** (267,325.80 ሽልንግ) የተከፈለ መሆኑ፤
- **በለንደን ኢምባሲ** የአገልግሎት ካሳ ክፍያ በሚል ብር **848,754.55(23,861.528 ዶላር)** የተከፈለ መሆኑ፤

በአጠቃላይ በድምሩ ብር **1,011,542.79** በመመሪያው ከተገለፁት ካሳ ከሚከፈልባቸው ምክንያቶች ውጭ የስራ ግዜያቸውን ላጠናቀቁ እና በፈቃዳቸው መ/ቤቱን ለለቀቁ ሰራተኞች ያለአግባብ የካሳ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡ በዚህም የበጀት ዓመቱ ወጪ ከፍ እንዲል አድርጓል፡፡

4. የሚሲዮኖች የፋይናንስ እና የግዥ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2010 ላይ ፋክቱር/ደረሰኝ/ ለሌላቸው ወይም ለማይሰጡ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች መቅረብ የሚኖርበት የመክፈያ ቅጽን በተመለከተ በመጨረሻ ገጹ ላይ አስቀምጧል፡፡ በዚሁ የመክፈያ ቅጽ ላይ ማሳሰቢያ ብሎ ቅፁ ህጋዊ የሚሆነው ከተሰራ በኃላ የሚሲዮኑ ማህተም ሲያርፍበት ብቻ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ

የናይሮቢ ኤምባሲ በተለያዩ ቀናት እና በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች በድምሩ ብር **145,412.25** (428,944.70 ሽልንግ) ለተገኘ አገልግሎትና የእቃ ግዥ ሲከፍል ከክፍያው ጋር የቀረበው የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ በመመሪያው ላይ እንደተገለጸው የሚሲዮኑ ማህተም ያረፈበት መሆን ሲገባው ማህተም ያልተደረገበት በመሆኑ የክፍያውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

5. የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 9 ክፍያ ከመፈጸሙ አስቀድሞ ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች የፅሑፍ ማረጋገጫ መቅረብ እንዳለበት እና በተገባው ውል መሠረት የሚከፈል ወጪ ከሆነ አገልግሎት መሰጠቱ መረጋገጥ እንደሚገባው ይገልፃል፡፡ እንዲሁም በ2002 ዓ.ም በወጣው የግዥ መመሪያ አንቀጽ 16.26 ንዑስ አንቀጽ 16.26.1 በመንግስት ግዥ አፈጻጸም እንደአስፈላጊነቱ ለአንድ አቅራቢ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ እስከ 30 በመቶ (30%) የሚደርስ የቅድሚያ ክፍያ ሊሰጥ ይችላል ይላል፡፡ ይሁን እንጂ

<u>በዋናው መ/ቤት</u>

- የሪፍረሽመንት እና የአዳራሽ አገልግሎት በሚል የተከፈለ **ብር 269,255.25**፤
- የባንዴራ መደርደሪያ ሽልፍ በቀጥታ ግዥ በብር 171,626.00 ከሙሃመድ ግዛው ሲገዛ ለድርጅቱ በመመሪያው መሰረት የቅድመ ክፍያ መከፈል የነበረበት ከአጠቃላዩ ዋጋ ብር 171,626.00 ላይ 30% ብር 51,487.80 ብቻ መሆን ሲገባው መመሪያውን በመተላለፍ 100% ብር 171,626.00 በወጪ ለመያዝ የሚያስችል ማስረጃ ሳይቀርብ በቀን 19/6/2013 በኢንቮይስ ቁጥር 18452 ከመመሪያ ውጪ ቅድሚያ ክፍያ በሚል ለድርጅቱ የተከፈለ መሆኑ በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

<u>በመስኮት ኦማን</u>

ብር 553,557.57 ለድርጅቶቹ ሲክፈል ክፍያውን በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ በድምሩ ብር 725,183.57 ለድርጅቶቹ ሲክፈል ክፍያውን በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ መሆኑን በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

6. በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5/መ ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብለት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ በበጀት ዓመቱ

- **በዋናው መ/ቤት** ብር 7,240,475.57፤
- **በሚሲዮኖች ብር 99,076,321.37**

በአጠቃላይ በድምሩ ብር **106,316,796.94** በተሰብሳቢ የተያዘበት ማስረጃ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ተከፋይ ሂሳብ፤

7. የፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 5(ሀ) ማናቸውም ወደፊት ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ ይኖርበታል ይላል፡፡ ይሁን እንጂ
   - በዋናው መ/ቤት **ብር 5,922,154.37፤**
   - በሚሲዮን **ብር 40,148,550.73፤**

በድምሩ ብር 46,070,705.10 ማስረጃ ያልቀረበለት ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 7 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የመ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

ትኩረት የሚሹ ጉዳዩች፤

ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የሚቀይረው ባይሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፤ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

ገቢ፤

8. የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1ለ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ማናቸውንም ገቢ በውጭ አገር ምንዛሪ የሚሰበሰብ ከሆነ በውጭ ምንዛሪ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ መሂ/2 ወይም ሚኒስቴሩን በማስፈቀድ በኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ መሰብሰብ እንዳለበት ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ **በዋሽንግተን ኤምባሲ** በተለያዩ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች የተሰበሰበ **ብር 24,658.55 (693.24ዶላር)** ከሳጥን ወደ ባንክ ገቢ የተደረገ ሲሆን፤ ገቢ በተደረገው የገንዘብ መጠን ልክ የውጭ ምንዛሪ የገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለት ልዩ ልዩ ገቢ በሚል በ1489 የሂሳብ መደብ በገቢ ተይዞ ተገኝቷል፡፡
9. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ገቢ በኢሚግሬሽን የአገልግሎት ክፍያ ተመን መመሪያ ቁጥር 1/2007 ዓ.ም መሰረት ገቢን በገቢ ምንጩና በገቢ ተመኑ መሰረት የሚሰበሰብ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በዱባይ ቆንስላ ጽ/ቤት በተለያዩ የገቢ ደረሰኞችና ቀናቶች በድምሩ ብር 179,488.73 ገቢ ሲሰበሰብ በገቢ ደረሰኙ ላይ የገቢው ምክንያት ሙሉ በሙሉ ሳይገለጽ እና በግልጽ ሳይጠቀስ ገቢ በመደረጉ በምን ያህል የገቢ ተመን እና የትኛው የገቢ ዓይነት እንደተሰበሰበ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
10. የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 10 ተራ ቁጥር 3 መሠረት ማንኛውም የመንግስትን ገንዘብ እንዲቀበል ወይም እንዲሰበስብ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የተቀበለውን ወይም የሰበሰበውን የመንግስት ገንዘብ ወደ ተጠቃለለው ፈንድ ገቢ ያደርጋል ይላል፡፡ ይሁን እንጂ በዱባይ ቆንፅላ ፅ/ቤት በተለያዩ የገቢ መሰብሰብያ ደረሰኞችና ቀናቶች የተሰበሰበ ገቢ ብር 37,205.76 በገንዘብ ገቢ ደረሰኝ ላይ ገንዘቡን የተቀበለው ወይም የሰበሰበው ባለሞያ ስም ሳይገለፅና ሳይፈረም ተገኝቷል፡፡

ወጪ፤

11. ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣዉ የእቃና የአገልግሎት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 24/3 መሰረት እንዲሁም ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ሕ/አ/2/59 ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣዉን የእቃና የአገልግሎት ግዥ አንዳንድ አንቀጾችን ለማሻሻል በወጣው መመሪያ መሰረት ከብር 150,000.00 በላይ የሆኑ የአገልግሎት ግዥዎች እና ከብር 200,000.00

በላይ ለዕቃ ግዥ በግልጽ ጨረታ መግዛት እንዳለበት ይገልጻል፡፡ እንዲሁም በሚሲዮኖች ያለውን የግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ለመመራት በ3/12/2010 በጸደቀው መመሪያ ክፍል 2 አንቀጽ 16 ንኡስ አንቀጽ 2 በአንድ ጊዜ የሚፈጸመዉ የግዥ መጠን ከ500 የአሜሪካ ዶላር በላይ በሚሆንበት ጊዜ እና ግዥውን ዋጋ በማሰባሰብ ማወዳደር የማይቻልበት ሁኔታ ሲያጋጥም የግዥ ኮሚቴ በሚያቀርበው የውሳኔ ሃሳብ የያዘ ቃለ-ጉባኤ መሰረት በሚሲዮኑ መሪ ጸድቆ ተግባራዊ ይደረጋል ይላል፡፡ በዚሁ መሰረት በዋና መ/ቤትና በኤምባሲዎች፤

- በዋናው መ/ቤት በቀጥታ ግዥ ዘዴ **በድምሩ በብር** 8,767,053.55፤
- በኒውዮርክ ሚሲዮን **በድምሩ ብር** 1,249,178.21 (35,118.87 **ዶላር**)፤
- በፕሪቶሪያ ኤምባሲ **በድምሩ ብር** 1,870,521.61 (946,142.61 **ራንድ**)፤
- በለንደን ኤምባሲ **በድምሩ ብር በድምሩ ብር** 102,256,227.66 (2,874,788.52 **ፓውንድ**)፤
- በናይሮቢ ኤምባሲ **በድምሩ ብር** 911,262.05 (2,688,088.72 **ሽልንግ**) ፤

በድምሩ ብር 12,932,641.65 ከመመሪያ ውጪ የእቃና የአገልግሎት ግዥ በቀጥታ ግዢ ለተከናወነበት ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

12. የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም. በክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ተራ ቁጥር 4 ላይ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣውን ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይቶ በተሰጠ የበጀት መለያ መደብ ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው ይገልጻል:: ይሁን እንጂ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤
    - በዋናው መ/ቤት በድምሩ ብር 17,176,806.43፤
    - በኒውዮርክ ኤምባሲ በድምሩ ብር 1,228,851.78 (34,547.42 **ዶላር**)፤
    - በመስኮት ኦማን ኤምባሲ በድምሩ ብር 58,199.42 (**ሪያድ** 636.30)፤
    - በለንደን ሚሲዮን በድምሩ **ብር** 767,367.25 (16,271.57 **ፓውንድ**)፤
    - የናይሮቢ ኤምባሲ በድምሩ **ብር** 719,197.50 (1,400,957.74 **ሽልንግ**)

በጠቅላላ በድምሩ ብር 19,950,422.38 የሂሳብ አርዕስታቸውን ሳይጠብቁ በወጪ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡

13. ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመርያ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 24.8 መ/ቤቱ በዋጋ ማቅረብያ በተደጋጋሚ ለሚፈጽማቸው ግዥዎች ከስታስቲክስ

ኤጀንሲው ድረ-ገጽ የሚወጣውን ወቅታዊ የዋጋ ዝርዝር እና በግዥ ስራ ክፍሉ የሚካሂድ የገበያ ጥናት በመጠቀም ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ ዋጋ መሆኑን ማመን ይኖርበታል ይላል፡፡ ይሁን እንጂ መ/ቤቱ የገበያ ጥናት ሳይደረግ በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ግዥው ተከናውኖ **ብር 1,043,052.47** ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

14. ሰኔ 2002 በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 16.27 ውልን በተመለከተ ንዑስ አንቀጽ 16.27.1 ማናቸውም የመንግስት መ/ቤት የመደበኛ ጨረታ ሠነዶች አንድ ክፍል የሆነውን አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች እና ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን ልዩ የውል ሁኔታዎች የያዘውን የውል ሠነድ ከአቅራቢው ጋር መፈራረም እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ መ/ቤቱ ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር ውል በመውሰድ ክፍያ ሲፈጽም በውሉ ላይ መካተት የሚገባቸው ሁኔታዎች የውሉ አካል ሳይደረጉ **በድምሩ ብር 2,528,159.03** ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

15. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሃምሌ 2009 ዓ.ም ባወጣው የወጭ ቅነሳ መመሪያ አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 8 የማስታወቅያ ወጪን በተመለከተ፡- ባለበጀት መ/ቤቶች ለህዝብ ጥቅም መተላለፍ ካለባቸው መልዕክቶች በስተቀር ራሳቸውን በብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች ማስተዋወቅ እና ሌሎች ድርጅቶችን ወይም በዓላትን ስፖንሰር ማድረግ አይቻልም፡፡ የመንግስት በጀትን በድጋፍ ስፖንሰር ማድረግ አይቻልም ይላል፡፡ ይሁን እንጂ መ/ቤቱ መ/ቤቱ ስፖንሰር ያደረገውን የኢድ አል አድሃ (የአረፋ) በዓልን ላቀረበበት **ብር 350,000.00** ለዋልታ ሚዲያና ኮሚዩኒኬሽን ኮርፖሬት አ/ማ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

16. የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመርያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 4 ጥሬ ገንዘብ የማይንቀሳቀስባቸው ወይም ጥሬ ገንዘብ ያልሆኑ ማናቸውም የሂሳብ ክንውኖች በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ መሂ/9 መፈጸም አለባቸው ይላል፡፡ እንዲሁም የሂሣብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ1ሀ እና1ለ የገቢ መሰብሰብያ ደረሰኝ አገልግሎቱ ገቢ ለመሰብሰብ ብቻ ስለመሆኑ በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ ይሁን እንጂ
በኒውዮርክ ኢምባሲ በድምሩ ብር 126,327.92 (3,551.53 ዶላር) በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ መሂ/9 መወራረድ ሲገባው ያለአግባብ በውጪ ምንዛሪ የገቢ ደረሰኞች የተወራረደ መሆኑ ታውቋል፡፡

17. የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት ስለገንዘብ ክፍያ፤ አንቀጽ 9 ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች ከሚለው ስር ንኡስ አንቀጽ

1 ላይ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት እቃው እንዲገዛ ወይም አገልግሎት እንዲሰጥ ትእዛዝ የተሰጠበት ማስረጃ መኖሩን ማረጋገጥ እንደሚገባ በግልጽ ያስቀምጠል፡፡ ይሁን እንጂ

- በኒውዮርክ ኤምባሲ በድምሩ ብር 929,016.55 (26,117.98 ዶላር)፤
- በናይሮቢ ኤምባሲ በድምሩ ብር 463,124.81(1,366,149.88 ሽልንግ)፤ እንዲሁም
- በኦማን ኤምባሲ በድምሩ ብር 69,315.03 (748.3 ሪያል)፤

በአጠቃላይ በድምሩ ብር 1,461,456.39 ለተለያዩ ድርጅቶች በተለያዩ ቀናትና በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች እቃና የአገልግሎት ግዥ ለተገዛበት ሲከፈል ግዥዎቹ የግዥ መጠየቂያ የሌላቸው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

18. የፌደራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀፅ ዘጠኝ ተራ ቁጥር 7 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ለተገዛ እቃ/አገልግሎት ሂሳብ ማወራረጃ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ኦርጅናል ደረሰኝ መሆን እንዳለበት በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ ይሁን እንጂ

በዋናው መ/ቤት በቀን 5/6/2013 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 21613 ብር **176,829.32** እንዲሁም በቀን 6/5/2013 በወጪ ማስስከሪያ ቁጥር 20490 **ብር 82,201.55 በድምሩ ብር 259,030.87** ከበላይ አብ ሞተርስ ተሽከርካሪ ላስጠገነበት በዱቤ የሽያጭ ደረሰኝ (Credit sales invoice) ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

19. የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመርያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለ ወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረብ እና ስልጣን ባለው አካል መፈቀድ አለበት በማለት ይደነግጋል፡፡ ይሁን አንጂ መስተንግዶው ለየትኛው ልዑክ እንደተፈፀመ የሚገልፅ ዝርዝር ደጋፊ ማስረጃ ከክፍያ ሰነድ ጋር ሳይቀርብ፤

- የናይሮቢ ኢምባሲ በድምሩ ብር 412,244.24 (1,216,059.69 ሽልንግ)፤
- በፕሪቶሪያ ኤምባሲ በተለያዩ ቀን እና የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥሮች ለተለያዩ ድርጅቶች በድምሩ ብር **134,913.78**፤

በአጠቃላይ በድምሩ ብር **547,158.02** ተገቢ ደጋፊ ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ ታውቋል፡፡

ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

20.በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 ፣ የፌደራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ቅድሚያ ክፍያዎች በወቅቱ የሚወራረዱ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤

- በዋናው ፋይናንስ በድምሩ ብር 7,850,787.11፤ እንዲሁም
- በሚሲዮን ፋይናንስ በድምሩ ብር 107,141,174.79

በአጠቃላይ በድምሩ ብር **114,991,961.90** በወቅቱ ሳይወራረድ በተሰብሳቢ ተይዞ ተገኝቷል ።

ተከፋይ ሂሳብ፤

21. በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 5/ሐ የተለያዩ አካላት ቀንሰው ያስቀሩትን የግብር እና ሌሎች ሂሳቦች ለሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ አካል ወቅቱን ጠብቀው ማስተላለፍ እንዳለበት ያስቀምጣል። ይሁን እንጂ ፤
   - በዋናው ፋይናንስ **በድምሩ ብር 5,715,851.95 እንዲሁም፤**
   - በሚሲዮን ፋይናንስ **በድምሩ ብር 40,134,622.13**

በአጠቃላይ በድምሩ ብር 45,85,0474.08 የተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ሳይከፈል ተገኝቷል።

በጀት፤

22. በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል 3/12 መሰረት የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ሊፈጸም ወይም ወጪ ሊደረግ የሚችለዉ የተፈቀደ በጀት ሲኖር ነዉ ይላል፤ ይሁን እንጂ
   - በሂሳብ መደብ 2311203 በበጀት አመቱ የተፈቀደው በጀት **ብር 136,711,682.35** ሲሆን፤ በሂሳብ መደቡ ብር **145,929,931.42** ወጪ የተደረገ በመሆኑ ከተመደበው በጀት በላይ **ብር 9,218,249.07** ባልተፈቀደ በጀት ክፍያ ተገኝቷል።
   - በመ/ቤቱ በዋናው ፋይናንስ በበጀት ዓመቱ በተለያዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው መደበኛ በጀት ስራ ላይ ያልዋለ በጀት **ብር 128,488,326.70 ተገኝቷል።**

ሌሎች ጉዳዮች፤

ንብረት፤

1 **ቋሚና አላቂ እቃዎች፤**

- በአላቂና ቋሚ እቃ ንብረት ክፍል ውስጥ እንዲሰሩ የተመደቡ ሰራተኞች ገቢንም ወጪንም ደርበው /ቀላቅለው የሚሰሩ መሆኑ፤
- ለናሙና ቀርበው የነበሩ 2 የሴትና 2 የወንድ ሙሉ ልብሶች፤ 2 የወንድና 2 የሴት ሸሚዞች፤1 ጫማ እና 1 የሴት ኮት ያለ ርክክብና የገቢ ደረሰኝ በስቶሩ የሚገኙ መሆኑ፤
- የመፈተሻ እቃዎች ገቢ ሳይደረጉ /በአደራ ሲቀመጡ የተዘጋጀ ፎርም ሳይኖር በስቶር መገኘታቸውን፤
- በግምጃ ቤት የእሳት ማጥፍያ ቢኖርም የአገልግሎት ዘመኑ ያለፈበት መሆኑ፤ በተመሳሳይ አገልግሎቱ ያለፈባቸው 5 አዳዲስ የእሳት ማጥፍያዎች ለአመታት ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፤
- የተበላሹ ብዛት ያላቸው ደረሰኞች /የቫት ደረሰኞች፤ እና ሞዴሎች በስቶር የሚገኙ መሆኑ፤
- አልፎ አልፎ ቢን ካርድ ያልተዘጋጀላቸው ንብረቶች፤ አንዳንድ ቢን ካርዶች ላይ መቼ ገቢ እንደተደረጉ የማይገልጽ መሆኑ፤
- ከስቶር ውጭ ጠረጴዛ፤ መካከለኛ ሽልፍ፤ ወንበርና ሌሎች ንብረቶች የሚገኙ መሆኑ፤
- ያለ ህጋዊ ርክክብ/ጊዚያዊ ንብረት ማስቀመጫ/ ብዛት ያላቸው ጠረጴዛዎች፤ 2 መኪና ጎማዎች፤ ብዛቱ የማይታወቅ የተለያዩ አገራት ባንዴራዎችና የባንዴራ መስቀያዎች /ማስቀመጫዎች፤ ብዛታቸው የማይታወቅ ጥላዎች፤ የመኪና የወንበር ልብሶች፤ አዳዲስ ያልተሰራበው ደረሰኞች፤ የተለያዩ የዱንካን ብረቶች፤ 19 ፍራሾች፤ 1 አልጋ፤ እና ሌሎች እቃዎች ገቢ ሳይደረጉ ማለትም ከሚጠቀምበት አካል ርክክብ ሳይደረግ በተመላሽ ስቶር በር ላይ የሚገኙ መሆኑ፤
- የሚሰሩና የማይሰሩ በሚል ያልተለዩ 9 የተለየዩ አይነት ተመላሽ ላፕቶፖች፤ ከ7 በላይ ፕሪንተሮች፤ 1 ፋክስ፤ 25 ዩፒኤስ፤ ከ8 በላይ የፎቶ ኮፒ ማሽኖች፤ 55 ኢንች ቲቪ፤ ብዛት ያላቸው የስልክ ቀፎዎች፤ የውሃ ማጣሪያና፤ የተለያዩ የመኪና ባትሪዎች የሚገኝ መሆኑ፤
- የሚሰራ፤ የማይሰራ እና አዳዲስ እቃዎች/ንብረቶች ባልተገባ ሁኔታ የሚገኙ መሆኑ፤
- የእሳት አደጋን ለመከላከል እንዲቻል የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ መዘጋጀት ሲገባው በተመላሽ ዕቃዎች ማስቀመጫ መጋዘን ውስጥ የሌለ መሆኑ፤

- በርካታ አዳዲስ የእንግዳ መቀመጫ ወንበሮች፤ ብዛት ያላቸው የመኪና ጎማዎች፤ እና ሌሎች የተለያዩ እቃዎች ባልተገባ እና ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- በመረጃ ሀብት ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን የስራ ክፍል እና በግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ብዛቱ የማይታወቅ የተለያዩ ዕቃዎችና የተቋሙ ንብረቶች ያልሆኑ ንብረቶች የሚገኙ መሆኑ በ2013 የንብረት ቆጠራ ሪፖርት ላይ ለማረጋገጥ ተችላሏል፡፡

2. <u>የተሽከርካሪ አያያዝን በተመለከተ</u>፤

- አንድ ላንድ ክሩዘር ተሽከርካሪ በኮድ 2-63258 ታርጋ የሚገኝ/የሚሰራ መሆኑ፤
- **አንድ አሽከርካሪ** ከአንድ በላይ ተሽከርካሪ ወጪ የሚያደርግ መሆኑ፤ ለምሳሌ አቶ ተፈራ በቀለ 21፤ አቶ ተስፋየ ግርማይ 7፤ አቶ ታደሰ አክሊሉ 9 ፤ አቶ ደጀኔ ጌታቸው 6፤ አቶ አብዱላዚዝ ሙሃመድ 3፤ እንዲሁም አቶ መልካሙ ከበደ 5 ተሽከርካሪዎች ወጪ ያደረጉ መሆኑን፤
- ለኮድ 4-24536 በተከፈተ የግል ማህደር ውስጥ የተሽከርካሪው ሊብሬ ያልተያያዘ መሆኑ፤
- የተበላሹና የሚወገዱ ተሽከርካሪዎች አንድ የሞተር ሳይክልን ጨምሮ በተለያየ ቦታ ለተጨማሪ ብልሽት በሚያጋልጥ ሁኔታ ተበታትነው የሚገኙ መሆኑ፤
- እስካንያ ቪአይፒ ባስ ኮድ 4-20315 በጥገና ምክንያት (ከሁለት አመት በላይ) የቆመ መሆኑ፤
- ቶይታ ያሪስ 4-15866 በጋራጅ ለጥገና ከ25/10/2013 ዓ.ም ጀምሮ የቆመ መሆኑ፤
- ሃይወንዳይ ሳንታፌ ኮድ 4-13453 እና 4-13454 ለጥገና ከ16/9/2013 ጀምሮ መቆመ መሆኑ፤
- ሃይወንዳይ ባስ ኮድ 4-13393 በጋራጅ ከ14/8/2013 ዓ.ም ጀምሮ የተቀመጠ መሆኑ፤
- እስካንያ አውቶብስ ኮድ 4-17956 እና 4-16397 የኪሎ ሜትር ንባቡ የማይሰራ መሆኑ፤
- ብዛት ያላቸው ተሽከርካሪዎች የሰርቪስ ጊዜያቸው ያለፈባቸው፤ ጥገና ያልተደረገላቸው መሆኑ፤

<u>ሌሎች ጉዳዮች</u>

- የፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀፅ '6' ንዑስ አንቀፅ '2' ፊደል "ለ" የበላይ ሃላፊዎች በመስሪያ ቤቱ የተቋቋመው የውስጥ ኦዲት ተገቢና በቂ የሰለጠነ የሰው ሀይል ያለው መሆኑን፣ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-__ የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬቱ በመዋቅሩ መሰረት ዳይሬክተሩን ጨምሮ 11 የሰው ሃይል እንደሚያስፈልገው የተገለጸ ቢሆንም ያለው የሰው ሃይል ግን 1 ተወካይ ዳይሬክተር፤ 1 ቡድን መሪ፤1 ከፍተኛ ኦዲተር እና 2 ጀማሪ ኦዲተር በድምሩ 5(አምስት) የሰው ሃይል /ኦዲተር/ ብቻ ሲሆን ቀሪው 6 የሰው ሃይል ያልተሟላ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማረገገጥ ተችሏል፡፡

- የፌደራል መንግሥት ሠራተኞች የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 11/2003 አንቀጽ 6 የመንግስት መ/ቤቶች ሃላፊነት ንዑስ አንቀጽ 1 ማንኛዉም የመንግሥት መስሪያ ቤት ከሚለው ስር፤ የፌደራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር እና የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ እና እነዚህን አዋጆች ለማስፈጸም በወጡ፣ ደንቦች እንዲሁም መመሪያዎች ስለመንግሥት ገንዘብና ንብረት አጠባበቅ፣አመዘጋገብና አያያዝ፣ ስለወጪ አከፋፈልና ጥቃቅን ወጪዎች የተወሰነ ገንዘብ እንዲሁም በግዥ ላይ ሊወሰዱ ስለሚገባቸዉ ጥንቃቄዎች የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በገንዘብ ያዥነትና ሰብሳቢነት ወይም ንብረት ያዥነት ወይም በጥበቃ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ሰራተኞች ሁሉ ለተሰጣቸዉ ኃላፊነት የሚሆን ዋስትና ወይም ተያዥ እንዲሰጡ እንዲያቀርቡ ማድረግ ይኖርበታል በማለት ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ በመ/ቤቱ 4 ገንዘብ ሰብሳቢዎች እና 9 የንብረት ሰራተኞች በመመሪያው መሰረት በቂ ዋስትና ማቅረብ ሲገባቸው ያላቀረቡ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከሰላምታ ጋር

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

ኦዲት ሥራ አመራር ሪፖርት፤

መግቢያ፤

የፌዴራልዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት **የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር** የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ መ/ቤቱን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

የሪፓርቱ ዓላማ፤

የዚህ ሥራ አመራር ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የመ/ቤቱ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፤

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት መ/ቤቱ ባዘጋጃቸው የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ /የኦዲት አስተያየት /ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን የሚያካትተው፡፡

- በሂሣብ ሪፖርቶቹ ላይ የሠፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎች የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሣብ ሪፖርቶቹን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸውን ጉልህ ግምቶች እና ውሣኔዎች መመዘን፣
- የመ/ቤቱ ሂሣብ አያያዝ የፌደራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ የተከተለ መሆኑን፣ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን፣ ያጠቃልላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የሂሣብ ሪፖርቶቹ አግባብነት ያላቸውን አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና መመርመርን ይጨምራል፡፡

የሂሣብ ሪፖርቶቹ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የጸዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሣብ ሪፖርቶቹ ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሠራርም ሆነ የሂሣብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ በመሆኑ የሂሣብ ሪፖርቶች ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥሮችና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሣይ አይችልም፡፡

የሂሣብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የመ/ቤቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሣብ ሪፖርቶችን ኦዲት ማድረግና ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የመ/ቤታችን ኃላፊነት ነው፡፡

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሣቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. **የገቢ ሂሳብ፤**

1.1 **ግኝት፤ ገቢ ያልተደረገ የጉዳት ካሳ ብር 236,104.50፤**

የፌዴራል መንግሥት የግዢ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/4 (ሀ) እና (ለ) መሰረት አቅራቢው ሳይፈጽም በቀረው የውል መጠን ላይ ውል ሰጪ የመንግስት መ/ቤቶች በየቀኑ 0.1% ወይም 1/1000ኛ ከውሉ ዋጋ 10 በመቶ ሳይበልጥ የጉዳት ካሳ ሊሰበስቡ እንደሚገባ ያስቀምጣል፡፡ በዚህም መ/ቤቱ መመሪያውን ተግባራዊ ማድረጉን ለማረገገጥ ኦዲት ሲደረግ፤- ለአገልግሎትና ለዕቃዎች ግዥ በተገባው ውሉ መሰረት ገቢ ላልተደረገበት የጉዳት ካሳ በድምሩ ብር 236,104.50 ከድርጅቶች ክፍያ ላይ በመቀነስ ለመ/ቤቱ ገቢ መደረግ ሲገባው ገቢ ያልተደረገ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ (ዝርዝሩም በአባሪ 01 ተመልክቷል)

ስጋት፤

- ዕቃዎቹ በውሉ መሰረት በወቅቱ ባለመቅረባቸው መንግስት ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል፡፡
- ክትትል ላይደረግበት ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ፤

አቅራቢው በገባው የውል ጊዜ መሠረት ባለማቅረቡ መ/ቤቱ ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም ባለማግኘቱ ለደረሰበት ጉዳት ገቢ መደረግ የሚገባው የጉዳት ካሳ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች ገቢ እንዲደረግ እና ለወደፊቱም አቅራቢዎች በውላቸው መሠረት ለመፈፀማቸው ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

- የውል አፈጻጸሙ በአስገዳጅ ሁኔታዎች ተብሎ በሚገመትበት የሀገር አቀፍና አለም አቀፋዊ ተጽዋ ምክንያት በተገባዉ ዉል መሰረት ማጠናቀቅ ባለመቻሉ መ/ቤቱ ይህንን ከግንዘቤ በመዉሰድ የተወሰኑ ድርጅቶችን የተቀበለ መሆኑና እና በቀጣይ በሚዘጋጁ ዉሎች የተሰጠዉን አስተያየት የምናካትት መሆኑን፣
- የተወሰኑ ድርጅቶችን በገጠማቸው ከአቅም በላይ ችግር መ/ቤታችን ከተገባው ውል ቀነ ገደብ ውጭ ገቢ እንዲያደርጉ የተቀበለው መሆኑ ለዚህም የመስሪያ ቤቱ ጥቅም እቃው ቢገባ

የተሻለ ነው ተብሎ ስለታመነ እና በቀጣይ በሚዘጋጁ ውሎች የተሰጠውን አስተያየተ የምናካትት መሆኑን ፤

- የውል አፈጻጸም በአስገዳጅ የሀገር አቀፍና ዓለም አቀፋዊ ተፅእኖ የተነሳ የግዥ ሂደት ላይ እያለ የCOVID -19 ወረርሽኝ በመከሰቱ ታውጆ የነበረው አስቸኮይ ጊዜ አዋጅ ምክንያት ከሁሉም ወገን ከአቅም በላይ የሆነ የተፈጥሮ ችግር ላይ Force Majeure በመደበኛ የጊዜ ሰሌዳው መከናወን ስላልቻለና በአቅራቢዎች በኩል የተከሰተ ችግር ስላልነበር የጉዳት ካሳ ሳይጠየቅ ግዥዉ ተፈጽሟል። በቀጣይ የተሰጠዉን አስተያየቱ ትኩረት ሠጥተን የምንሠራ መሆኑን ከግንዛቤ ዉስጥ በማስገባት ከግኝት እንዲወጣልን እንጠይቃለን።

1.2 <u>ግኝት፤ የገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥ ባንክ ገቢ የተደረገ የልዩ ልዩ ገቢ ብር 24,658.55፤</u>

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 ክፍል አራት ቁጥር 22.2 ላይ ገንዘብ ለመሰብሰብ ውክልና የተሰጠው ሰው ለሰበሰበው የመንግሥት ሕጋዊ የገቢ ደረሰኝ ለከፋዩ መስጠት እንዳለበት ይገልጻል። እንዲሁም የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1ለ የመንግስት መስሪያቤቶች ማናቸውንም ገቢ በውጭ አገር ምንዛሪ የሚሰበሰብ ከሆነ በውጭ ምንዛሪ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ መሂ/2 ወይም ሚኒስቴሩን በማስፈቀድ በኤልክትሮኒክስ ደረሰኝ መሰብሰብ እንዳለበት ይገልፃል። ይሁን እንጂ በዋሽንግተን ኤምባሲ በተለያዩ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች የተሰበሰበ **ብር 24,658.55 (693.24ዶላር)** ከሳጥን ወደ ባንክ ገቢ የተደረገ ሲሆን፤ ገቢ በተደረገው የገንዘብ መጠን ልክ የውጭ ምንዛሪ የገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለት ልዩ ልዩ ገቢ በሚል በ1489 የሂሳብ መደብ በገቢ ተይዞ ተገኝቷል።

<u>ስጋት፤</u>

- በመንግስት የሚወጡ መመሪያዎች ሊጣሱ ይችላሉ።
- ገቢ በአግባቡ ላይሰበሰብ ይችላል።

<u>የማሻሻያ ሃሳብ፤</u>

በሚሲዮኑ የሚሰበሰቡ ማንኛውንም አይነት ገቢ በመመሪያው መሰረትና በወጣለት ተመን ልክ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ እየተቆረጠለት ሊሰበሰብና ባንክ ገቢ ሊደረግ ሲገባ በድምር በመሆኑ የሚለው ምላሽ ተቀባይነት የለውም። በመሆኑም ለወደፊቱም ሚሲዮኑ ገቢ የገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት መሆኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል።

የሥራ አመራሩ ምላሽ

በዋሽንግተን ኤምባሲ በተለያየ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች የተሰበሰበ ገቢ ከሳጥን ወደ ባንክ ገቢ በሚያደርግበት ወቅት ልዩ ልዩ ገቢ በሚል በ1489 የሂሳብ መደብ ብር 24,658.55 በሂሳብ ማዘዣ ገቢ የተደረገ መሆኑን ለሚለው በኦዲት ወቅት ከተሰጠው ምላሽ በተጨማሪ በልዩ ልዩ ገቢ ተመዝግቦ የሚታየው ገንዘብ መጠን አንደኛ በግኝት ቁጥር 1.3 ላይ የተጠቀሰው ግኝት ለማየት እንደሚቻለውና ከዚህ ግኝት ጋር ተያያዥነት ያለው መሆኑ ታሳቢ እንዲደረግ ያህል በብልጫ የገባ ገንዘብ በአገሩ ባለው አሰራር መሰረት ሚሲዮኑ ከገንዘብ አስተላላፊ ድርጅት በጥቅል ወደ ባንክ ገቢ ያደረገበት አድቫይስ ሲደርሰው ወደ ሚሲዮኑ ባንክ አካውንት ለገባው ገንዘብ Cash at Bankን በምዝገባ ማዘዣ ሲመዘግብ በብልጫ ገቢ የሆነውን ገንዘብ በልዩ ልዩ ገቢ የተመዘገበ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

የኦዲተር አስተያየት

በብልጫ ለተመዘገበው ገቢ ተመጣጣኝ የገቢ ደረሰኝ እንዲዘጋጅ መመሪያው የሚያዝ በመሆኑ ተገቢው የገቢ ደረሰኝ ሊቀረጥ ይገባል፡፡

1.3 ግኝት፤የገቢው ምክንያት ሳይገለጽ የተሰበሰበ ገቢ ብር 179,488.73 ፤

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ገቢ በኢሚግሬሽን የአገልግሎት ክፍያ ተመን መመሪያ ቁጥር 1/2007 ዓ.ም መሰረት ገቢን በገቢ ምንጩና በገቢ ተመኑ መሰረት የሚሰበሰብ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በዱባይ ቆንስላ ጽ/ቤት በተለያዩ የገቢ ደረሰኞችና ቀናቶች **በድምሩ ብር 179,488.73** ገቢ ሲሰበሰብ በገቢ ደረሰኙ ላይ የገቢው ምክንያት ሙሉ በሙሉ ሳይገለጽ እና በግልጽ ሳይጠቀስ ገቢ በመደረጉ በምን ያህል የገቢ ተመን እና የትኛው የገቢ ዓይነት እንደተሰበሰበ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ስጋት፤

- ፍትሀዊ የአገልግሎት አሰጣጥ ላይኖር ይችላል፡፡
- ገቢው በወጣለት ተመን መሰረት መሰብሰቡን ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ፤

ማንኛውም ገቢ የገቢው ምክንያት በገቢ ደረሰኙ ላይ በአግባቡ ሊገለጽና በወጣው ተመን መሰረት መሰብሰቡ ተገቢው የቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

በዱባይ ቆንስላ ፅ/ቤት በተለያዩ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ብር 179,488.73 ገቢ ሲሰበሰብ የገቢ ደረሰኙ ላይ የገቢው ምክንያት ሙሉ በሙሉ ሳይገለጽ እና በግልጽ ሳይጠቀስ ገቢ የተሰበሰበ ለሚለው በኦዲት ወቅት ከተሰጠው ምላሽ በተጨማሪ በCovid -19 ወረርሽኝ ምክንያት የቆንስላ አገልግሎት የሚሰበስቡ ሰራተኞች በቁጥር ማነስ እና የሚሰጠው አገልግሎት ሰፊ ከመሆኑ አንፃር ከስራ መደራረብ የተነሳ አልፎ አልፎ የተፈጠረ መሆኑን እየገለፅን፤ የሰጠውን አገልግሎት ለማረጋገጥ እንዲቻል በአባሪው ላይ የተጠቀሱትን የውጭ ምንዛሪ የገቢ ደረሰኝ ቁጥሮች መሰረት በማድረግ የአገልግሎቱን ዓይነት በሚሲዮኑ ቀሪ ደረሰኝ ላይ በማስፈር በሚሲዮኑ በኩል የቀረበ መሆኑን እየገለፅን ያለውን የስራ ስፋት ከግምት ውስጥ በማስገባ ግኝቱ በድጋሚ እንዲታይልን እንጠይቃለን፡፡

<u>**የኦዲተር አስተያየት**</u>

የተሰበሰበውን የገቢ ዓይነት በገቢ ደረሰኝ ላይ በተገቢው ሁኔታ መገለፅ ሲገባው በሚሲዮኑ ቀሪ ደረሰኝ ላይ መስፈሩ የተገለጸ ቢሆንም ይህንን ለማረጋገጥ የሚያስችለ ማስረጃ ለኦዲቱ ሥራ አልቀረበም፡፡ በመሆኑም በገቢ ደረሰኙ ላይ የገቢው ምክንያት ሊገለጽ ይገባል፡፡

1.4 ግኝት፤<u>የገንዘብ ገቢ ደረሰኝ በተቀባይ ሳይፈረም የተከፈለ ብር 37,205.76 ፤</u>

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 10 ተራ ቁጥር 3 መሠረት ማንኛውም የመንግስትን ገንዘብ እንዲቀበል ወይም እንዲሰበስብ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የተቀበለውን ወይም የሰበሰበውን የመንግስት ገንዘብ ወደ ተጠቃለለው ፈንድ ገቢ ያደርጋል ይላል፡፡ ይሁን እንጂ በዱባይ ቆንፅላ ፅ/ቤት በተለያዩ የገቢ መሰብሰብያ ደረሰኞችና ቀናቶች የተሰበሰበ ገቢ **ብር 37,205.76** በገንዘብ ገቢ ደረሰኝ ላይ ገንዘቡን የተቀበለው ወይም የሰበሰበው ባለሞያ ስም ሳይገለፅና ሳይፈረም መገኘቱ ተገኝቷል፡፡

<u>**ስጋት፤**</u>

- ገቢው/ገንዘቡ በሚመለከተው አካል የተሰበሰበ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ አዳጋች ሊሆን ይችላል፡፡
- በገቢ አሰባበሰቡ ሂደት ላይ ለሚፈጠር ችግር ተጠያቂነትን ለማስፈን ሊያስቸግር ይችላል፡፡

<u>**የማሻሻያ ሃሳብ፤**</u>

ገቢው በሚመለከተው አካል የተሰበሰበ ስለመሆኑ ማረጋገጥ እንዲቻል ገቢውን የሚሰበስብበው አካል በደረሰኙ ላይ በፊርማው ትክክለኛነቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

በዱባይ ቆንስላ ፅ/ቤት በተለያዩ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ብር 37,205.76 ሲሰበሰብ የገቢ ደረሰኙ ላይ ያዘጋጀው እና የተቀባይ ስምና ፊርማ የሌለው ለሚለው በኦዲት ወቅት ከተሰጠው ምላሽ በተጨማሪ በCovid -19 ወረርሽኝ ምክንያት የቆንስላ አገልግሎት የሚሰበስቡ ሰራተኞች በቁጥር ማነስ እና የሚሰጠው አገልግሎት ሰፊ ከመሆኑ አንፃር ከስራ መደራረብ የተነሳ አልፎ አልፎ የተፈጠረ መሆኑን እየገለፅን፤ በደረሰኙ ላይ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ተቀባዩ ስለመቀበሉ በቀሪ ደረሰኝ ላይ ተፈርሞ በሚሲዮኑ በኩል የቀረበ መሆኑን እየገለፅን ያለውን የስራ ስፋት ከግምት ውስጥ በማስገባ ግኝቱ በድጋሚ እንዲታይልን እንጠይቃለን፡፡

የኦዲተር አስተያየት፤

ከኦዲቱ በኂላ በቀሪ ደረሰኝ ላይ ተፈርሞ መቅረቡ በተሰጠው ምላሽ ቢገለፅም፤ የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ተግባራዊ ሳይደረግ የኦዲት ግኝት እንዳይሆን ለማድረግ ሲባል ብቻ ተዘጋጅቶ መቅረቡ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ተገቢው የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ መደረጉ የገቢው ትክክለኛነት እንዲረጋገጥ እና ተጠያቂነት እንዲኖር የሚያደርግ በመሆኑ በገቢ አሰባሰብ ወቅት ገቢውን የሚያዘጋጀው ባለሞያ እና ገንዘቡን የተቀበለው ሰው በተገቢው ቦታ እንዲፈርሙ በማድረግ የውስጥ ቁጥጥሩ ሊጠናከር ይገባል፡፡

1.5 ግኝት፤ ከኮንትራት (ሎካል) ሰራተኞች ደመወዝ ያልተቀነሰ የሥራ ግብር ብር 15,202,769.03

የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ዓ.ም ክፍል አንድ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 አንድ ተቀጣሪ ከመቀጠር የሚያገኘው ገቢ በኢትዮጵያ የመነጨ ነው የሚባለው ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) ክፍያው የሚፈጸምበት ስፍራ ግምት ውስጥ ሳይገባ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚከናወን የቅጥር አገልግሎት የተገኘ ገቢ ወይም ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የቅጥር አገልግሎቱ የትም ቢከናወን በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሳዊ ሪፐብሊክ መንግስት ወይም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሳዊ ሪፐብሊክ መንግስት ስም ክፍያው ለተቀጠረው ከተፈጸመ ነው ይላል፡፡ በዚሁ ክፍል አንቀጽ 9 ማንኛውም ገቢ የሚያገኝ ሰው በዚህ አዋጅና ታክስ አስተዳደር አዋጅ መሰረት ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት ይላል፡፡ በተጨማሪም በዚሁ አዋጅ ክፍል ሁለት ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ስለመጣል ከሚለው ንዑስ አንቀጽ 1 በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም ተቀጣሪ በአንድ ወር ውስጥ ከመቀጠር ከሚያገኘው ጠቅላላ የወር

ወይም የወሩ ክፍያ ገቢ ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 01 በተወሰኑት ምጣኔዎች መሰረት በእያንዳንዱ ወር ግብር ይከፍላል ይላል፡፡ ይሁን እንጂ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተለያዩ የኢፌድሪ ኤምባሲዎች ለሚገኙ የሚሲዮን ኩንትራት ሰራተኞች ደመወዝ ብር **46,603,136.24** በተለያየ ፒቪ፣ ጀቪና በተለያዩ ቀናት ክፍያ የፈፀመ ሲሆን፤ ፤

- በኢፌዲሪ ፕሪቶሪያ ኤምባሲ ብር 2,394,641.97፤
- በኢፌዲሪ ኒወርክ ኤምባሲ ብር 4,272,483.33፤
- በኢፌዲሪ ለንደን ኤምባሲ ብር 5,919,774.00፤
- በኢፌዲሪ በመስኮት ኦማን ኤምባሲ ብር 1,383,137.96 እንዲሁም
- በኢፌዲሪ ናይሮቢ ኤምባሲ ብር 1,232,731.77

በድምሩ ብር 15,202,769.03 የስራ ግብር ተቀናሽ ተደርጎ ለመንግስት ገቢ መደረግ ሲገባ ሳይቀነስ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

ስጋት፤

- *መንግሥት ማግኘት የሚገባውን ገቢ ያሳጣዋል፡፡*
- *መንግሥት ያወጣውን አዋጅ ደንብና መመሪያ ተከትሎ ያለመፈጸም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡*

የማሻሻያ ሃሳብ፤

የኢምባሲ ኩንትራት ሰራተኞች ደመወዝ ላይ በደንብና በመመሪያው መሰረት መቀነስ ሲገባው ያልተቀነሰውን የስራ ግብር እንዲመልሱ /እንዲሰበሰብ/ በማድረግ ለገቢ ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት ገቢ ሊያደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም በገቢ ግብር አዋጁ መሰረት ሊፈጸም ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ኤምባሲ ፕሪቶሪያ፣ ኒዮርክ፣ ለንደን፣ ሙስካት/ኦማን፣ ናይሮቢ በድምሩ ብር 15,199,597.68 የስራ ግብር በመቀነስ ለመንግስት ገቢ ማድረግ ሲገባ ያልተደረገ መሆኑን ለሚለው ተጨማሪ ምላሽ በተቋማችን ስር በተለያዩ አገራት ያሉ ሚሲዮኖቻችን ላይ የተሰማሩ የዋና መ/ቤት ሰራተኞች በመ/ቤቱም ሆነ በሚሲዮኑ የአገልግሎት ቆይታቸው ጊዜ በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ዓ.ም መሰረት የግብር ግዴታቸውን እየተወጡ መሆኑን እየገለፅን፤ የኮንትራት ሰራተኞችን በተመለከተ ግን በሎካል ሰራተኝነት ሚሲዮኑ በሚገኝበት አገር ላይ የቅጥር ውል ፈፅመው ለተወሰነ ጊዜ አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን በመ/ቤታችን የውጭ ግንኙነት አዋጅ 790/2005 እንዲሁም በዋነኛነት በአገራቶች ስምምነት በ1961 የቬይና ኮንቬንሽንና በሪስፕሮሲቲ ስምምነት አንቀፅ 37 ቁጥር 3 ላይ እንደተጠቀሰው Member of the

service staff of the mission በሚል ከታክስ ነፃ መሆናቸውን ይገልፃል፤ በመሆኑም በዚሁ መሰረት ሚሲዮኖች ከኮንትራት ቅጥር የሚገኝ ገቢ ላይ ታክስ የማይሰበስቡ መሆኑን እየገለፅን

የኦዲተር አስተያየት፤

እ.አ.አ በ1961 የዲፕሎማቲክ ግንኙነት የቬይና ኮንቬንሽንና በሪስፕሮሲቲ ስምምነት እና የውጭ ግንኙነት አገልግሎት አዋጅ 790/2005 መሰረት የስራ ግብር የማይቀነስባቸው መሆኑን በመግለፅ ምላሽ ቢሰጥም የተጠቀሰው አዋጅ ዲፕሎማቶችን እንጂ የኮንትራት ሠራተኞችን የማይገልፅ በመሆኑ፤ እንዲያውም በተጠቀሰው አዋጅ ክፍል 6 ቁጥር 38 ላይ ለውጭ ግንኙነት አገልግሎት ከሚከፈል ደመወዝ ላይ ግብር የሚከፈል መሆኑን ይገልጻል፡፡ በመሆኑም ምላሹ ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለሆነም ከሁሉም የኢምባሲ ኮንትራት ሰራተኞች ደመወዝ ላይ በደንብና በመመሪያው መሰረት መቀነስ ሲገባው ያልተቀነሰውን የስራ ግብር እንዲመለስ /እንዲሰበሰብ/ በማድረግ ለገቢ ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት ገቢ ሊያደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም በገቢ ግብር አዋጁ መሰረት ሊፈጸም ይገባል፡፡

2. የወጪ ሂሳብ፤

2.1 ግኝት፤በግልጽ ጨረታ መፈፀም ሲገባው በቀጥታ ለተከናወነ ግዥ የተከፈለ ብር 12,932,641.65፤

ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣዉ የእቃና የአገልግሎት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 24/3 መሰረት እንዲሁም ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ሕ/አ/2/59 ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣዉን የእቃና የአገልግሎት ግዥ አንዳንድ አንቀጾችን ለማሻሻል በወጣው መመሪያ መሰረት ከብር 150,000.00 በላይ የሆኑ የአገልግሎት ግዥዎች እና ከብር 200,000.00 በላይ ለዕቃ ግዥ በግልጽ ጨረታ መገዛት እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በተጨማሪ የፌዴራል መንግሥት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 51 ንኡስ አንቀጽ 1/ሀ የመንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም የሚችሉት እቃው ወይም አገልግሎቱ የሚገኘው ከአንድ እጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ ይገልጻል፡፡

እንዲሁም በሚሲዮኖች ያለውን የግዥና ፋይናንስ አስስተዳደር ለመመራት በ3/12/2010 በጸደቀው መመሪያ ክፍል 2 አንቀጽ 16 ንኡስ አንቀጽ 2 በአንድ ጊዜ የሚፈጸመዉ የግዥ መጠን ከ500 የአሜሪካ ዶላር በላይ በሚሆንበት ጊዜ እና ግዥውን ዋጋ በማሰባሰብ ማወዳደር የማይቻልበት ሁኔታ ሲያጋጥም የግዥ ኮሚቴ በሚያቀርበዉ የዉሳኔ ሃሳብ የያዘ ቃለ-ጉባኤ

መሰረት በሚሲዮኑ መሪ ጸድቆ ተግባራዊ ይደረጋል ይላል። በዚሁ መሰረት በዋና መ/ቤትና በኤምባሲዎች የተከናወኑ የተለያዩ ግዥዎች በመመሪያ መሰረት የሚፈፀሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በዋናው መ/ቤት በቀጥታ ግዥ ዘዴ **በድምሩ በብር** 8,767,053.55፤
- በኒውዮርክ ሚሲዮን **በድምሩ ብር** 1,249,178.21 (35,118.87 **ዶላር**)፤
- በፕሪቶሪያ ኤምባሲ **በድምሩ ብር** 1,870,521.61 (946,142.61 **ራንድ**)፤
- በለንደን ኤምባሲ **በድምሩ ብር በድምሩ ብር** 102,256,227.66 (2,874,788.52 **ፓውንድ**)
- በናይሮቢ ኤምባሲ **በድምሩ ብር** 911,262.05 (2,688,088.72 **ሽልንግ**) ፤

በድምሩ ብር 12,932,641.65 ከመመሪያ ውጪ በቀጥታ ግዢ ለተፈፀ መበትተከፍሎ ተገኝቷል።

ስጋት፤

- ማንኛውም ግዥ በመመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ጥቅም ማስገኙቱን ማረጋገጥ አይቻልም።
- የግዥ አዋጁን እና መመሪያውን ተከትሎ ግዥዎችን ያለመፈጸም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል።

የማሻሻያ ሃሳብ፤

መ/ቤቱ በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ግዥዎች ሊፈፀሙ ይገባል። በተጨማሪም ከሚሲዩኖች ግዥ ጋር በተያያዘ የአገልግሎት ግዥ ወይም በውል የሚፈጸም ስራ እንደ እቃ ግዥ መመሪያው በሚፈቅደው የግዢ ዘዴ እንዲገዛ መደረግ ይኖርበታል።

የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

- በቀጥታ የተገዙትን በተመለከተ በግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 51 ንኡስ 1ሀ፣ለ፣ረ መሰረት በተደነገገው መሰረት በበላይ ሃላፊዎች ተፍቅዶ ግዥው የተፈጸመ መሆኑ፣በአንዳንዱ አቅርቦትን የሚሰጠው ብቸኛ የመንግስት ተቋም በመሆኑ፣ለረጅም አመታት እየሰራ ያለ ድርጀት መሆኑ እንዲታወቅና ለዚህም ከድርጅቱ ጋር ውል የተገባ በመሆኑ፣ የዋጋ ማወዳደሪያ ቀርቦና በቃለ-ጉባኤ ፀድቆ አገልግሎት እየተሰጠ በመሆኑ፣ከተለያየ ቦታ በተለያየ አድራሻና በተለያየ ደረሰኝ የተፈፀመ መሆኑ ገልፆ ነገር ግን ከተፈቀደው ጣሪያ በማለፉ የተፈጠረ በመሆኑ በቀጣይ ጥንቃቄ የሚወሰድ መሆኑን ፣

- የሚሲዮን ፋይናንስ በተመለከተ በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎችና ቀናቶች ለተፈፀመ የእቃና የአገልግሎት ግዝ በኒውዮርክ ሚሲዮን 1,249,178.21፣ በፕሪቶሪያ ሚሲዮን 1,870.521.61 በለንደን ሚሲዮን 134,626.23 በናይሮቢ ሚሲዮን 911,262.05 በድምሩ 4,165,588.10 ከመመሪያ ውጪ በቀጥታ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል ለሚለው በኦዲት ወቅት ከተሰጠው ምላሽ በተጨማሪ
- **በኒውዮርክ** ሚሲዮን በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 54874፣ 54893፣ 54908፣ 54915፣ 54940፣ 55302፣ 54988፤ 54980፣ 55339፣ 54865፣55303 ብር 761,890.55 በሚሲዮኑ ጽ/ቤትና መኖሪያ ቤት ከህንፃ ላይ የተገጠመው ኤሴ ከህንፃው ጋር የተገጠመ መሆኑ እና የገጠመው ኩባንያ በየወሩ ሰርቪስና ጥገና የሚያከናውን መሆኑን እንዲሁም በየሦስት ወሩ ክፍያ የሚከፈለው በመሆኑ ዋጋ ማወዳደሪያ የማይቀርብበት መሆኑን፤ የሣርና የአትክልት እንክብካቤ እና የፅዳት አገልግሎት ወርሃዊ የጉልበት ስራ ክፍያ በመሆኑ የዋጋ ማወዳደሪያ ያልቀረበበት መሆኑን፣ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 54864፣54896፣ 208968፣ 692224፣ 54992፣ 692236፣ 692242፣ 208954ብር 399,074.06 በአገሩ አሰራር መሰረት ድርጅቶች የዋጋ ማወዳደሪያ ስለማይሰጡ በጀት አመቱ መጀመሪያ ላይ በቃለ- ጉባኤ የግዥ ፍላጎት በማሳወቅ የተፈፀመ ግዥ መሆኑን እየገለፅን የግዥ ፍላጎት ማሳወቂያ ቃለ ጉባኤውን አባሪ አድርገን ያቀረብን በመሆኑን በድጋሚ ቢታይልን፤
- **ፕሪቶሪያ** በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 97386፣ 97429፣ 97566፣97415፣ 97722፣ 47149፣98016ብር 1,870,521.61 Red Alert ከሚባል ድርጅት ጋር ቀደም ሲል ባለን የስራ ውል መሰረት የተከፈለ የጥበቃ አገልግሎት ክፍያ ሲሆን ውሉን አባሪ ያደረገን መሆኑን እንገለፅን በድጋሚ እንዲታልን እንጠይቃለን፤
- **ኬንያ /ናይሮቢ** በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 47216፣ 47149፣, 47295፣ 47320፣ 47428፣47417፣47568 ብር 667,508.18 G4S ከሚባል ድርጅት ጋር ቀደም ሲል ባለን የስራ ውል መሰረት የተከፈለ የጥበቃ አገልግሎት ክፍያ ሲሆን ውሉን አባሪ ያደረገን መሆኑን እንገለፅን በድጋሚ እንዲታልን እንጠይቃለን፣በምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 99612፣30922፣30932፣30936፣99627 ብር 182,794.90 ለሚሲዮኑ አገልግሎት የሚውሉ ግዢዎች መሆናቸው፣ በክቡር አምባሳደር የፀደቀ ግዥ መሆኑ እንዲሁም ሞዴል 19 የተቆረጠላቸው መሆኑን ከግምት እንዲገባልን እንዲሁም በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 47138፣47136 ብር 60,958.98 በቀጣይ ትምህርት የምንወስድበት መሆኑን እንገልፃለን፡

➢ **ለንደን** በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 37178 ብር 134,626.23 ሚሲዮኑ ግዥውን ሲፈፅም ቃለ ጉባኤ ይዞ መሆኑን እየገለፅን ለዚህም ቃለ-ጉባዔ አባሪ ያደረግን ሲሆን በወጪ ማስመስከሪያቁጥር 37130፣ 37131፣37132፣37206፣ 37207፣37208 ብር 101,418,604.61 ሚሲዮኑ ዋና መ/ቤቱ በለንደን አገር እና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በተለያየ አገራት ከሚገኘው ኢንሹራንስ ኩባንያ የጤና መድህን ኢንሹራንስ ለመግባት የተፈጸመ ክፍያ ሲሆን ለዚህም ቃለ-ጉባኤ አባሪ የተደረገ በመሆኑ ግኝቱ እንዲወጣልን እንጠይቃለን፡፡

<u>የኦዲተር አስተያየት፤</u>

ሥራ አመራሩ በሰጠው ምላሽ በቀጥታ የተገዙትን በተመለከተ በግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 51 ንኡስ 1ሀ፣ለ፣ረ መሰረት በተደነገገው መሰረት በበላይ ሃላፊዎች ተፍቅዶ ግዥው የተፈጸመ መሆኑ፣ በአያንዳንዱ አቅርቦት የሚሰጠው ብቸኛ የመንግስት ተቋም በመሆኑ፣ የሚል ሲሆን በተጠቀሰው አዋጅ እቃ /አገለግሎት/ /ግንባታ/ የሚገኘው ከአንድ አቅራቢ /እጩ ተወዳዳሪ ብቻ መሆኑ ሲታወቅና ማወዳደር የማይቻል መሆኑ እና ብቸኛ አቅራቢ ለመሆኑ ሲረጋገጥ፤ በመሆኑ ይህ የተረጋገጠበት ማስረጃ አልቀረበም፡፡

የሚሲዮን ፋይናንስን በተመለከተ

ኒውዮርክ ዋጋ ማወዳደሪያ ድርጅቶች በአገሩ አሰራር መሰረት የማይሰጡ ስለሆነ በማለት ምላሽ ቢቀርብም የማይሰጡ ከሆነ በግዥ መመሪያው ላይ እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም በምን መልኩ ግዥ ሊፈጸም እንደሚገባ የተቀመጠ በመሆኑ በመመሪያው መሰረት ተፈጻሚ ሊደረግ ይገባል፡፡

ፕሪቶሪያ ቀደም የአገልግሎት ግዥው ከመመሪያ ውጭ የተፈፀመበት ምክንያት ሊገለፅ ወይም ማስረጃ ማቅረብ ሲገባ በነበረ ውል መሠረት የተከፈለ ነው የሚለው ምላሽ ከቀረበው ግኝት ጋር አግባብነት የለውም፡፡

ኬኒያ ቀደም ሲል መመሪያን ያልተከተለ ግዥ መፈፀሙን በተመለከተ ለቀረበ ግኝት በነበረን የስራ ውል መሰረት የተከፈለ ነው በሚል የተሰጠው ምላሽ ከግኝቱ ጋር አይዛመድም በመሆኑም ግዥው በቀጥታ ግዥ መፈጸሙ አግባብ ባለመሆኑ መመሪያውን ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል ፡፡ በአምባሳደር የጸደቀ በመሆኑ ማስረጃ ቀርቧል ቢባልም የተባለው ማስረጃ ለኦዲቱ አልቀረበም፡፡

2.2 ግኝት፤ በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ ወጪዎች በድምሩ ብር 19,950,422.38፤

የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም. በክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ተራ ቁጥር 4 ላይ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣውን ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይቶ በተሰጠ የበጀት መለያ መደብ ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው ይገልጻል:: ይሁን እንጂ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጪ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤

- በዋናው መ/ቤት በድምሩ ብር 17,176,806.43፤
- በኒውዮርክ ኤምባሲ በድምሩ ብር 1,228,851.78 (34,547.42 ዶላር)
- በመስኮት ኦማን ኤምባሲ በድምሩ ብር 58,199.42 (ሪያድ 636.30)
- በለንደን ሚሲዮን በድምሩ ብር 767,367.25 (16,271.57 ፓውንድ)
- የናይሮቢ ኤምባሲ በድምሩ ብር 719,197.50 (1,400,957.74 ሽልንግ)

በጠቅላላ በድምሩ ብር 19,950,422.38 የሂሳብ አርዕስታቸውን ሳይጠብቁ ወጪ የተደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ታውቋል።

ስጋት፤

- ወጪዎች በተገቢው የወጪ ሂሳብ መደብ ተመዝግበው ሪፖርት የማይደረግ ከሆነ የሚኒስቴሩ የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታ እንዳያሳይ ሊያደርገው ይችላል።
- የተመደበው በጀት በአግባቡ በሥራ ላይ ላይውል ይችላል።

የማሻሻያ ሀሳብ፤

ወጪዎች በመመሪያው መሰረት እንዲመዘገቡ መደረግ ይኖርበታል።

የሥራ አመራሩ ምላሽ

በተገቢ የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ ወጪዎች ዝርዝርን በተመለከተ

- በተራ ቁጥር 1 እና 2 የተገለጹት ለ5ተኛ ዙር ሰልጣኝ ዲፕሎማቶች ለመኝታ| ለምግብ እና ለህክምና አገልግሎት በተገባዉ ዉል መሰረት በሂሳብ መደብ ቁጥር 6233 በጀት ተይዞለት ብር 8,932,606.73 ክፍያ እንዲፈፀም የተደረገ ነው። ይህም ክፍያ ከ1ኛ ዙር ጀምሮ እስከ 5ተኛ ዙር ድረስ ለዚሁ አገልግሎት ክፍያ የሚውል በጀት ከገንዘብ ሚኒስቴር በመጠየቅና በወጪ ሂሳብ መደብ ቁጥር 6233 /በመስተንግዶ ክፍያ/ እየተፈፀም ይገኛል። በመሆኑም

መ/ቤታችን ከአገልግሎት ሰጪው ጋር በገባው ውል መሠረት የተከፈለ ክፍያ ሲሆን ይህም ለሰልጣኞች ለስልጠና የተከፈለ ክፍያ ሳይሆን በስልጠና ቆይታቸዉ ወቅት ለምግብ ለአልጋና ለመሳሰሉት ክፍያዎች በተፈቀደው በጀት መሠረት የተፈፀመ ክፍያ መሆኑን እየገለጽን የቀረበዉ ግኝት በድጋሜ ታይቶ ከግኝት እንዲወጣ እንጠይቃለን፡፡

- በተራ ቁጥር 8 የተገለጸዉ ለጅቡቲ አምባሰደር በስጦታ የተገዛዉ ጌጣጌጥ በተመለከተ በወጪ ሂሳብ መደብ 6417 መያዝ ነበረበት ለሚለዉ ግኝት በበጀት አመቱ በወጪ ሂሳብ መደቡ በጀት ያልተያዘ ሲሆን ባለን በጀት መሰረት ከዚህም ቀደም ለተለያዩ ስጦታዎች ግዥ በምንጠቀመዉ መሠረት በወጪ ሂሳብ መደብ 6233 የተመዘገበ በመሆኑ ይህም የሚሰጡ የተለያዩ ስጦታዎችን የሚካትት በመሆኑ ግኝቱ በድጋሚ እንዲታይና ከግኝት እንዲወጣ እንጠይቃለን፡፡

በተራ ቁጥር 11፣ 12 እና 19 ለጽዳት አገለግሎት የተከፈለ ክፍያ በተመለከተ ምንም እንኳን ዉል የሚገባ ቢሆንም ስራዉ የአገልግሎት ስራ በመሆኑና የሚሰጠው

- አገልግሎት የፕሮፌሽናል አገልግሎት ባለመሆኑ ክፍያው በሂሳብ መደብ 6256 በጀት ተይዞለት በዚሁ መሠረት ክፍያ እየተፈፀመ ያለ ሲሆን፣ በወጪ ሂሳብ መደብ 6251 ስር የሚካተቱት Professional service (የሙያ አገልግሎት) የሆኑ የምክር አገልግሎት፣ የጥናት የሕክምና ምርምር፣ በመንግስት መ/ቤቶች የሚከናወን የካርታ እና የቅየሳ ስራ እንዲሁም የምህንድስና ምክር (የማማከር) አገልግሎት መሆናቸውን እየገለጽን፣ የተከፈለው ክፍያ ለመ/ቤታችን ለተሰጠ የጽዳት አገለግሎት በመሆኑና መደበኛ የሆነና ፕሮፎሽናል ያልሆነ አገልግሎት በመሆኑ 6256 የተያዘ መሆኑ ታውቆ ግኝቱ በድጋሚ እንዲታይና ከግኝት እንዲወጣ እንጠይቃለን፡፡
- በተገቢዉ የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ ወጪዎች ተብለው የቀረቡ ሌሎች 12 ግኝቶችን በተመለከተ፣ በበጀት ዓመቱ ሚኒስትር መ/ቤታችን ከሚሰበሰበዉ የዉስጥ ገቢ እንደ በጀት (6412) እንድንጠቀም ከገንዘብ ሚኒስቴር ከተፈቀደልን በጀት ላይ በተፈቀደው በጀት አርዕስት 6412 መሠረት ወጪ የተደረገ መሆኑን እየገለፅን፤ይህም ከውስጥ ገቢ እንደ በጀት እንድንጠቀም ከተፈቀደው ላይ በበላይ አመራር ተፈቀዶ ወጪ የተደረገ በመሆኑ ግኝቱ በድጋሚ ታይቶ ከግኝት እንዲወጣ እንጠይቃለን፡፡

በኒዮርክ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 55052 ብር 5,371.07 ክፍያ ሲፈፀም በሚሲዮኑ የተሰጠው አገልግሎት በመሆኑ በ6256 የተመዘገበ ሲሆን በተጠቀሰው የሂሳብ ኮድ

(6255/6252) ለመመዝገብ ቀደም ሲል በጀት ባለመያዙ ምክንያት የተመዘገበ መሆኑ እንዲታወቅ እየጠየቅን በቀጣይ በተገለጸው የሂሳብ ኮድ በቂ በጀት በማስያዝ በተሰጠው አስተያየት መሰረት የምንሰራ መሆኑን፣በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 54864፣ 54865፣ 54893፣ 54908፣ 55303፣54856 ብር 455,295.29 ሚሲየኑ በተጠቀሰው ኮድ 6251 ቀደም ሲል በጀት ባለመያዙ ምክንያት ድርጅቱ የሰጠው አገልግሎት በመሆኑ በ6256 የተመዘገበ መሆኑ እንዲታወቅ እየጠየቅን በቀጣይ በተጠቀሰው የሂሳብ ኮድ በቂ በጀት በማስያዝ የምንሰራ መሆኑን፣በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 54874፣ 54915፣ 55302፣ 54980 ብር 320,936.37 የሙያ አገልግሎት የተሰጠበት ሳይሆን የግቢ ጽዳጽ፣ የሳርና አትክልት ማስተካከል ስራ የጉልበት አአገልግሎት ክፍያ በመሆኑ የሂሳብ ኮድ 6256 የተመዘገበ በመሆኑ ግኝቱ በድጋሚ ቢታይልን፣በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 55070፣ 54925 ብር 49,264.45 ሚሲየኑ በተጠቀሰው ኮድ 6255 ቀደም ሲል በጀት ባለመያዙ ምክንያት ለአንድ ጊዜ የገጠመ ወጪ በመሆኑ ለሰጠው አገልግሎት በ6256 የተመዘገበ መሆኑ እንዲታወቅ እየጠየቅን በቀጣይ በተጠቀሰው የሂሳብ ኮድ በቂ በጀት በማስያዝ የምንሰራ መሆኑን፣በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 55068፣55346፣692246 ብር 134,766.60 አስተያየቱን ተቀብለናል በተገለጸው የሂሳብ ኮድ መሰረት የምንሰራ መሆኑን፣ የኒውዮርክ ኢምባሲ ለእቃና ለአገልግሎት ግዥዎች ቅድመ ክፍያ ብር 263,218.00 ሲከፍል ምዝገባውን በትክክለኛው የሂሳብ መደብ በ4211 የሂሳብ መደብ መመዝገብ ሲገባው በሂሳብ መደብ 4203 የተመዘገ መሆኑ ታይቷል። ሆኖም ግን ሒሳቡ በወቅቱ የተወራረደ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ማስረጃ ያቀረብን በመሆኑ በድጋሚ ቢያይልን፤ **ለንደን** በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 37110፣ 37070፣ 37079፣ 37084፣ 37047፣ 37055፣ 35983 ብር 727,995.25 ሚሲዮኑ በወጪ ያልመዘገበበት ምክንያት ወጪው በሚሲዮኑ ውስጥ ያሉ የሶስተኛ ወገን የኢሚግሬሽን /የብሔራዊ መረጃና ደህንንነት ቢሮ ሰራተኞች ክፍያ የሚውል በመሆኑና የዋና መ/ቤት በጀት አለመሆኑ እነዲሁም ለሶስተኛ ወገን ለብቻ በወጪ መዝግቦ ለሚመለከተው ባለድርሻ መ/ቤት ሪፓርት የሚያደርግ በመሆኑ ምክንያት ሲሆን ለዚህም ቀደም ሲል ገቢው ሲገባ በተከፋይ ተመዝግቦ የነበረ ስለመሆኑ ማስረጃ የቀረበ በመሆኑን ግኝቱ በድጋሚ እንዲታይልን፤በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 37112 ብር 1,091.75 ቀጥታ የፖስታ አገልግሎት ስለሆነ የሂሰብ ኮዱ በ6259 የመዘገበ መሆኑን እየገለፅን ከግኝት እንዲወጣልን እንጠይቃለን።በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 37063፣ ብር 23,073.03 ሚሲየኑ በተጠቀሰው ኮድ 6244 ቀደም ሲል በጀት ባለመያዙ ምክንያት ድርጅቱ የሰጠው አገልግሎት በመሆኑ በ6256 የተመዘገበ መሆኑ እንዲታወቅ እየጠየቅን በቀጣይ በተጠቀሰው የሂሳብ ኮድ በቂ በጀት በማስያዝ

የምንሰራ መሆኑን እንዲሁም በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 37016፣ 35963፣ 35965 ብር 15,207.22 የተሰጠውን አስተያየት ተቀብለናል በተገለጸው የሂሳብ ኮድ መሰረት የምንሰራ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ሙስካት/ኦማን በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 232974 ብር 1,852.60 ወጪው በጀት ተተክሎለት በቋሚነት/ በኮንትራት/በውል የተፈፀመ የአገልግሎት ክፍያ ሳይሆን ለአንድ ጊዜ የተከፈለ የጉልበት ዋጋ ክፍያ በመሆኑ በድጋሚ እንዲታይል እንጠይቃለን፡፡በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 232976፣ 233053፣ 233119፣ 233092 ብር 47,546.97 የተሰጠውን አስተያየት ተቀብለናል በተገለጸው የሂሳብ ኮድ መሰረት የምንሰራ መሆኑን፣ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 233006፣ 27417፣ 232806፣ 233019፣ 232942 ብር 8,799.85 ለአገልግሎት የተከፈለ ክፍያ በመሆኑ ምክንያ በ6256 የተመዘገበ መሆኑን :

ናይሮቢ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 30900፣ 47118፣47117፣47311 ብር 15,255.00 ለጉልበት ዋጋ የተከፈለ ክፍያ በመሆኑ ምክንያ በ6256 የተመዘገበ በመሆኑን በመሆኑ በድጋሚ ቢታይልን፤ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 47297፣ 47298፣ 47259፣ 47412፣ 47404 ብር 293,143.03 ወጪው ቀደም ሲል በጀት ያልተያዘለት በመሆኑ እና ለአንድ ጊዜ የተከፈለ ክፍያ በመሆኑ ከግምት በማስገባት በድጋሚ እንዲታይልን፤ (በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 47297 ሁለት ጊዜ የተመዘገበ በመሆኑን እንዱን ብቻ ቢያዝ)፣ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 47206፣ 47267፣ 47349፣ ብር 124,962.18 በፖስታ ቤት የተላከ በመሆኑ በሂሰብ ኮድ 6259 የተመዘገበ በመሆኑ በድጋሚ ቢታይልን፤ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 47107 ብር 6,640.33 ለጽዳት እቃና ለፓስታ መለኪያ ስለሆነ በ6218እና በ6259 የተያዘ በመሆኑ እንዲታይልን፣በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 99627 ብር 39,832.50 ወጪው ለህተመት የተከፈለ በመሆኑ በድጋሚ እንዲታይልን፣ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 99627 ብር 3,864.60 ወጪው ገመድ የተገዛበት እንጂ የስልክ ወይም የኢንተርኔታ አገልግሎት አለመሆኑ ከግምት እንዲያዝና በድጋሚ እንዲታይልን፣በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 47261፣47345 ብር 6,780.00 ሚሲዮኖች የኢንሹራንሽ ሽፋን ስላላቸው በተጠቀሰው የሒሳብ ኮድ 6214 በጀት ስለማይያዝ እና የምርመራ አገልግሎቱ ወቅታዊ የወረርሽኝ በሽታ በመሆኑ በ6256 የተያዘ መሆኑ እንዲታወቅልን፣(በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 47261 ሁለት ጊዜ የተመዘገበ በመሆኑን እንዱን ብቻ ይዘናል) በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 47210፣ 47299፣ 47243፣ 99627፣ 99626፣ 47345፣ 30924፣ 47261፣ 47095፣ 99636 ብር 103,557.04 በተሰጠን አስተያየት መሰረት በተጠቀሰው የሂሳብ ኮድ መሰረት የምንሰራ መሆኑን፣ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር

47349፣47238፣47138 ብር 199,513.96 ሚሲየኑ በተጠቀሰው ኮድ 6255 ቀደም ሲል በጀት ባለመያዙ ምክንያትና ድርጀቱ የሰጠው አገልግሎት በመሆኑ በ6256 የተመዘገበ መሆኑ እንዲታወቅ እየጠየቅን በቀጣይ በተጠቀሰው የሂሳብ ኮድ በቂ በጀት በማስያዝ የምንሰራ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

<u>የኦዲተር አስተያየት፤</u>

የበጀት እጥረት ቢያጋጥም እንኳን የበጀት ዝውውር በመጠየቅ ክፍያው መፈፀም ሲገባው በሥራ አመራ ምላሹ በጀት ስለማይያዝ እና የምርመራ አገልግሎቱ ወቅታዊ የወረርሽኝ በሽታ በመሆኑ ምክንያትና ድርጀቱ የሰጠው አገልግሎት በመሆኑ ነው በሚል የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለሆነም በተገቢ ሂሳብ መደብ ምዝገባ ለመከናወኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

2.3 <u>ግኝት፤ የገበያ ጥናት ሳይደረግ ለተፈፀመ የእቃ ግዥ የተከፈለ ብር 1,043,052.47፤</u>

ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመርያ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 24.8 መ/ቤቱ በዋጋ ማቅረብያ በተደጋጋሚ ለሚፈጽማቸው ግዥዎች ከስታስቲክስ ኤጀንሲው ድረ-ገጽ የሚወጣውን ወቅታዊ የዋጋ ዝርዝር እና በግዥ ስራ ክፍሉ የሚካሂድ የገበያ ጥናት በመጠቀም ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ ዋጋ መሆኑን ማመን ይኖርበታል ይላል፡፡ ይሁን እንጂ

መ/ቤቱ በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያ ቫውቸሮችና በተለያዮ ቀናት በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ የተለያዩ እቃዎችና አገልግሎቶችን ግዥ ሲፈጽም መመሪያው በሚያዘው መሰረት በተወዳዳሪዎቹ/በአቅራቢዎቹ የሚያቀርቡት ዋጋ ያልተጋነነና ትክክለኛነት ስለመሆኑ ከስታስቲክስ ኤጂንሲ ወይም በግዥ የስራ ክፍል በሚደረግ የገበያ ጥናት መሰረት እየተረጋገጠ ግዥውን መፈጸም ሲገባ መመሪያውን በመተለላፍ ከኤጀንሲው ድረ-ገጽ የሚወጣውን ወቅታዊ የዋጋ ዝርዝር ሳይወሰድና ምንም አይነት የገበያ ጥናት ሳይደረግ በድምሩ **በብር 1,043,052.47** በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት፤</u>

መመሪያን ያልተከተለ ግዥ በመፈፀሙ መ/ቤቱ ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

መ/ቤቱ በግዥ መመሪያ መሠረት ግዥ ማከናወኑ ተገቢው ከትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

- መ/ቤታችን በየአመቱ የገቢያ ጥናት Price Consumer index ዳሰሳ ጥናት በማድረግ የዓመቱን በጀትና የግዥ ፍላጎት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በማቅረብ ግዥዎች የሚፈፀሙ ሲሆን፣በዋጋ ማቅረቢያ የሚገዙት ቁሳቁሶች በባህሪያቸው በብዛት የማይገኙ፣ የሚፈለጉት በቁጥርና በአይነት ትናንሽና የተለያዩ ከሞናቸው ጋር በተያያዘ የገቢያ ጥናት ሰነድ ለማዘጋጀት ምቹ ያልሆኑና በዕቅድ ለመያዝ የማይቻሉና ለደራሽና ተጨማሪ ስራዎች የሚያስፈልጉ በመሆናቸው ካለው የግዥ ዘዴ ውስጥ በዋጋ ማቅረቢያ ዘዴ የተገዙ መሆናቸው ታውቆ ግኝቱ እንዲወጣልን እንጠይቃለን፡፡
- የተጠቀሰው ግኝት በግዥ አፈፃፀም መመሪያው መሰረት የፐሪፎርማ ግዥ አሰራር በፍጥነት የሚፈፀም እና አስቸኳይ የሚከናወን መሆኑ እና በተቻለ አቅም በቂ አቅራቢዎች ለማፈላለግ ጊዜ ስለሚወስድ እንዲሁም በተጨማሪ በሥራ ክፍሉ የተዘጋጀ የገቢያ ጥናት ያለ ቢሆንም በአባሪ -2 ከተራ ቁጥር 1-5 የቀረቡ ግዥዎችን በወቅቱ ገቢያ መሆኑን ለማረጋገጥ በዘርፉ የተሰማሩ በቂ አቅራቢዎች ያለመኖር እንዲሁም የገቢያ ጥናት ለመስጠት ፍቃደኛ ድርጅቶች ለማግኘት ባለመቻሉና በመቸገራችን በመ/ቤታችን ስራ ላይ ከፍተኛ ጫና ብሎም ችግር ስለሚፈጥር በዚሁ አግባብ የተከናወነ ግዥ መሆኑ ተወስዶ ከግኝት እንዲወጣ እየጠየቅን ያለገበያ ጥናት ለተፈጸመ የዕቃ ግዥ ለሚለዉ ግኝት መ/ቤታችን በየአመቱ የገበያ ጥናት Price Consumer Index ዳሰሳ ጥናት በማድረግ የዓመቱን በጀትና የግዢ ፍላጎት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው የግዢና ንብረቶች አስተዳደር ኤጀንሲ በማቅርብ ግዢዎች የፊጸሙ ሲሆን፤ በዋጋ ማቅረቢያ የሚገዙት ቁሳቁሶች በባህሪያቸው በብዛት የማይገኙ፤ የሚፈለጉት በቁጥርና በአይነት ትናንሽ የተለያዩ ከመሆናቸው ጋር በተያያዘ የገበያ ጥናት ሰነድ ለማዘጋጀት ምቹ ያልሆኑና በእቅድ ለመያዝ የማይቻሉና ለደራሽና ተጨማሪ ስራዎች የሚያስፈልጉ በመሆናቸው ካለው የግዢ ዘዴ ውስጥ በዋጋ ማቅርቢያ ዘዴ የተገዙ መሆናቸው፤ ታውቆ ግኝቱ እንደገና ቢታይ እያልን የገበያ ጥናት ዳሰሳ ሰነድ አደራጅተን አቅርበናል፡፡

<u>የኦዲተር አስተያየት፤</u>

- አመታዊ አቅድ ሲዘጋጅ የገበያ ጥናት ተደርጎ ነው በሚል ምላሽ ቢሰጥም እቃው/አገልግሎቱ ሲገዛ በእቅድ ዝግጅት ወቅት የተጠና የገበያ ጥናት/ካለ/ አሁን ያለውን ዋጋ የሚያሳይ ባለመሆኑ ምላሹ ወቅታዊና አሁናዊ መረጃን የሚሰጥ ባለሞኑ ተቀባይነት የለውም፡፡
- በፕሮፎረማ የሚገዙ ግዥዎች በብዛት የማይገኙ እና ብዛታቸው ትንንሽ ስለሆኑ የገበያ ጥናት ለማድረግ ምቹ አይደሉም ለሚለው የመንግስትን መመሪያ የሚጣረስና በግኝቱ የተጠቀሱት ንብረቶችም በብዙ አቅራቢዎች የሚገኙ በመሆናቸው ምላሹ አግባብነት የለውም፡፡
- ንብረቶቹ /አገልግሎቶቹ በእቅድ ለመያዝ የማይችሉና ለደራሽና ተጨማሪ ስራዎች የሚፈለጉ ናቸው በሚል የተመለሰው ምላሽ በግኝቱ የተነሱትን ንበረቶች እንደ አብነት ብንጠቅስ ለምሳሌ ተሽከርካሪ ወንበር፤ ዩፒኤሶች፣ የጥገና አገልግሎት ለተገኘበት፣ የፕሪንተር ቶነሮች፤ የሴቶች ሽሚዝ፤የቢሮ ስቲከር፤ እና እንጨጥ ቁምሳጥንና የግድግዳ ስቲከር በእቅድ ሊያዙ የሚችሉና በብዛት ሊገኙ የሚችሉ እና ደራሽ ግዥዎች አለመሆናቸውን ማሳያ ናቸው፡፡ በመሆኑም ምላሹ ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም በዋጋ ማወዳደሪያ የግዥ ዘዴ የሚፈጸሙ ግዥዎች ከኤጀንሲው ድረ-ገጽ እንዲሁም በግዥ ክፍል በሚደረግ የገበያ ጥናት ትክክለኛ ዋጋ እንዲቀርብ በማድረግ በመመሪያው መሰረት እንዲፈፀሙ ሊደረግ ይገባል፡፡

2.4 ግኝት፤ ባልተሟላ የውል ስምምነት የተከፈለ ብር 2,528,159.03፤

ሰኔ 2002 በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 16.27 ውልን በተመለከተ ንዑስ አንቀጽ 16.27.1 ማናቸውም የመንግስት መ/ቤት የመደበኛ ጨረታ ሠነዶች አንድ ክፍል የሆነውን አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች እና ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን ልዩ የውል ሁኔታዎች የያዘውን የውል ሠነድ ከአቅራቢው ጋር መፈራረም እንዳለበት፡፡ ንዑስ አንቀጽ 16.27.3(ሀ) በውሉ የሚቀርበው እቃ የአከፋፈል ሁኔታና የክፍያ ዘዴውን፤ ንዑስ አንቀጽ 16.27.3(መ) ለውል አፈጻጸም የተያዘው የውል ማስረከቢያ ሊወረስ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች፤ እንዲሁም ንዑስ አንቀጽ 16.27.3(ሸ) አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፤ አጠናቆ ባያስረክብ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደውን እርምጃ በወል ላይ ማመላከት እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ

- መ/ቤቱ ከሚልፎርድ ትሬዲንግ ሁለት 5ዲ ማርክ ካሜራ ለመግዛት በተያዘው/በተገባው የውል ስምምንት ላይ የአከፋፈል ሁኔታና የክፋያ ዘዴውን፤ ለውል አፈጻጸም የተያዘው

የውል ማስረከቢያ ሊወረስ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች እንዲሁም አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን አጠናቆ ባያስረክብ ሳዘገየበት ጊዜ የሚወሰደውን እርምጃ መካተት ሲገባው በመመሪያው የተገለፁት ሁኔታዎች ሳይካተቱ ውል ተፈፅሞ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 22538 በቀን 30/8/2013 ዓ.ም በሂሳብ መደብ 2311101 ብር **466,600.00** የተከፈለ መሆኑ፤

- መ/ቤቱ ከቢናዚር የኮንስትራክሽን እና የኤሌክትሮኒክስ አጠቃላይ ጅምላ ንግድ ጋር የተለያዩ የኮንስትራክሽን እና የኤሌክትሮኒክስ ለመግዛት በገባው የውል ስምምንት ላይ መገለፅ የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች በመመሪያው መሰረት ሳይካተቱ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 23287 በቀን 24/10/2013 በሂሳብ መደብ 2631101 ብር **140,879.75** የተከፈለ መሆኑ፤
- መ/ቤቱ ከሃበሻ የኮምፒዊተር፤ የኤሌክትሪክ፤ የቤትና የቢሮ እቃዎች አስመጪ ጋር Outdoor Led Display ከ3*3 ወደ 3*5 ከፍ ለማድረግ ለተሰራ ስራ በተያዘው የውል ስምምንት ላይ በውሉ ሊካተቱ የሚገባቸው ጉዳዮች ሳይገለፁ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 23374 በቀን 29/10/2013 ዓ.ም በሂሳብ መደብ 2631101 **ብር 811,900.00** የተከፈለ መሆኑ፤
- መ/ቤቱ ከሙሃመድ አሚን የኮንስትራክሽን ማቴሪያሎች ችርቻሮ ንግድ ጋር የኤሌክትሪክና የቧንቧ እቃዎችን ለመግዛት በተገባው የውል ስምምንት ላይ መገለፅ የሚገባቸው ሁኔታዎች ሳይካተቱ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 23180 በቀን 21/10/2013 ዓ.ም በሂሳብ መደብ 2231102 ብር **138,329.92** የተከፈለ መሆኑ፤ እንዲሁም
- መ/ቤቱ ከእልፍነሽ እንዳለ ለማ ድርጅት ጋር የደንብ ልብስ ለመግዛት በተገባው የውል ስምምንት ላይ የሚፈፀሙ ሁኔታዎች ባልተካተተበት ሁኔታ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 22923 በቀን 9/10/2013 ዓ.ም በሂሳብ መደብ 2211101 **ብር 970,449.36** የተከፈለ መሆኑ፤

በአጠቃላይ ድምር ብር 2,528,159.03 መ/ቤቱ ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር ውል በመውሰድ ክፍያ ሲፈጽም በውሉ ላይ መካተት የሚገባቸው ሁኔታዎች የውሉ አካል ሳይደረጉ የተከፈለ ሆኖ ተገኝቷል።

<u>ስጋት፤</u>

- የውል ግዴታዎች ተፈፃሚ አለመደረጋቸው ተጠያቂነት እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል።

- በመንግስት ታምኖበት የሚወጡ መመሪያዎች ተግባራዊ የማይደረጉ ከሆነ ተጠያቂነትም ሊያስከትል ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፤

በመ/ቤቱ የተፈፀሙ ውሎች የተቋሙን ጥቅም ሊያስጠብቁ በሚችሉበት መንገድ መሆናቸውና በግዥ መመሪያው መሰረት የውል ስምምነቶች እንዲፈፀሙ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

በቀረበው ግኝት መሰረት የውል አፈፃፀሙ በአስገዳጅ ሁኔታዎች ተብሎ በሚገመት የሀገር አቀፍና አለም አቀፋዊ ተፅእኖ ምክንያት በተገባው ውል መሰረት መጠናቀቅ ባለመቻሉ መ/ቤቱ ይህንን ከግንዛቤ በመውሰድ የተወሱ ድርጅቶችን በገጠማቸው ከአቅም በላይ ችግር በወቅቱ ከነበረው ችግር አንፃር አቅራቢዎች አቅርቦቱን በተመቻቸ ሁኔታ ማቅረብ የሚችሉበት ደረጃ በላመሆኑ እና አስገዳጅ የሆኑ ውሎች ከተካተቱ አቅራቢዎችን የሚያሸሽ በመሆኑ ለዚህም የመስሪያ ቤቱ ጥቅም እቃው ቢገባ የተሻለ ነው ተብሎ ስለታመነ እና በቀጣይ በሚዘጋጁ ውሎች የተሰጠውን አስተያየት የምናካትት መሆኑን ከግምት በማስገባት ግኝቱ እንዲወጣልን እንጠይቃለን፡፡

የኦዲተር አስተያየት፤

መ/ቤቱ የሚፈፅማቸው ውሎች ተገቢውን አስገዳጅ ሁኔታዎች እንዲኖሯቸው በማድረግ እንዲፈፀሙ መደረጉ መ/ቤቱ አገልግሎቱን ወይም ዕቃውን በተፈለገው ጥራት፤ መጠንና ግዜ እንዲያገኝ የሚያደርገው በመሆኑና በተለያዩ ምክንያቶች አቅራቢው ግዴታውን ባይወጣ ተጠያቂ በማድረግ ጥቅሙን እንዲያስጠብቅ የሚያስችለው በመሆኑ መሰረታዊ የውል ግዴታዎች መገባት ይኖርባቸዋል፡፡በመሆኑም መ/ቤቱ በግዥ መመሪያ መሠረት የግዥ ውልን ማሟለት ሲገባው አስገዳጅ ሁኔታዎች በውሉ የሚካተቱ ከሆነ አቅራቢዎችን የሚያሸሽ በመሆኑ ነው በሚል ምላሽ መስጠቱ ተቀባይነት የለውም፡፡

2.5 ግኝት፤ ለለአግባብ ለስፖንሰርነት የተከፈለ ብር 350,000.00፤

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሃምሌ 2009 ዓ.ም ባወጣው የወጭ ቅነሳ መመሪያ አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 8 የማስታወቅያ ወጪን በተመለከተ፡- ባለበጀት መ/ቤቶች ለህዝብ ጥቅም መተላለፍ ካለባቸው መልዕክቶች በስተቀር ራሳቸውን በብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች ማስተዋወቅ እና ሌሎች ድርጅቶችን ወይም በዓላትን ስፖንሰር ማድረግ አይቻልም፡፡ የመንግስት

በጀትን በድጋፍ ስፖንሰር ማድረግ አይቻልም ይላል፡፡ ይሁን እንጂ መ/ቤቱ ለዋልታ ሚዲያና ኮሚዩኒኬሽን ኮርፖሬት አ/ማ መ/ቤቱ ስፖንሰር ያደረገውን የኢድ አል አድሃ (የአረፋ) በዓልን ላቀረበበት **ብር 350,000.00 ክፍያ ተፈፅሞ** በቀን 12/1/2013 ዓ.ም በኢንቮይስ ቁጥር 20285 በወጪ የተያዘ መሆኑንና የአገልግሎት ግዢው ከዋልታ ሚዲያና ኮሚዩኒኬሽን ኮርፖሬት አ/ማ ከመመሪያ ውጪ በቀጥታ የተከናወነ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስጋት፤

- ማንኛውም ግዥ በመመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ጥቅም ማስገኘቱን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡
- በመንግስት የሚወጡ መመሪያዎች ተግባራዊ የማይደረጉ ከሆነ የመንግስት ሃብት ለብክነትና ለምዝበራ ሊዳረግ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፤

መ/ቤቱ እስከተቻለ ድረስ ማንኛውንም አይነት ግዢ በመመሪያው መሰረት ማከናወን ይኖርበታል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የውጭ ጉዳይ ሚኒስስቴር ከሚያከናውናቸው ተግባራት አንዱ የሀገር ገፅታ ግንባታ ሲሆን በዚህም በሀገር አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ውጤት ተመዝግቧል፡፡ስለሆነም የሀገር ገፅታ ግንባታ የዲፕሎማሲ ስራዎች ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ እና ለሥራው አመቺ በሆነ መልኩ መከናወን ያለበት መሆኑ ታውቆ ለስፖንሰር የተከፈለ ክፍያ ማለትም በዋልታ ሚዲያና ኮሚኒኬሽን የኢድ - አል - አድሃ(አረፋ) በዓል ብር 350,000.00 የተከፈለውን በተመለከተ ፣ የመ/ቤታችን የፐብሊክ ሥራ ዘርፍ በዕቅድ ይዘው የሚሰራቸው ተግባር መካከል በገፅታ ግንባታ ዙሪያ የሚሰራ ሲሆን በሀገራችን የሀይማኖት እኩልነትና አብሮነት እንዲሁም የክብረ በዓሉ አካል በመሆኑ በአገር ውስጥና በውጭው አለም በዶክመንተሪ አዘጋጅቶ ተደራሽ ከማድረግ አንፃር ዋልታ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን መንግስታዊ እንደመሆኑ ዶክመንተሪ አዘጋጅቶ ተደራሽ ከማድረግ አንፃር ዋልታ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን መንግስታዊ እንደመሆኑ ዶክመንተሪና ፊልሞች ከማዘጋጀት አንፃር ከሁሉም የሚዲያ ተቋማት የተሻለ ልምድና አቅም ያለው በአጠቃላይ ከሚሰራቸው ስራዎች መካከል በዋናነት የሚታወቀው በዶክመንተሪና ፊልም ስራ በመሆኑ እንዲሁም የመንግስት ድርጅት በመሆኑ በዚህ ዙሪያ ምንም ክፍተት የሌለው ስለሆነ ከግኝት እንዲወጣልን እንጠይቃለን፡፡

የኦዲተር አስተያየት፤

ዋልታ ሚዲያና ኮሙኒኬሽን መንግስታዊ እንደመሆኑ ዶክመንተሪና ፊልሞች ከማዘጋጀት አንፃር ከሁሉም የሚዲያ ተቋማት የተሻለ ልምድና አቅም ያለው ነው በሚል አገልግሎቱ መገዛቱን በተሰጠው ምላሽ ቢገለፅም የተጠቀሰው ድርጅት መንግስታዊ ሳይሆን ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት በመሆኑ እንደማንኛው ግብር ከፋይ አቅራቢ ሊወዳደር እንደሚገባ በኦዲቱ የመውጫ ውይይት ወቅት ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም የወጣው የወጪ ቅነሳ መመሪያ የመንግስት መ/ቤቶች እስፖንስር ማድረግ እንደማይችሉ የተገለፀ በመሆኑ ግዥው መመሪያን የጣሰ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለወደፊቱም መ/ቤቱ የመንግሥትን መመሪያ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

2.6 <u>ግኝት</u>፤ <u>በገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ የተወራረደ ቅድመ ክፍያ ብር 126,327.92 (3,551.53 ዶላር)</u>፤

የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመርያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 4 ጥሬ ገንዘብ የማይንቀሳቀስባቸው ወይም ጥሬ ገንዘብ ያልሆኑ ማናቸውም የሂሳብ ክንውኖች በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ መሂ/9 መፈጸም አለባቸው ይላል፡፡ እንዲሁም የሂሣብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ1ሀ እና1ለ የገቢ መሰብሰብያ ደረሰኝ አገልግሎቱ ገቢ ለመሰብሰብ ብቻ ስለመሆኑ በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ ይሁን እንጂ

<u>በኒውዮርክ ኢንባሲ</u>

- በቀን 5/02/2013 በውጪ ምንዛሪ የወጪ ማስመስከርያ ቁጥር 54924 በሂሳብ መደብ 4203 ለቁሳቁስ መግዣ በሚል 1,000.00 ዶላር ቅድመ ክፍያ ለተከፈለ ገንዘብ ሂሳቡ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ መሂ/9 መወራርድ ሲገባው ያለአግባብ በውጪ ምንዛሪ የገቢ ደረሰኝ ቁጥር 208968 በቀን 25/02/2013 **997.25 ዶላር (ብር 35,472.18)** የተወራረደ መሆኑ፤
- በ27/11/2012 በውጪ ምንዛሪ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 54870 በሂሳብ መደብ 4203 ለእንግዶችን የመስተንግዶ ቁሳቁስ መግዣ በሚል 1,500.00 ዶላር ቅድመ ክፍያ የተከፈለ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ መሂ/9 መወራረድ ሲገባው ያለአግባብ በውጪ ምንዛሪ የገቢ ደረሰኝ ቁጥር 208956 በቀን 28/11/2012 **1,355.75 ዶላር (ብር 48,224.03)** የተወራረደ መሆኑ፤ እንዲሁም
- በውጪ ምንዛሪ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 54887 በሂሳብ መደብ 4203 ለጤና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን ለመግዛት በሚል 2,000.00 ዶላር ቅድመ ክፍያ ለተከፈለው ያለአግባብ በውጪ

ምንዛሪ የገቢ ደረሰኝ ቁጥር 208954 በቀን ኦገስት 08/12/2012 **1,198.53 ዶላር (ብር 42,631.71)** የተወራረደ መሆኑ፤

በድምሩ ብር 3,551.53 ዶላር በብር ብር 126,327.92 በውጪ ምንዛሪ የገቢ ደረሰኝ ያለአግባብ/ የተወራረደ ስለመሆኑ በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ስጋት፤

- የሂሳብ አያያዝ መመሪያን ይጥሳል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፤

ኤምባሲው የሂሳብ ምዝገባ ክንውን በፌዴራል የመንግስት መ/ቤቶች በሂሳብ አያያዝ መመሪያ ተከትሎ መፈጸሙ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደረግ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

ሥራ አመራሩ ማሻሻያ ሃሳቡን ተቀብሎታል፡፡

2.7 ግኝት፤ በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ብር 725,183.57፤

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 9 ክፍያ ከመፈጸሙ አስቀድሞ ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች የፅሑፍ ማረጋገጫ መቅረብ እንዳለበት እና በተገባው ውል መሠረት የሚከፈል ወጪ ከሆነ አገልግሎት መሰጠቱ መረጋገጥ እንደሚገባው ይገልፃል፡፡ እንዲሁም2002 በወጣው የግዥ መመሪያ አንቀጽ 16.26 ንዑስ አንቀጽ 16.26.1 በመንግስት ግዥ አፈጻጸም እንደአስፈላጊነቱ ለአንድ አቅራቢ ከውሉ ጠቅላለ ዋጋ እስከ 30 በመቶ (30%) የሚደርስ የቅድምያ ክፍያ ሊሰጥ ይችላል ይላል፡፡ ይሁን እንጂ

በዋናው መ/ቤት

- በወጪ ማስመሰከሪያ ቁጥር 22983 በቀን 10/10/2013 ዓ.ም በሂሳብ መደብ 2221103 ለሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ የሪፍረሽመንት እና የአዳራሽ አገልግሎት በሚል **ብር 269,255.25** ሲከፈል ክፍያው በተሰብሳቢ መመዝገብ ሲገባው ከክፍያው ሰነዱ ጋር ምንም አይነት የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ ዩኒቨርስቲው ቀድሞ ክፍያ እንዲከፈለው በጠየቀው ደብዳቤ ብቻ ሂሳቡ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤

- መ/ቤቱ በቀን 28/7/2013 በኢንቮስ ቁጥር 22298 በብር 171,626.00 የባንዴራ መደርደሪያ ሽልፍ በቀጥታ ግዥ ከሙሃመድ ግዛው ሲገዛ ለድርጅቱ በመመሪያው መሰረት የቅድመ ክፍያ መከፈል የነበረበት ከአጠቃላዩ ዋጋ ብር 171,626.00 ላይ 30% ብር 51,487.80 ብቻ መሆን ሲገባው መመሪያውን በመተላለፍ 100% ብር 171,626.00 በወጪ ለመያዝ የሚያስችል ማስረጃ ሳይቀርብ በቀን 19/6/2013 በኢንቮይስ ቁጥር 18452 ከመመሪያ ውጪ ቅድሚያ ክፍያ በሚል ለድርጅቱ የተከፈለ መሆኑ በኦዲቱ ለማረጋገገጥ ተችሏል፡፡

<u>በመስኮት ኦማን</u>

- በቀን 24/12/2012 በኢንቮይስ ቁጥር 95261 **ብር 149,365.88 (1,612.50 ኦማን ሪያል)** ለኢምባሲው ጽ/ቤት የሚሆን ሲኩሪቲ ካሜራ ለመግዛት ለድርጅቱ የተከፈለ ቅድመ ክፍያ
- በቀን 27/5/2013 በኢንቮይስ ቁጥር 232962 **ብር 62,988.40 (680.00 ኦማን ሪያል)** ለኢምባሲው ጽ/ቤት የሚሆን የኢንተርኔትና የካሜራ ሲስተም በክስ ደህንነት ለመጠበቅ ሲኪሪቲ ቁልፍ ለማሰራት ለድርጅቱ ቅድመ ክፍያ ወጪ የሆነ፤
- በቀን 5/12/2013 በኢንቮይስ ቁጥር 27443 **ብር 71,948.04** ምዝገባው በቅደመ ክፍያ ሂሳብ ተይዞ መመዝገብ ሲገባ ማስረጃ ሳይኖር በ6244 የሂሳብ መደብ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤

በአጠቃላይ በድምሩ ብር 553,557.57 ለድርጅቶቹ ሲክፈል ክፍያውን በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበ መሆኑን በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት፤</u>

- ያለበቂ ማስረጃ/ሰነድ ክፍያን በወጪ መመዝገብ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡
- ላልተገኘ አገልግሎት የሚከፈል ክፍያን በወጪ መመዝገብ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ካለማስቻሉ በተጨማሪ ቀድሞ የተከፈለለት አገልግሎት ላይገኝ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

<u>የዋናው ፋይናንስ፤</u>

ክፍያው በወጪ ሲመዘገብ ማስረጃ ባልቀረበበት እና ቅድሚያ ክፍያ በሚል አጠቃላይ የውል ዋጋ (100%) ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ በመሆኑም ግዥዎች በግዥ መመሪያው መሠረት መፈጸም ይኖርባቸዋል፡፡ እንዲሁም ከመመሪያ ውጪ ቅድመ ክፍያ መክፍል ተገቢ ባለመሆኑ ሊታረምና ቅድሚያ ክፍያም በተሰብሳቢ መመዝገቡ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

በኦማን ሙስካት ሚስዮን፤

በመመሪያው መሰረት ቅድሚያ ክፍያን በተሰብሳቢ ሂሳብ መዝገብ ሲገባ በወጪ መመዝገቡ አግባብነት የለውም፡፡በመሆኑም አገልግሎቱን የሰጠው ድርጅት በተከፈለው የገንዘብ መጠን ልክ ደረሰኝ ቆርጦ የሰጠ በመሆኑ ምክንያት ቀጥታ በወጪ የተያዘ መሆኑን፤ በሚል የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

ከሚያዚያ 25 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ ለ69 የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባልደረቦች ለ45 ቀናት ለሪፍሬሽመንት እና አደራሽ አገልግሎት ከድርጅቱ ጋር በብር 288,040.50 ዉል መዋዋላችን ይታወሳል፡፡

በዚሁ መሰረት ድርጅቱም በዉሉ መሰረት የሪፍሬሽመንት እና የአደራሽ አገልግሎት ለመስጠት እኛም በዉላችን መሰረት ክፍያዉን ለመከፈል የተስማማን ቢሆንም አገልግሎቱ ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም የሚጠናቀቅ በመሆኑ በአመቱ መጨረሻ ላይ ለመክፈል የምንቸገር መሆኑን ከግምት ዉስጥ በማስገባት በዉላችን መሰረት ሰኔ 10 ቀን 2013 ዓ.ም ሙሉ ክፍያዉን የከፈልን ሲሆን|

ነገር ግን አገልግሎቱን ካገኘን በ፟ኋላ ወይም ግማሽ ክፍያ ለመክፈል አስበን የነበረ ቢሆንም ከዚሁ ዩኒቨርስቲ ጋር በተለያ ጊዚያት አብረን እየሰራን በመሆኑና በቀጣይም የምንሰራ መሆኑን ከግምት ዉስጥ በማስገባት ከዚህ ቀደም የነበራቸዉን አፈጻጸም በማየት እንዲሁም በዉሉ መሰረት አገልግሎት እየሰጡ ያሉ በመሆኑ በዉሉ መሰረት ሙሉ ክፍያ የተከፈለ መሆኑን እናሳዉቃለን፡፡

በኦማን ሙስካት ሚስዮን የተለያዩ ወጪዎች ለተከናወነበት ብር 149,365.88 ክፍያ ሲከናወን በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበ ለሚለው እንደየአገራቱ አሰራር ድርጅቶች የራሳቸው የሆነ አሰራር እንዳላቸው ከግንዛቤ እንዲወሰድልን እያልን በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 95261 የተከፈለው ብር 149,365.88 ለሚሲዮኑ ጽ/ቤት እና ለክቡር አምባ. መኖሪያ ቤት ካሜራ የተገጠመበት ቅድመ ክፍያ ቢሆንም አገልግሎቱን የሰጠው ድርጅት በተከፈለው የገንዘብ መጠን ልክ ደረሰኝ ቆርጦ የሰጠ በመሆኑ ምክንያት ቀጥታ በወጪ የተያዘ መሆኑን ለዚህም ቀሪ ክፍያውን በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 95287 ሲከፍል ብር 49788.62 ድርጅቱ ለቀሪው ክፍያ ብቻ ደረሰኝ የሠጠ በመሆኑ ሚሲዮኑ የቀሪውን ክፍያም በደረሰኙ መሰረት በወጪ የያዘ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አባሪ አድርገን ያቀረብን በመሆኑ

እንዲታይልን፣ ሚስዮኑ የተለያዩ ወጪዎች ለተከናወነበት ብር 62,988.40 ክፍያ ሲከናወን በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበ ለሚለው እንደየአገራቱ አሰራር ድርጅቶች የራሳቸው የሆነ አሰራር እንዳላቸው ከግንዛቤ እንዲወሰድልን እያልን በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 232962 የተከፈለው ብር 62,988.40 ለሚሲዮኑ ጽ/ቤት የኢንተርኔት እና የካሜራ ሲስተም ቦክስ ፓርቲሽን ለመዘጋት የፓርቲሽን ስራ አገልግሎት ቅድመ ክፍያ ቢሆንም አገልግሎቱን የሰጠው ድርጅት በተከፈለው የገንዘብ መጠን ልክ ደረሰኝ ቆርጦ የሰጠ በመሆኑ ምክንያት ቀጥታ በወጪ የተያዘ መሆኑን ለዚህም ቀሪ ክፍያውን በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 232996 ሲከፍል ብር 15,747.10 ድርጅቱ ለቀሪው ክፍያ ብቻ ደረሰኝ የሠጠ በመሆኑ ሚሲዮኑ የቀሪውን ክፍያም በደረሰኙ መሰረት በወጪ የያዘ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አባሪ አድርገን ያቀረብን በመሆኑ እንዲታይልን፣ ሚስዮኑ የተለያዩ ወጪዎች ለተከናወነበት ብር 71,948.04 ክፍያ ሲከናወን በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበ ለሚለው እንደየአገራቱ አሰራር ድርጅቶች የራሳቸው የሆነ አሰራር እንዳላቸው ከግንዛቤ እንዲወሰድልን እያልን በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 27443 የተከፈለው ብር 71,948.04 ለሚሲዮኑ ጽ/ቤት ካሜራ የተገጠመበት አገልግሎት ቅድመ ክፍያ ቢሆንም አገልግሎቱን የሰጠው ድርጅት በተፈለገው መንገድ ስራውን መስራት ባለመቻሉ ገንዘቡ በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 709774 ተመላሽ ያደረገ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አባሪ አድርገን ያቀረብን በመሆኑ በድጋሚ እንዲታይልን እንጠይቃለን፡፡

<u>የኦዲተር አስተያየት</u>

መ/ቤቱ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ መሠረት ሂሳቡን መዝግቦ መያዝ ሲገባው መሰረት በውሉ መሰረት አገልግሎት እየሰጡ ያሉ በመሆኑ የተከፈለ ነው በማለት በሥራ አመራሩ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡ በተጨማሪም አገልግሎቱን የሰጠው ድርጅት በተከፈለው የገንዘብ መጠን ልክ ደረሰኝ ቆርጦ ቢያቀርብም መ/ቤቱ አገልግሎቱን ወይም ዕቃውን ማግኘቱን ሳያረጋግጥ ሂሳቡን በወጪ መመዝገቡ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

2.8 <u>ግኝት፤ የግዥ መጠየቂያ ሳይኖር የተፈጸመ ግዥ ብር 1,461,456.39፤</u>

የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት ስለገንዘብ ክፍያ፤ አንቀጽ 9 ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች ከሚለው ስር ንኡስ አንቀጽ 1

ላይ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት እቃው እንዲገዛ ወይም አገልግሎት እንዲሰጥ ትእዛዝ የተሰጠበት ማስረጃ መኖሩን ማረጋገጥ እንደሚገባ በግልጽ ያስቀምጠል፡፡ ይሁን እንጂ

- በኒውዮርክ ኤምባሲ በድምሩ ብር 929,016.55 (26,117.98 ዶላር)፤
- በናይሮቢ ኤምባሲ በድምሩ ብር 463,124.81(1,366,149.88 ሽልንግ)፤እንዲሁም
- በኦማን ኤምባሲ በድምሩ ብር 69,315.03 (748.3 ሪያል)፤ ሲከፈል፤

በአጠቃላይ በድምሩ ብር 1,461,456.39 ለተለያዩ ድርጅቶች በተለያዩ ቀናትና በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች የእቃና የአገልግሎት ግዥ ለተፈፀመበት ሲከፈል ግዥዎቹ የግዥ መጠየቂያ የሌላቸው ስለመሆኑ በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት፤

- ፍላጎትን መሰረት ያላደረገ ግዥ እንዲፈጸም ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡
- በፍላጎት መሰረት ያልተገዛ ንብረት/እቃ ተገቢ ያልሆነ የንብረት ክምችት ሊፈጠር ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፤

በፈላጊው ክፍል እቃው በግዥ መጠየቂያ ተጠይቆ በሚሲዮኑ መሪ ሲጸድቅ በግዥ ክፍል ግዥው መፈፀም ይኖርበታል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

በተለያዩ ድርጅቶች በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች እቃና የአገልግሎት ግዝ ለገዛበት ሲከፈል ግዥዎቹ የግዥ መጠየቂያ የሌለቸው ስለመሆኑ ታይቷል ለሚለው

- **በኒዮርክ** ሚሲዮን በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 54874፣ 54915፣ 54908፣ 54850፣ 55315፣ 55339 ብር 304,057.34 ወጪው የአገልግሎት ክፍያ ስለሆነ የግዥ መጠየቂያ ሳይሆን የክፍያ መጠየቂያና መፍቀጃ ተያይዟል በድጋሚ እንዲታይልን፣ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 54864፣ 54893፣,54940፣ 54973፣ 55302፣ 54980፣ 55097፣54988፣55323፣54980 ብር 616,051.05 ወጪው የጥገና አገልግሎት ስለሆነ የግዥ መጠየቂያ ሳይሆን የክፍያ መጠየቂያና መፍቀጃ ተያይዟል በድጋሚ እንዲታይልን፣በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 55053፣55099፣55096፣ብር 8,908.16 በቀጣይ በተሰጠን አስተያየት መሰረት የምንሰራ መሆኑን እንገልፃለን፡፡ (በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 55096ሁለት ጊዜ ስለተጠየቀ አንዱን ብቻ ቢያዝ)

- **ናይሮቢ** በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 47107 ብር 273,568.93 ወጪው የአገልግሎት ክፍያ ስለሆነ የግዥ መጠየቂያ ሳይሆን የክፍያ መጠየቂያ የተያያዘ በመሆኑ በድጋሚ ቢታይልን፤ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 47201 ብር 4,237.50 ወጪው የጥገና አገልግሎት ስለሆነ የግዥ መጠየቂያ ሳይሆን የክፍያ መጠየቂያና መፍቀጃ የተያያዘ በመሆኑ በድጋሚ ቢታይልን፣ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 47149 ብር 173,058 ክፍያው ለተለያዩ አገልግሎቶች የተፈፀመ ክፍያ ሲሆን ከዚህም ውስጥ ለጥበቃ፣ለመብራት አቅራቢ፣ለስልክ መስመር፣ለወተት አቅራቢ የተከፈለ ሲሆን ለዚህም በውል የሚፈጸሙ ግዥዎች እንደሆኑ ሚሲዮኑ አስረድቷል፡፡ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 30901፣ 30899፣ 30945፣ 232841 ብር 12,259.87 በቀጣይ በተሰጠን አስተያየት መሰረት የምንሰራ መሆኑን እንገልፃለን፡፡**ኦማን** በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 233159 ብር 42,267.07 በቀጣይ በተሰጠን አስተያየት መሰረት የምንሰራ መሆኑን እንገልፃለን፡፡ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 233092፣ 233112 ብር 27,047.96 ወጪው የሎካል ሰራተኛ የደንብ ልብስ ስፌት አገልግሎት ስለሆነ የግዥ መጠየቂያ ሳይሆን የክፍያ መጠየቂያና መፍቀጃ የተያያዘ በድጋሚ እንዲታይልን እንጠይቃለን፡

<u>የኦዲተር አስተያየት፤</u>

ከክፍያ መጠየቂያ በፊት የአገልግሎትም ሆነ የዕቃ ግዥ መጠየቂያ ሊቀርብ ሲገባ በሥራ አመራሩ በተሰጠው ምላሽ የጥገና አገልግሎት ስለሆነ የግዥ መጠየቂያ ሳይሆን የክፍያ መጠየቂያና መፍቀጃ የተያያዘ መሆኑ ፤የሰራተኛ የደንብ ልብስ ስፌት አገልግሎት ስለሆነ የግዥ መጠየቂያ ሳይሆን የክፍያ መጠየቂያና መፍቀጃ የተያያዘ መሆኑ በሚል የተገለጸውን የክፍያ መጠየቂያን እንደ ግዥ መጠየቂያ አድርጎ ምላሽ መሰጠቱ ከመመሪያ አንጻር ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ግዥ ከግዥ ፈላጊው ክፍል የግዥ መጠየቂያ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2.9 <u>ግኝት፤ የሚሲዮኑ ማህትም የተደረገበት ፋክቱር/ደረሰኝ ሳይቀርብ የተከፈለ ብር 145,412.25፤</u>

የሚሲዮኖች የፋይናንስ እና የግዥ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2010 ላይ ፋክቱር/ደረሰኝ/ ለሌላቸው ወይም ለማይሰጡ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች መቅረብ የሚኖርበት የመክፈያ ቅጽን በተመለከተ በመጨረሻ ገጹ ላይ አስቀምጧል፡፡ በዚሁ የመክፈያ ቅጽ ላይ ማሳሰቢያ ብሎ ቅፁ ህጋዊ የሚሆነው ከተሰራ በኃላ የሚሲዮኑ ማህተም ሲያርፍበት ብቻ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ፤

የናይሮቢ ኤምባሲ በተለያዩ ቀናት እና በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች **በድምሩ ብር 145,412.25 (428,944.70 ሽልንግ)** ለተገኘ አገልግሎትና የእቃ ግዥ ሲከፍል ከክፍያው ጋር የቀረበው የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ በመመሪያው ላይ እንደተገለጸው የሚሲዮኑ ማህትም ያረፈበት መሆን ሲገባው ማህተም የሌለው መሆኑ በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የእቃና የአገልግሎት ግዥዎችን ህጋዊና እውቅና ካላቸው ተቋማት በመግዛት ህጋዊ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኞችና ማስረጃዎችን እንዲያቀርቡ ማድረግ ሲቻል ግዥዎች በአብዛኛው ከግለሰቦችና ደረሰኝ ከሌላቸው ድርጅቶች እንዲገዙ የሚደረግ መሆኑ በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ስጋት፤

- ከሚሲዮኑ መሪ/ከሚሲዮኑ/ እውቅና ውጪ ክፍያው ሊፈጸም ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፤

በሚሲዮኖች የፋይናንስ እና የግዥ አስተዳደር መመሪያ መሰረት መሠራቱ ተገቢው ክትክልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

በመመሪያ 9/2010 መሰረት ደረሰኝ ማቅረብ ለማይችሉ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ከመመሪያው ጋር አባሪ በተደረገው የመክፈያ ቅጽ መሰረት አስፈላጊውን መረጃ በመሙላት እና የሚሲዮኑን ማህተም በማሳረፍ አባሪ መደረግ እንደሚገባው ይታወቃል ሆኖም ግን በናይሮቢ ኤምባሲ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 47117፣ 47116፣ 47112፣ 47216፣ 47213፣ 47210፣ 47243፣ 47106፣ 47114፣ 47261፣ 47413፣ 47412፣ 47345 ብር **145,412.25** ቅጹ ተሞልቶ አባሪ ሲደረግ ማህተም ያለመኖሩ ምክንያት በስራ መደራረብ አልፎ አልፎ የተፈጠረ መሆኑን ከግምት እንዲገባልን እና ሚሲዮኑ በቀሪው ላይ ማህተም በማድረግ የቀረበ መሆኑን እየገለፅን ከግኝት እንዲወጣልን እንጠይቃለን፡፡

የኦዲተር አስተያየት

ከኦዲት ግኝት በኂላ ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ በወቅቱ ያልነበረና ያልተሰራን ስራ እንደነበረ ወይም እንደተሰራ አደርጎ በማቅረብ እንዲሁም በቀደመ በጀት አመት ከተያዘ የኦዲት ግኝት ትምህርት በመውሰድ ማስተካከል ሲገባ ማስረጃ በማዘጋጀት እንደነበረ አድርጎ በማቅረብ ተጨማሪ የአሰራር ስህተት መፈፀም ሌላ ወንጀል መስራት በመሆኑ ሊታረም ይገባል። በመሆኑም ማስረጃው ቢቀርብም በኦዲት ወቅት ያልነበረና ፎቶ ኮፒ በመሆኑ ለመቀበል ያስቸግራል።

የኦዲት ዓላማ የተሻለ የአሰራር ስርዓት እንዲኖር ማገዝ ሲሆን የኦዲት ግኝቶች እንዳይያዙና የተያዙትም ከሪፖርት እንዲወጡ ለማድረግ ሲባል ብቻ አግባብ ያልሆኑ ማስረጃዎችን እንዲቀርቡ ማድረግ ተጠያቂነትን የሚያስከትል በሁሉም ሚሲዮኖች እርምት ሊደረግበት ይገባል።

2.10 <u>ግኝት፤ ለሎካል / ለኮንትራት/ ሰራተኞች የተከፈለ የካሳ ክፍያ ብር 1,011,542.79 ፤</u>

በአዋጅ ቁጥር 377/96 (ስለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ በወጣ አዋጅ) ዘርፍ ሦስት ስለ ስራ ስንብት ክፍያና ስለካሣ አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) ድርጅቱ በመክሰሩ ወይም በሌላ ምክንያት ለዘለቄታው በመዘጋቱ የስራ ውል ሲቋረጥ፤1(ለ) ህግ ከደነገገው ውጪ በአሰሪው አነሳሽነት የስራ ውል ሲቋረጥ፤1(ሐ) በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት ሰራተኛው ከስራ ሲቀነስ፤1(መ) አሰሪው በሰራተኛው ላይ ሰብዓዊ ክብሩንና ሞራሉን የሚነካ ወይም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሰረት የሚያስቀጣ አድራጎት በመፈጸሙ የተነሳ ሠራተኛው የስራ ውሉን ሲያቋራጥ፤ 1(ሠ) አሰሪው ለሰራተኛው ድኅንነት ወይም ጤንነት የሚያሰጋ አደጋ እንዳይደርስ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት እርምጃ ባለመወሰዱ የተነሳ ሠራተኛው የስራ ውሉ ሲቋረጥ፤ ወይም 1(ረ) ሙሉ ወይም ዘላቂ የአካል ጉዳት በመድረሱ ሠራተኛው ስራ ለመስራት አለመቻሉ በህክምና ተረጋግጦ የስራ ውሉ ሲቋረጥ በአሰሪው የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት እንዳለው ያስቀምጣል። ይሁን እንጂ

- በዋናው መ/ቤት በቀን 15/3/2013 ዓ.ም በኢንቮይስ ቁጥር 20813 በዋናው መ/ቤት ቅጥር ተፈጽሞላቸው በዳካር የኤፌዲሪ ኤምባሲ በሎካል ሰራተኝነት ይሰሩ ለነበሩ ወ/ሪት አስቴር ሃንዲሶ ስራቸውን በፍቃዳቸው በለቀቁበት ሁኔታ የአገልግሎት ካሳ ክፍያ በሚል ብር **39,301.08** የተከፈለ መሆኑ፤

- በፕሪቶርያ ኢንባሲ በቀን 22/07/2013 ዓ.ም በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 0032962 በሎካል ደንብ መሰረት ለ14 ዓመት ከ6 ወራት ከ18 ቀናት አገልግለው ከስራ ለተሰናበቱት በሚል Juta Ramolefe Makube ለተባለ ግለሰብ የአገልግሎት ካሳ ክፍያ በሚል **ብር 32,863.71 /16,632.02 ራንድ/** የተከፈለ መሆኑ፤
- በናይሮቢ ኢንባሲ በቀን 05/05/2013 ዓ.ም በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 47275 በሎካል ደንብ መሰረት ለ5 ዓመት ከ9ወራት ከ13 ቀናት አገልግለው ከስራ ለተሰናበቱት በሚል Mr. Caroline Bora የአገልግሎት ካሳ **ክፍያ ብር 66,059.09** (194,864.57 ሽልንግ) ፣ በቀን 09/04/2021 ዓ.ም በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 97292 በሎካል ደንብ መሰረት ኤምባሲውን አገልግለው ከስራ ለተሰናበቱት በሚል ያሬድ ኃይሌ **14,998.27** ብር(44,242.68ሽልንግ) እና ሂሩት ኃ/ኢየሱስ ብር **9,566.09** (28,218.55ሽልንግ) የአገልግሎት ካሳ ክፍያ በሚል በጠቅላላ ድምር ብር **90,623.45** (267,325.80 ሽልንግ) የተከፈለ መሆኑ እንዲሁም፤
- በለንደን ኢንባሲ በቀን 10/09/2013 ዓ.ም በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 037138 በሎካል ሰራተኝነት በኮንትራት ይሰሩ ለነበሩ ለወ/ሮ እጅጋየሁ አለሙ ከስራቸው ሲሰናበቱ በቋሚ ሰራተኛና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ አዋጅና መመሪያ መሰረት የአገልግሎት ካሳ ክፍያ በሚል በሂሳብ መደብ 6416/ 1201220/ ብር **848,754.55(23,861.528 ዶላር)** የተከፈለ መሆኑ፤

በአጠቃላይ በድምሩ ብር 1,011,542.79 ያለአግባብ የተከፈለ መሆኑ በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት፤</u>

- በመንግስት የሚወጡ መመሪያዎች ተግባራዊ የማይደረግ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ ሊባክን ይችላል፡፡
- ተጠያቂነትንም ሊያስከትል ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

<u>ዋናው መ/ቤት</u>

ከምላሹ ጋር በቀረበው የተሸሸላው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 የገቡት የሰራ ውል/የቆይታ ጊዜ/ ሲቋረጥ ካሳ ይከፈላቸዋል የሚል ባለመኖሩ የውል አካል በማድረግ ውል መውሰድ ተገቢ ባለመሆኑ የቀረበው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም ከመመሪያ ውጪ የተከፈለው ክፍያ አለአግባብ በመሆኑ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

<u>የሚሲዮኖችን በተመለከተ</u>

ያለአዋጅ የተከፈለው ክፍያም ተገቢነት ስለሌለው የተፈጸመው ክፍያ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

- የካሳ ክፍያን በተመለከተ ቀደም ሲል በመ/ቤቱ እና በሰራተኛው መካከል የተደረገ የውል ስምምነት የአራት አመት የጊዜ ገደቡ በማብቃቱ ውሉ የተጠናቀቀ በመሆኑና የሥራ ውል በመቋረጡ ፣ለተጨማሪ 3 አመት በጤና እክል ምክንያት ለማደስ ባለመፈለጋቸው በህጉ መሰረት 1 ወር የማሳወቂያ ጊዜ በመስጠት መ/ቤቱን የለቀቁ ሲሆን መ/ቤቱን ለአገለገሉበት 4 አመት ከ 1 ወር በህጉ መሰረት ለሰራተኛዋ ሂሳቡን አስልቶ የአገልግሎት ክፍያው ተከፍሏቸዋል፡፡ሰራተኛዋ በኮካል ደንብ መሰረት ለወጥ ቤትና መስተንግዶ የሥራ ዘርፍ አመታት በኮንትራት የተቀጠሩ በመሆኑና ወደ አገር ቤት ተመልሰው በተመሳሳይ የሥራ ዘርፍ ለመመደብ መ/ቤቱ ቦታ ስለሌለው በገቡት ውል መሰረት የውል ጊዜው ሲጠናቀቅ /የሥራ ውል ሲቋረጥ/ለአገለገሉበት የ አራት አመት ቆይታ ካሳ ተከፍሏቸው ስለተሰናበቱ ጉዳዩን ከግምት በማስገባት ከግኝት እንዲወጣልን እንጠይቃለን፡፡
- በፕሪቶሪያ፣ናይሮቢና ለንደን ሚሲዮኖች በተለያየ ጊዜያት ለሎካል ሰራተኞች የአገልግሎት ካሳ ክፍያ ብር 942,241.71 አለአግባብ የተከፈለ ለሚለው በኦዲት ወቅት ከተሰጠው ምላሽ በተጨማሪ በሚሲዮኑ የሚቀጠሩ ኮንትራት ሰራተኞች እንደሚታወቀው አገር ውስጥ ያለውን የኢኮኖሚ ሁኔታ በመገንዘብ የውጭ ዜጋ ቀጥሮ ከማሰራት ይልቅ ቅድሚያ የመደቡ በጀት ያስተዳድራቸዋል ተብሎ ሲገመት አንድም ስራ አጥነትን ከመቀነስ አኳያ ለአገራችን ዜጎች ቅድሚያ በመስጠት የሚሰማሩ መሆኑ እንዲሁም ለመደቡ የተፈቀደው በጀት ዝቅ በሚልባቸው አገራት ላይ የአገሩ ዜጎች የሚቀጠሩ መሆኑን እየገለፅን፤ በሌላ በኩል አገራችን ካላት በጀት አንፃር ለመደቡ የሚደለደለው በጀት በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ቅጥራቸው ሚሲዮኑ በሚገኝበት አገር ባለው የሠራተኞች አዋጅና ህግና መሰረት ስንብት ቢፈፀም የተቋማችንን ብሎም የአገራችንን በጀት ስለሚፈትን በአገራችን ባለው የሰራተኛ እና አሰሪ አዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት ቅጥር የምንፈፅም መሆኑን እና የተሻሻሉ ህጎችን መሰረት ያደረገ የስንብት ክፍያዎች የሚፈፀሙ መሆኑን እየገለፅን ግኝቱ በድጋሚ እንዲታይልን እንጠየቃለን፡፡

<u>የኦዲተር አስተያየት፤</u>

- በአዋጅ ቁጥር 790/2005 ላይ እንዲሁም እ.ኤ.አ 1961 የተወሰደው ስምምነትም ላይ ስለ ኩንትራት ቅጥር የተገለጸ ሃሳብ ባለመኖሩ፤

- በአዋጅ ቁጥር 377/96 (ስለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ በወጣ አዋጅ) ዘርፍ ሦስት **ስለ ስራ ስንብት ክፍያና ስለካሳ** አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) ድርጅቱ በመክሰሩ ወይም በሌላ ምክንያት ለዘለቄታው በመዘጋቱ የስራ ውል ሲቋረጥ፤1(ለ) ህግ ከደነገገው ውጪ በአሰሪው አነሳሽነት የስራ ውል ሲቋረጥ፤1(ሐ) በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት ሰራተኛው ከስራ ሲቀነስ፤1(መ) አሰሪው በሰራተኛው ላይ ሰብዓዊ ክብሩንና ሞራሉን የሚነካ ወይም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሰረት የሚያስቀጣ አድራጎት በመፈጸሙ የተነሳ ሠራተኛው የስራ ውሉን ሲያቋራጥ፤ 1(ሠ) አሰሪው ለሰራተኛው ድኅንነት ወይም ጤንነት የሚያሰጋ አደጋ እንዳይደርስ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት እርምጃ ባለመወሰዱ የተነሳ ሠራተኛው የስራ ውሉ ሲቋረጥ፤ ወይም 1(ረ) ሙሉ ወይም ዘላቂ የአካል ጉዳት በመድረሱ ሠራተኛው ስራ ለመስራት አለመቻሉ በህክምና ተረጋግጦ የስራ ውሉ ሲቋረጥ በአሰሪው የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት እንዳለው ነው ያስቀምጣል፡፡በሌላ በኩል በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ላይም ቢሆን ስለ ኮንትራት ሰራተኞች የስራ ስንብትና ካሳ በግልጽና በዝርዝር ባልተገለጸበት ሁኔታ ስራ አጥነትን ከመቀነስ አኳያ በሚል ክፍያ መፈፀሙን በመግለፅ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡ በተጨማሪም በአዋጅ ባልተገለጸና ባልተደገፈ ሁኔታ ክፍያን መፈጸም አግባብነት የለውም፡፡ ስለሆነም ከአዋጅ ወጪ ክፍያ እንዲፈጸም የፈቀዱ የሥራ ኃላፊዎች ተጠያቂ ሊደረጉ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደገም ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.11 <u>ግኝት፤ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የተፈፀመ ክፍያ ብር 259,030.87</u>፤

የፌደ.ራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀፅ ዘጠኝ ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች በሚለው ስር ማንኛዉም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ተራ ቁጥር 7 ላይ ለተገዛ እቃ/አገልግሎት ሂሳብ ማወራረጃ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ኦርጅናል ደረሰኝ መሆን እንዳለበት በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ይሁን እንጂ

በዋናው መ/ቤት በቀን 5/6/2013 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 21613 ብር **176,829.32** እንዲሁም በቀን 6/5/2013 በወጪ ማስከሪያ ቁጥር 20490 **ብር 82,201.55 በድምሩ ብር 259,030.87** ከበላይ አብ ሞተርስ ተሽከርካሪ ላስጠገነበት በዱቤ የሽያጭ ደረሰኝ (Credit sales invoice) ክፍያ መፈፀሙን በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት፤</u>

ህጋዊ እና ኦርጅናል የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳይኖር ወይም ሳይቀርብ ክፍያ መፈጸም የሂሳቡን ትክክለኛነት ካለማሳየቱ ባለፈ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

ማንኛውንም አይነት ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት መሟላት ያለባቸውን መሰረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች ስለመሟላታቸው ሊረጋገጥና ክፍያ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ተከፈለ የተባለው ተከፍሎ ሳይሆን ህጋዊ ደረሰኝ ቀርቦለት በደረሰኝ የተከፈለ መሆኑን እየገለፅን ፣ ነገር ግን ሰነዱ ፋይል ሲደረግ ደረሰኙ አብሮ ያልተያያዘ በመሆኑ በኦዲት ግኝቱ መሰረት ከሰነዶቹ ጋር አብሮ ያያዝን በመሆኑ እና ለወደፊቱ ጥንቃቄ የሚወሰድ ይሆናል፡፡

<u>የኦዲተር አስተያየት</u>

የቀረበው የዋናው ፋይናንስ ማስረጃ በተጠየቀው የገንዘብ መጠን ልክ የቀረበ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ቢሆንም ዋናው ወይም ኦርጅናል የክፍያ ደረሰኝ ባለመሆኑ ኦርጅናል የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሊቀርብ ይገባል፡፡

2.12 <u>ግኝት፤የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ ብር 547,158.02፤</u>

የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመርያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለ ወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረብ እና ስልጣን ባለው አካል መፈቀድ አለበት በማለት ይደነግጋል፡፡ ይሁን አንጂ

<u>የናይሮቢ</u>

ኢንባሲ በተለያዩ ቀናቶችና በተለያየ የወጪ ማስመስከሪያዎች የመስተንግዶ አገልግሎት በድምሩ ብር **234,256.70 (691,022.69 ሽልንግ)** ለተለያዩ ድርጅቶች ሲከፈል፤ በተጨማሪም በተለያዩ ቀን እና የወጪ ማስመስከሪያዎች በድምሩ **ብር 177,987.54** (525,037.00ሽልንግ)

በድምር ብር 412,244.24 ክፍያ መፈፀሙን፤

<u>በፕሪቶሪያ ኢንባሲ</u>

በተለያዩ ቀን እና የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥሮች ለተለያዩ ድርጅቶች **በድምሩ ብር 134,913.78 (69,504.17 ራንድ)** ክፍያ መፈፀሙን፤

በአጠቃላይ በድምሩ ብር 547,158.02 ተገቢ ማስረጃ ከክፍያ ሰነዱ ጋር መቅረብ ሲገባ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ክፍያው የተፈፀመ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ስጋት፤

የውጪውን ትክክለኛነት ሊያረጋግጥ የሚችል ማለትም ለማን እና ለምን ወጪ እንደተደረገ የሚያሳይ ህጋዊና በቂ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ክፍያዎችን መፈጸም የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሊያስቸግር ይችላል፡፡ በተጨማሪም በሚሲዮኑ ስም ላልተሰጠ አገልግሎት ክፍው ሊከፈል ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፤

የኦዲት ግኝቱ ክፍያ የተፈፀመባቸው ደጋፊ ማስረጃዎች አለመቅረባቸውን የሚገልፅ እንጂ ደረሰኞች አልቀረቡም የሚል ባለመሆኑ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት የቀረበው ማስረጃ ሙሉ ስለመሆኑ በሚገባ ማጣራት ይኖርበታል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

በፌዴራል የመንግስት መሰሪያ ቤቶች የሒሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ሚሰዮኖች ክፍያ ሲፈፅሙ አስፈላጊና ተገቢ ማስረጃ ከክፍያ ሰነዱ ጋር ማቅረብ ሲገባ ያላቀረቡ መሆኑ ለሚለው፡

- **በፕሪቶሪያ** በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 97466 ብር 19,992.21 ሚሲዮኑ አመታዊ የቦሎ እድሳት ለ9 ተሽከርካሪች የሚያሳይ ማሰረጃ እና የሰሌዳ ቁጥራቸውን የሚያሳይ ማሰረጃ ያቀረበ በመሆኑ ማሰረጃው በድጋሚ ቢታይልን፣በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 97625፣ 97676፣ 97721 ብር 60,673.01 የሰርቪስ ቻርጅ ባንኩ ስለመቀነሱ ማስረጃው አባሪ የተደረገ በመሆኑ ማሰረጃው ቢታይልን፣ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 97674፣ 97551 ብር 56,744.52 የወጪ ማስረጃው አባሪ የተደረገ በመሆኑ ማሰረጃው እንዲታይልን እየጠየቅን፤
- **በናይሮቢ** ሚሲዮን በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 99634 ብር 3,480.51 አምባሳደሩ መኖሪያ ቤት የመጡ እንግዶች መስተንግዶ መሆኑ የእቃ ግዥ መጠየቂያው ላይ የተገለፀ መሆኑ፣ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 47428 ብር 1,695. በሚሲዮኑ መሪ በተሰጣቸው ፍቃድ መሰረት ለሚሲዮኑ እንግዶች የመስተንግዶ ወጪ መሆኑ፣በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 99655 ብር 9,159.78 የሚሲዮኑ መሪ በቪዛ ካርድ በተለያየ ጊዜያት ለሚሲዮ እንግዶች

የተፈፀሙ የመስተንግዶ ወጪዎች መሆኑ፣ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 99649 ብር 13,634.24 የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 47575 ላይ የግዥ መጠየቂያ እና ሞዴል 19 አባሪ በተደረገው መሰረት በክቡር አምባ. መኖሪያ ቤት ለሚሲዮኑ እንግዶች የመስተንግዶ ወጪ መሆኑ፣ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 99647 ብር 64,345.93 የግዥ መጠየቂያ ፎርም ላይ የመስተንግዶ ወጪው የተገለፀ መሆኑ፣ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 47587 ብር 24,879 በተለያየ ጊዜያት ለሚሲዮ እንግዶች በሆቴል የተከናወነ የመስተንግዶ ወጪዎች መሆኑ፣ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 47578 ብር 915.30 ለሚሲዮኑ እንግዶች የአቀባበል የመስተንግዶ እቃዎች ግዢ የተፈፀመበት ክፍያ መሆኑ፣ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 47568 ብር 59,877.57 በተለያየ ጊዜያት ለሚሲዮ እንግዶች በሆቴል እና በክቡር አምባ. በመኖሪያ ቤት የተከናወነ የመስተንግዶ ወጪዎች መሆኑ እንጠይቃለን፡፡

<u>የኦዲተር አስተያየት፤</u>

በሥራ አመራሩ በተሰጠው ምላሽ ማስረጃ መቅረቡ ቢገለጽም የቀረቡት ማስረጃዎች በኦዲት ወቅት የታዩ፤ ጥያቄ የተነሳበቸውና በግኝት የተያዙ በመሆናቸው ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም በኤምባሲዎቹ በተለያዩ ቀናቶችና በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች የተፈፀመው የመስተንግዶ አገልግሎት ክፍያ ለእነማን እንደተከፈለ፤ መስተንግዶ የተደረገበት ቀን ብዛት፤ እና መሰተንግዶ የተደረገበትን ምክንያት የሚገልፅ ማስረጃ ሊሆን ይገባል፡፡ በመሆኑም ተገቢው ማስረጃ ሊቀርብ ይገባል፡፡

3. <u>ተሰብሳቢ ሂሳብ፤</u>

3.1 <u>ግኝት በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 114,991,961.90፤</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 ፣ የፌደራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ቅድሚያ ክፍያዎች በወቅቱ የሚወራረዱ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤

- በዋናው ፋይናንስ በድምሩ ብር 7,850,787.11፤ እንዲሁም
- በሚሲዮን ፋይናንስ በድምሩ ብር 121,429,194.35 107,141,174.79

በአጠቃላይ በድምሩ ብር 114,991,961.90 በወቅቱ ሳይወራረድ በተሰብሳቢ ተይዞ ተገኝቷል ፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

ኦዲተሮች በመ/ቤታችን ውስጥ በኦዲት ስራ ወቅት በነበሩበት ወቅት የተሰጠው ምላሽ እንደተጠበቀ ሆኖ የመ/ቤታችን ተሰብሰቢ ሂሳብ በአብዛኛው የሶስወስተኛ ወገን ማለትም የተለያዩ የመንግስት መ/ቤቶች በውጭ አገር በሚገኙ ሚሲዮኖቻችን አማካኝነት አገልግሎቶችን ለማግኘት ጠይቀውና በሚመለከተው መ/ቤት ተፈቅዶ የተከፈለና በተሰብሳቢ ሂሳብ የተመዘገበ ሲሆን ሂሳቡን በወቅቱ እንዲተኩ በተደጋጋሚ የተጠየቀ ቢሆንም ባለመተካቱና ተቋማችን በየበጀት ዓመቱ በሚያደርገው የውጭ ምንዛሬ ማስተካከያ ምክንያት በከፍተኛ መጠን በየበጀት ዓመቱ እየጨመረ የመጣ በመሆኑና ከመንግስት መ/ቤት የሚሰበሰብ መሆኑን ለገንዘብ ሚኒስቴር የመንግስት ሂሳቦች ዳይሬክቶሬት የስራ ሃላፊዎች ጋር በተደጋጋሚ ግንዛቤ በማስጨበጥና መግባበት ላይ እየተደረሰ በመሆኑ 50 ሚሊዮን ብር የሚሆን ዝርዝር ማስረጃዎችን አቅርበን የተግባባን ስለሆነ የተሰብሳቢ ሂሳቡ በበጀት ዓመቱ ሊወራረድ እንደሚችል ይገመታል፡፡ይህ የማይፈጸም ከሆነ በተቋማችን ደረጃ ሂሳቡ እንዲተካ ተደጋጋሚ ጥያቄዎችን ከማቅረብ ባለፈ የምናደርገው ነገር ስለማይኖር የተሰብሳቢ ሂሳቢ በተመዘገበባቸው የመንግስት መ/ቤቶች ስም ተመዝግቦ የሚቆይ ይሆናል፡፡

በውጭ አገር የሚገኙ የኢፌድሪ ሚሲዮኖች የቢሮና የክቡራን አምባሳደሮች መኖሪያ ቤት በአገሮች ህግ መሰረት በኪራይ ስንከራይ ለሴኩሪቲ ዲፖዚት (Security Deposit) በማስያዣ የተያዘና በተሰብሳቢ ሂሳብ ለተመዘገበው ሂሳብ ብር 15,002,727.42 የኪራይ ውሉ እስካልተቋረጠ ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ ተመዝግቦ የሚቀጥል ሲሆን የኪራይ ውል እንድናቀርብ በወቅቱ ያልተጠየቅን ሲሆን አሁንም የኪራ ውሉን ለማየት የሚፈለግ ከሆነ ማቅረብ የሚቻል መሆኑ፤

የኦዲተር አስተያየት

- ለተለያዩ የኢፌድሪ ሚሲዮኖች ኪራይ የኪራይ ማስያዥ (Security Deposit) በተሰብሳቢ ተመዝግቦ የተያዘ ሲሆን የኪራይ ውል ጊዜያቸው የተጠናቀቀ ስምምነቶች ውሎቹ እንዲታደሱ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ከሶስተኛ ወገን የሚሰበሰቡ ሂሳቦችን በተመለከተ ለገ/ሚ/ር ጋር በመወያየት ሂሳቡ በመ/ቤቶቹ ስም እንዲደረግ በመውጫ ውይይት ወቅት በተሰጠው የማስተካከያ ሀሳብ መሰረት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል ፡፡

በየበጀት ዓመቱ በሚደረግ የቋሚ ምንዛሬ ለውጥ ምክንያት ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ እየጨመረ እንዲሄድ ያደርገዋል በሚል የተመለሰው በተመለከተ ተገቢው እርምጃ እንዲሰወድ ተገቢው ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

3.2 ግኝት ማስረጃ ያልቀረበለት ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 106,316,796.94

በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5/መ ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብለት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ በበጀት ዓመቱ

- በዋናው መ/ቤት **ብር 7,064,519.66፤** በሚሲዮን **ብር 99,076,321.37 በድምሩ ብር 106,140,841.03** በተለያዩ የሂሳብ መደቦች በተሰብሳቢ የተያዘ ማስረጃ ያልቀረበለት በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ በሂሳብ መደብ 4202 ብር 12,617.58፤ በሂሳብ መደብ 4210 ብር 64,864.56፤ እንዲሁም በሂሳብ መደብ 4274 ብር 98,473.77 **በድምሩ ብር 175,955.91**

በአጠቃላይ በድምሩ ብር **106,316,796.94** በተሰብሳቢ የተያዘበት ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ስጋት፤

ለቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰብሳቢውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አዳጋች ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ሂሳቡ ወደማይወራረድበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፤

መ/ቤቱ ባቀረበው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት የተገለጸው ሂሳብ በማስረጃ የተደገፈ ሊሆን ይገባል፡፡እንዲሁም ለኦዲት ሲጠየቅ የማቅረብ ግዴታ እንዳለበት ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የተሰብሳቢ ሂሳብ ሰነዶች ተቋሙ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ማስረጃ እንድናቀርብ ተጠየቅን የሚለው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለዚህ ማስረጃ ያልቀረበለት ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገቢው ማስረጃ ለኦዲት ስራ ሊቀርብ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በግኝቱ የተገለጸው ለተሰብሳቢ ሂሳቡ ማስረጃ እንዲቀርብ እንጂ ስለ ሂሳቡ መተካት አልተጠየቀም፡፡ በመሆኑም በተሰጠው ምላሽ የ3ኛ ወገን ሂሳብ በመሆኑ ሂሳቡ እንዲተካ በተደጋጋሚ ደብዳቤ በመጻፉ መገለጹ ለግኝቱ አግባብነት ያለው ምላሽ ሆኖ አልተገኘም፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

የኦዲት ግኝቱ በ2012 በጀት ዓመት እንደ ግኝት ቀርቦ የነበር ሲሆን በወቅቱ ስራ ክፍላችን ለኦዲተሮች በኦዲት ስራ ወቅት እያሉም ሆነ ከኦዲት ስራ ውጭ ከቢሯቸው ድረስ ኮፒ የሂሳብ ማስረጃዎችን በበቂ ሂኔታ አቅርበን የነበር ሲሆን በ2013 በጀት ዓመት ሰነድ እንዲቀርብ ጥያቄ ያልቀረበ መሆኑ፤

የተሰብሳቢ ሂሳብ የቋሚ ሂሳብ (Permanent Accounts) አካል በመሆናቸው በየበጀት ዓመቱ የሂሳብ ባላንሳቸውን (Carrying forward balance) ይዘው የሚመጡ ሲሆን የ2013 በጀት ዓመት የኦዲት ስራ በተከናወነ ወቅት በኦዲተሮች የናሙና አመራረጥ መሰረት በ2013 በጀት ዓመት ከተፈጠሩ የተሰብሳቢ ሂሳቢች ዝርዝር ውስጥ የተወሰኑትን እንድናቀርብ ተጠይቀን ማስረጃዎችን ሙሉ በሙሉ ያቀረብን ሲሆን የ2012 በጀት ዓመት ሰነዶችን እንድናቀርብ በወቅቱ ያልተጠየቅን ሲሆን ከላይ በግኝት ተ.ቁ 3.1 ላይ የሰጠነው ማብራሪያ የተቋሙ ተሰብሳቢ ሂሳብ በአብዛኛው በተለያዩ የመንግስት መ/ቤቶች ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ሂሳብ በመሆኑ ሂሳቡን ለማወራረድ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር እየተሰራ በመሆኑ ማስረጃ የለውም በሚል የቀረበው ትክክል አለመሆኑ፤

<u>የኦዲተር አስተያየት</u>

በተለያዩ የመንግስት መ/ቤቶች ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ሂሳብ በመሆኑ ሂሳቡን ለማወራረድ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር እየተሰራ በመሆኑ ማስረጃ የለውም በሚል የቀረበው ትክክል አይደለም በሚል ምላሽ ቢሰጥም የኦዲት ግኝቱ ለሂሳቡ ማስረጃ እንዲቀርብ የሚጠይቅ እንጂ ሂሳቡ መተካቱን በተመለከተ ባለመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ በመሆኑም ማስረጃ ያልቀረበለት ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገቢው ማስረጃ ሊቀርብለት ይገባል፡፡

4. ተከፋይ ሂሳብ፤

4.1 ግኝት፤ በወቅቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ በድምሩ ብር 45,850,474.08፤

በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 5/ሐ የተለያዩ አካላት ቀንሰው ያስቀሩትን የግብር እና ሌሎች ሂሳቦች ለሚመለከተው ግብር አስገቢ አካል ወቅቱን ጠብቀው ማስተላለፍ እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡ ይሁን እንጂ ፤ ከሚሲዮን ብር በድምሩ ብር

- በዋናው ፋይናንስ **በድምሩ ብር 5,715,851.95 እንዲሁም፤**
- በሚሲዮን ፋይናንስ **በድምሩ ብር 40,134,622.13**

በአጠቃላይ ድምር ብር 45,85,0474.08 በመ/ቤቱ በወቅቱ መከፈል ሲገባው ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ ስለመኖሩ በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ስጋት፤

- ተከፋይ ሂሳብ መከፈል ባለበት የጊዜ ገደብ የማይከፈል ከሆነ የዕዳ ክምችት ሊፈጠር ይችላል፡፡ ክምችቱም በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ላይ ተፅእኖ ሊያሳድር ይችላል፤፡
- ማስረጃ ያልቀረበለት ተከፋይ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሊያስቸግር ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፤

ለብር 1,988,249.24 የኪራይ ውል ማስያዢያ የኪራይ ውሉ እስካልተቋረጠ የተከፋይ ሂሳብ ቀጣይነት ያል መሆኑ ቢገለጽም ለኪራይ ውል ማስያዣ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ በመሆኑም ተከፋይ ሂሳቦች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲከፈሉ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የዊዝሆንዲንግ ተከፋይ መከፈል የሚገባው ታክስ በመሆኑ ለሚመለከተው አካል ገቢ መደረግ ሲገባው በተከፋይ መያዙ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ የደመወዝ ተቀናሽ ሂሳቦች ለገንዘብ ሚ/ር ፈሰስ በማድረግ ለባለመብቱ ክፍያ እንዲፈፀም ሲጠየቅ በጀት በማስፈቀድ እንዲከፈል መደረግ ሲገባው በተከፋይ ተይዞ መቆየቱ አግባብ ባለመሆኑ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድመደረግ ይኖርበታል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

1ኛ የሚሲዮናችን/የሀገራችን/ንብረት የሆኑ ህንፃ የኪራይ ማስያዣ(Security Deposit) በተከፋይ ተመዝግቦ የተያዘን በተመለከተ ፣ በኒዎርክ የሚገኘው የኢፌድሪ ቋሚ መልክተኛ ጽ/ቤት/ የሀገራችን/ ንብረት የሆነው ህንፃ በከራይ መልክ ሚሲዮኑ ሲያከራይ በሀገሩ ህግ መሰረት የኪራይ ውል ማስያዣ (Security Deposit) ማለትም በአገልግሎት ወቅት ለሚፈጠሩ የህንጻ ጉዳቶች ማስጠገኛ አገልግሎት የሚውል ገንዘብ ከተከራይ ካምፓኒ ተቀግሎ በሚሲዮኑ አካውንት በተከፋይ ሂሳብ ውስጥ ተመዝግቦ የሚገኝ በመሆኑ በግኝቱ ከተጠቀሰው የተከፋይ ሂሳብ ውስጥ ብር 1,988,249.24 የሚሆን ተከፋይ የኪራይ ውል እስካልተቋረጠ ድረስ የሚቀጥል መሆኑ፣

2ኛ. ከአንድ ዓመት በላይ የቆዩ በተከፋይ ሂሳብ ተመዝግበው የሚገኙ ሂሳቦች ከሂሳብ መዝገብ ላይ መሰረዝ እንዲቻል ከገንዘብ ሚኒስቴር ተጠይቆ ምላሽ ተሰጥቶ በትክክል ላይ የሚገኙ ሂሳቦችን በተመለከተ፡- በተቋማችን ከተጠቃለለው የሂሳብ ሪፖርት ውስጥ ከአንድ ዓመት

በላይና ለረጅም ዓመታት ሳያከፈል የቆዩ በተከፋይ ሂሳብ ተመዝግበው የሚታዩ ሂሳቦች በቀድሞው የሂሳብ መደብ ከ 5002 ብር 2,527,255.96 ፣ ከ5003 የሂሳብ መደብ ብር 30,464.34 ፣ ከ5004 የሂሳብ መደብ ብር 1,550,337.66 ፣ ከ5006 የሂሳብ መደብ ብር 306,702.32 ፣ ከ5009 የሂሳብ መደብ ብር 30,001.93 ፣ ከ5028 የሂሳብ መደብ ብር 7,229,249.43 ከ 5054 የሂሳብ መደብ ብር 3,028,234.64 በድምሩ ብር 15,451,712.51 ከመዝገብ ላይ መሰረዝ እንዲቻል የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ገንዘብ ሚኒስቴር በጠየቀው መሰረት አጣርተን የላክንና በክትትልላይ የሚገኝ መሆኑ፣

3ኛ. በየበጀት ዓመቱ የሚደረግ የቋሚ ምንዛሬ ለውጥ ምክንያት የተከፋይ ሂሳብ እየጨመረ የሚሄድ መሆኑ፣ ከላይ በተሰብሳቢ ሂሳብ ማብራሪያ የተጠቀሰው በየዓመቱ የሚደረገው የቋሚ ምንዛሬ ማስተካከያ ተመን ለተከፋይ ሂሳብ መጨመር እንደ ምክንያት የሚወሰድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

<u>የኦዲተር አስተያየት</u>

የኪራይ ውል ማስያዣ (Security Deposit) በተከፋይ የተያዘበት የኪራይ ውል ሊቀርብ ይገባል፡፡

4.2 ግኝት <u>ማስረጃ ያልቀረበለት የተከፋይ ሂሳብ ብር 46,070,705.1</u>

የፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 5(ሀ) ማናቸውም ወደፊት ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ ይኖርበታል ይላል፡፡ ይሁን እንጂ በመ/ቤቱ በ2012 በጀት አመት ኦዲት፤

- በዋናው መ/ቤት **ብር 5,922,154.37፤**
- በሚሲዮን **ብር 40,148,550.73**

በድምሩ ብር 46,070,705.1 ማስረጃ ያልቀረበለት ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ በዚህም የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑንና በ2013 በጀት አመት ኦዲትም ማስረጃው ያልቀረበ ስለመሆኑ በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡

<u>ስጋት፤</u>

ማስረጃ ባለመቅረቡ የተከፋይ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሊያስቸግር ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

ያለ ማስረጃ ለተመዘገበው ተከፋይ ሂሳብ ተገቢው የሰነድ ማስረጃ ሊቀርብ ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

1ኛ. የሚሲዮናችን/የሀገራችን/ንብረት የሆኑ ህንፃ የኪራይ ማስያዣ(Security Deposit) በተከፋይ ተመዝግቦ የተያዘን በተመለከተ ፣ በኒዎርክ የሚገኘው የኢፌድሪ ቋሚ መልክተኛ ጽ/ቤት/ የሀገራችን/ ንብረት የሆነው ህንፃ በከራይ መልክ ሚሲዮኑ ሲያከራይ በሀገሩ ህግ መሰረት የኪራይ ውል ማስያዣ (Security Deposit) ማለትም በአገልግሎት ወቅት ለሚፈጠሩ የህንጻ ጉዳቶች ማስጠገኛ አገልግሎት የሚውል ገንዘብ ከተከራይ ካምፓኒ ተቀግሎ በሚሲዮኑ አካውንት በተከፋይ ሂሳብ ውስጥ ተመዝግቦ የሚገኝ በመሆኑ በግኝቱ ከተጠቀሰው የተከፋይ ሂሳብ ውስጥ ብር 1,988,249.24 የሚሆን ተከፋይ የኪራይ ውል እስካልተቋረጠ ድረስ የሚቀጥል መሆኑ፣

2ኛ. ከአንድ ዓመት በላይ የቆዩ በተከፋይ ሂሳብ ተመዝግበው የሚገኙ ሂሳቦች ከሂሳብ መዝገብ ላይ መሰረዝ እንዲቻል ከገንዘብ ሚኒስቴር ተጠይቆ ምላሽ ተሰጥቶ በትክክል ላይ የሚገኙ ሂሳቦችን በተመለከተ፡- በተቋማችን ከተጠቃለለው የሂሳብ ሪፖርት ውስጥ ከአንድ ዓመት በላይና ለረጅም ዓመታት ሳያከፈል የቆዩ በተከፋይ ሂሳብ ተመዝግበው የሚታዩ ሂሳቦች በቀድሞው የሂሳብ መደብ ከ 5002 ብር 2,527,255.96 ፣ ከ5003 የሂሳብ መደብ ብር 30,464.34 ፣ ከ5004 የሂሳብ መደብ ብር 1,550,337.66 ፣ ከ5006 የሂሳብ መደብ ብር 306,702.32 ፣ ከ5009 የሂሳብ መደብ ብር 30,001.93 ፣ ከ5028 የሂሳብ መደብ ብር 7,229,249.43 ከ 5054 የሂሳብ መደብ ብር 3,028,234.64 በድምሩ ብር 15,451,712.51 ከመዝገብ ላይ መሰረዝ እንዲቻል የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ገንዘብ ሚኒስቴር በጠየቀው መሰረት አጣርተን የላክንና በክትትልላይ የሚገኝ መሆኑ፣

3ኛ. በየበጀት ዓመቱ የሚደረግ የቋሚ ምንዛሬ ለውጥ ምክንያት የተከፋይ ሂሳብ እየጨመረ የሚሄድ መሆኑ፣ ከላይ ነተሰብሳቢ ሂሳብ ማብራሪያ የተጠቀሰው በየዓመቱ ሚደረገው የቋሚ ምንዛሬ ማስተካከያ ተመን ለተከፋይ ሂሳብ መጨመር እንደ ምክንያት የሚወሰድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በተቋሙ ከአንድ ዓመት በላይና ለረጅም አመታት ሳይከፈል የቆዩና የተሟላ መስረጃ ሳይኖራቸው በመዝገብ ላይ ብቻ በተከፋይ ሂሳብ ተመዝግበው የሚታዩ ሂሳቦች ብር

15,451,712.51 ከመዝገብ ላይ መሰረዝ እንዲቻል ከኢ.ፌ.ደ.ሪ. ገንዘብ ሚኒስቴር በተጠየቀው መሰረት አጣርተን የላክን እና በክትትል ላይ የሚገኝ መሆኑን እየገለፅን ከግኝት እንዲወጣ እንጠይቃለን፡፡ ሂሳቡ የ2012 በጀት ዓመት ግኝት በመሆኑ ከግኝት ወጥቶ በክትትል ኦዲት ላይ እንደሚገባ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡

<u>የኦዲተር አስተያየት፤</u>

ማስረጃ ሊቀርብለት የሚገባው ተከፋይ ሂሳብ ተገቢው ማስረጃ ማቅረብ ሲገባ ሂሳቡ የ2012 በጀት ዓመት ግኝት በመሆኑ ከግኝት ወጥቶ በክትትል ኦዲት ላይ እንደሚገባ መግባባት ላይ ተደርሷል የሚለው ምላሽ አግባብነት የሌለውና ከሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ወጪ በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡ ስለሆነም በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሠረት ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

5. **<u>በጀት፤</u>**

5.1 <u>ግኝት፤ ስራ ላይ ያልዋለ መደበኛ በጀት በድምሩ ብር 128,488,326.70</u>፤

የፌደራል መንግስት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል 3 አንቀጽ 02/1 መ/ቤቱ ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛ ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠሩን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በመ/ቤቱ በዋናው ፋይናንስ በበጀት ዓመቱ ከተለያዩ የሂሳብ መደቦች ከተመደበ በጀት ስራ ላይ ያልዋለ በጀት **በድምሩ ብር 128,488,326.70** በበጀት አመቱ ከተለያየ የሂሳብ መድብ ከ10% በላይ ስራ ላይ ሳይውል ስለመቅረቱ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

<u>ስጋት፤</u>

መንግስት ለሌሎች መሰረተ ልማቶች ሊያውል የሚችለውን ገንዘብ በተገቢ ቦታና ጊዜ ጥቅም ላይ እንዳይውል ሊያደርግ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

መ/ቤቱ በጥናት ላይ የተመሰረተ የበጀት ዕቅድ በማዘጋጀት የተፈቀደለትን በጀት በስራ ላይ ማዋል ይጠበቅበታል፡፡ በሌላ መልኩ በጎላ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሳይውሉ በቀሩት የሂሳብ መደቦች የበጀት አጠቃቀም ላይ ክትትል በማድረግ እና የማይጠቀምበትን በጀት ለይቶ በማውጣት የበጀት እጥረት ላለባቸው መሥሪያ ቤቶች የበጀት ዝውውር ተደርጎ ጥቅም ላይ እንዲውል ለገንዘብ ሚኒስቴር ማሳወቅ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

<u>የሥራ አመራ ምላሽ፤</u>

- በ2013 በጀት አመት ለሚ/ር መ/ቤታችን የተፈቀደው በጀት እጥረት ያጋጠመን መሆኑን በመግለፅ ለገንዘብ ሚ/ር በ19/9/2013 ዓ.ም. ለዋናው መ/ቤት እና ለሚሲዮን የደመወዝ እና ሥራ ማስኬጃ ጥያቄ አቅርበናል፡፡በዚህም መሰረት የገንዘብ ሚኒስቴር ጥያቄያችንን መሰረት በማድረግ ዘግይቶ የበጀት ዓመቱ ሊጠናቀቅ 7 ቀናት ሲቀረው በ23/10/2013 ዓ.ም.የፈቀደበት ቅፅ በማ/1.3 ያሳወቅን ሲሆን ከዚም በኃላ ይህንን በጀት ሥራ ላይ ለማዋል የጥሬ ገንዘብ ፍሰት ከገንዘብ ሚኒስቴር ተጠይቶ ገንዘቡ/በጀቱ ከተለቀቀ በኃለ ለሚሲዮኖቻችን ለመላክ ብሔራዊና የኢትዮጲያ ንግድ ባንክ ማስፈቀድና ወረፋ መጠበቅ ግዴታ መሆኑ ይታወቃል፡፡ስለዚህ በዚህ ሁኔታ ይህንን በጀት ስራ ላይ ለማዋል በፍጹም ስለማይቻል ያለው አመራጭ የመንግስት ሀብት ወደ ፈቀደው ገንዘብ ሚኒስቴር መመለስ ብቸኛው አማራጭ ሆኗል፡፡ በመሆኑም የበጀት አጠቃቀም ከ 10 በመቶ በላይ (ዝቅተኛ) አፈፃፀም ታይቷል፡፡በዚህ መሰረት የአጠቃቀም ክፍተቱ የተጠየቀው በጀት በወቅቱ ባለመፈቀዱ ምክንያት እና ከመ/ቤታችን ቁጥጥር ዉጪ በሆነ ሁኔታ መሆኑን እየገለፅን የበጀት አጠቃቀም ላይ የታየውን ጉዳይ በግኝቱ ታሳቢ እንዲደረግ ይህን ምላሽ የሰጠን መሆኑን እንገልፃለን፡፡
- ስራ ላይ ያልዋለ መደበኛ በጀት በድምሩ ብር **128,488,326.70** በበጀት ዓመቱ ከተለያዩ የሂሳብ መደብ ከ10% በላይ ስራ ላይ ሳይውል ስለመቅረቱ በኦዲት መረጋገጡ ተገልጿል፡፡በዚሁ መሰረት በኦዲቱ ወቅቱ ምላሽ የተሰጠው ለሚ/ር መ/ቤታችን የተፈቀደው በጀት እጥረት ያጋጠመን መሆኑን ገልፀን ለገንዘብና አኮኖሚ ሚኒስቴር ባቀረብነው የተጨማሪ በጀት ጥያቄ መሰረት ተጨማሪ በጀቱ የበጀት ዓመቱ ማብቂያ ላይ የተፈቀደ በመሆኑ በስራ ላይ ማዋል አለመቻላችንን መግለጻችን ይታወሳል፡፡በመሆኑም በቀጣይ ስራ ላይ ሳይውሉ የሚቀሩ የሂሳብ መደቦች የበጀት አጠቃቀም ላይ ክትትል በማድረግ እና መስሪያ ቤታችን የማይጠቀምበትን በጀት ለይቶ በማወጣት ለገንዘብ ሚኒስቴር የምናሳውቅ መሆኑን እንዲሁም በጥናት ላይ የተመሰረተ የበጀት ዕቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት የምናደረግ መሆኑን በማለት ገልጸዋል፡፡

5.2 <u>ግኝት፤ ከተፈቀደ በጀት በላይ ወጪ የሆነ ብር 9,218,249.07፤</u>

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል 3/12 መሰረት የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ሊፈጸም ወይም ወጪ ሊደረግ የሚችለዉ የተፈቀደ በጀት ሲኖር ነዉ ይላል፤ ይሁን እንጂ በሂሳብ መደብ 2311203 በበጀት አመቱ የተፈቀደው በጀት **ብር 136,711,682.35** ሲሆን፤

በሂሳብ መደቡ ብር 145,929,931.42 ወጪ የተደረገ በመሆኑ ከተመደበው በጀት በላይ **ብር 9,218,249.07** ባልተፈቀደ በጀት ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስጋት፤

የበጀት ዝውውር ሳይደረግ ወይም ተጨማሪ በጀት ሳይፈቀድ፤ ከተፈቀደዉ በጀት በላይ መጠቀም መመሪያን ከመጣሱም በላይ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ፤

በእርዳታም ሆነ በብድር የሚገኝ ገንዘብ የተጠቃለለ ፈንድ አካል መሆኑ ታውቆ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፋይናንስ አስተዳደር ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈቀደለትን በጀት በተገቢው መንገድ በሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

ከፕላንና በጀት ዳይሬክቶሬት የተሰጠ ምላሽ፣ በ2013 በጀት ዓመት ከበጀት ኮድ 2311203(6323)ስር ለሚገኙ አራት ሚሲዮኖች ለበጀት አመቱ የተስተካከለ በጀት ብር 136,711,682.35 ከኢፍሚስ የተረጋገጠ ሲሆን በበጀት አመቱ በድምሩ ብር 132,747,554.87 (97.5%) ስራ ላይ የዋለ መሆኑን እየገለፅን በፌዴራል ኦዲት ቡድን በኩል ብር 145,929,931.42 ስራ ላይ ዉሏል በሚል የቀረበው የበጀት አጠቃቀም በኢፍሚስ ሲስተም መረጃው የሌለ በመሆኑ በእናንተ በኩል የዚህ አጠቃቀም መረጃ በድጋሚ ተጣርቶ ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ ስንል ይህንን ምላሽ የላክን መሆኑን **እንገልፃለን**፡፡

ከሚሲዮን ፋይናንስ የተሰጠ ምላሽ፣ ከበጀት በላይ የተመዘገበ በሚል የቀረበውን ግኝት በተመለከተ በ2009 ዓ.ም. በቱርክና በኢትዮጲያ መካከል በተደረገው የሚሲዮኑ ጽ/ቤት እና አምባሳደር መኖሪያ ቤት ቦታ ልውውጥ በነጋሪት ጋዜጣ የታወጀና በዛው አከባቢ በልውውጡ ወቅት 3.2 ሚሊዮን ዶላር ለኢትዮጲያ መንግስት ቦታው ላይ ጭማሪ የተሰጠ ሲሆን በተገኘው ገንዘብ ከ2010 ዓ.ም. ጀምሮ ገንዘብ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በህጉ መሰረት የአፈፃፀም ሪፖርት እንዲደረግና ገንዘቡ የገቢ አካል ስላልሆነ ገቢ ደረሰኝ ላይ ተመዝግቦ ሪፖርት ለማድረግና የበጀት አካል ማድረግ የማይጠበቅ መሆኑን ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመወያየትና የእርዳታ ገንዘብን አስመልክቶ ባለው አዋጅ መሰረት ሲፈፀም የቆየና ሪፖርቱ በIFMIS ተጠቃሎ ሲላክ በኔጋቲቭ ቢታይም በገንዘብ ሚኒስቴርም ተቀባይነት ያለው መሆኑን እንዲሁም ፕሮጀክቱ ተጀምሮ እስከሚያልቅበት ጊዜ ድረስ የነበረው አሰራር ከዚህ ጋር ተያይዞ ያለውን ደጋፊ መስረጃዎች አያይዘን እየላክን መሆኑን የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

<u>የኦዲተር አስተያየት፤</u>

በሥራ አመራሩ ምላሽ ደጋፊ ማስረጃዎች ተያይዘው መቅረቡ ቢገለጽም ከማስረጃዎቹ ለመረዳት እንደተቻለው፤ በእርዳታም ሆነ በብድር የሚገኝ ገንዘብ የተጠቃለለ ፈንድ አካል መሆኑ ታውቆ የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ተግባራዊ ተደርጎ ሪፖርት መደረግ እንዳለበት የሚገልፅ በመሆኑ ከገ/ሚ/ር ጋር ውይይት በማድረግ የበጀት ዓመቱን የወጪ ሂሳብ ከፍ እንዲል ያደረገው የድጋፍ ወይም የእርዳታ ገንዘብ በመ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት በገቢ ባለመያዙ ምክንያት መሆኑኑ በኦዲት መውጫ ውይይት ወቅት ማብራሪያ የተሰጠበት በመሆኑ ክትትል በማድረግ ትክክለኛ የሂሳብ ሪፖርት እንዲቀርብ መደረግ ይኖርበታል፡፡

6. <u>ንብረት፤</u>

6.1 <u>ግኝት፤የንብረት አያያዝና አስተዳደርን በተመለከተ</u>፤

የመ/ቤቱ የንብረት አያያዝና አስተዳደር በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 እና በፌዴራል መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፤-

<u>የአላቂና የቋሚ እቃ ስቶር</u>፤

- በአላቂና ቋሚ እቃ ንብረት ክፍል ውስጥ እንዲሰሩ የተመደቡ ሰራተኞች ገቢንም ወጪንም ደርበው/ቀላቅለው የሚሰሩ መሆኑ፤
- ለናሙና ቀርበው የነበሩ 2 የሴትና 2 የወንድ ሙሉ ልብሶች፤ 2 የወንድና 2 የሴት ሸሚዞች፤ 1 ጫማ እና 1 የሴት ኮት ያለምንም ርክክብና የገቢ ደረሰኝ በስቶሩ የሚገኙ መሆኑ፤
- የመፈተሻ እቃዎች ገቢ ሳይደረጉ/በአደራ ሲቀመጡ የተዘጋጀ ፎርም ሳይኖር በስቶር የሚገኙ መሆኑ፤
- ስቶር ውስጥ የእሳት ማጥፍያ ቢኖርም የአገልግሎት ዘመኑ ያለፈበት መሆኑ፤ በተመሳሳይ አገልግሎቱ ያለፈባቸው 5 አዳዲስ የእሳት ማጥፍያዎች ለአመታት ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፤
- የተበላሹ ብዛት ያላቸው ደረሰኞች /የቫት ደረሰኞች፤ የተለያዩ መሂዎች እና ሞዴሎች በስቶር የሚገኙ መሆኑ፤ (በ2013 የቆጠራ ሪፖርትም የታየ)

- አልፎ አልፎ ቢን ካርድ ያልተዘጋጀላቸው ንብረቶች የሚገኙ መሆኑ፣ እንዲሁም አንዳንድ ቢን ካርዶች ላይ መቼ ገቢ እንደተደረጉ የማይገልጽ መሆኑ፣ ለአብነት መልቲ ፋንክሽን ስልኮች፣
- ከስቶር ውጭ ጠረጴዛ፣ መካከለኛ ሽልፍ፣ ወንበርና ሌሎች ንብረቶች የሚገኙ መሆኑ በኦዲቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

<u>**በተመላሽ ስቶር፣**</u>

- ያለ ህጋዊ ርክክብ/ጊዚያዊ ንብረት ማስቀመጫ/ ቁጥራቸው የማይታወቅ የሚገጣጠሙ ጠረጴዛዎች፣ 2 መኪና ጎማዎች፣ ብዛቱ የማይታወቅ የተለያዩ አገራት ባንዴራዎችና የባንዴራ መስቀያዎች/ማስቀመጫዎች፣ ብዛታቸው የማይታወቅ ጥላዎች፣ የመኪና የወንበር ልብሶች፣ አዳዲስ ያልተሰራበው ደረሰኞች፣ የተለያዩ የዱንካን ብረቶች፣ 19 ፍራሾች፣ 1 አልጋ፣ እና ሌሎች እቃዎች ገቢ ሳይደረጉ ማለትም ከሚጠቀምበት አካል ርክክብ ሳይደረግ በተመላሽ ስቶር በር ላይ የሚገኙ መሆኑ፣
- የሚሰሩና የማይሰሩ በሚል ያልተለዩ 9 የተለየዩ አይነት ተመላሽ ላፕቶፖች፣ ከ7 በላይ ፕሪንተሮች፣ 1 ፋክስ፣ 25 ዩፒኤስ፣ ከ8 በላይ የፎቶ ኮፒ ማሽኖች፣ 55 ኢንች ቲቪ፣ ብዛት ያላቸው የስልክ ቀፎዎች፣ የውሃ ማጣሪያና፣ የተለያዩ የመኪና ባትሪዎች የሚገኝ መሆኑ፣
- የሚሰራ፣ የማይሰራ እና አዳዲስ እቃዎች/ንብረቶች ባልተገባ ሁኔታ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፣
- የእሳት አደጋን ለመከላከል እንዲቻል የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ መዘጋጀት ሲገባው በተመላሽ ዕቃዎች ማስቀመጫ መጋዘን ውስጥ የሌለ መሆኑ፣
- ቁጥራቸው የማይታወቅ በርካታ አዳዲስ የእንግዳ መቀመጫ ወንበሮች፣ ብዛት ያላቸው የተላየዩ አይነት የመኪና ጎማዎች፣ የሚገጣጠሙ የአጥር ብርቶች፣ ብዛት ያላቸው የእንጨት ሽልፎች፣ በርና የመስኮት ብረቶች፣ የተበላሸ አንድ የፍተሻ ማሽን፣ ከ10 በላይ የእሳት ማጥፍያዎች፣ ብዛት ያላቸው መደበኛ የስልክ ቀፎች፣ ብዛት ያለቸው የወለል/የመሬት ላይ ምንጣፎች፣ ከ10 በላይ የቢራ ጠርሙሶች/ ካሳዎች ባልተገባ እና ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፣

<u>**ሌሎች፣**</u>

- በመረጃ ሀብት ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን የስራ ክፍል ብዛቱ የማይታወቅ ፋይል ካቢኔት/ሼልፍብዛት 3፣ ትንሹ ፓንቸር ብዛት 2፣ ፓንቸር ትልቁ 02፣ እስቴፕለር መምቻ

ብዛት 04 ፤ ፔፐር ትሪ ብዛት 02፤ ደስት ቢን ብዛት 05፤ አስቸኳይ ማህተብ ብዛት 03፤ አማርኛ እንግሊዘኛ፤ የአቅጣጫ ማህተብ ብዛት 02 ፤ማህተብ መርገጫ ብዛት 01፤ አውቶማቲክ የግርጌ ማህተብ ብዛት 01 ፤አውቶማቲክ ቶፐ ማህተብ ብዛት 03፤ ገቢ ማህተብ ብዛት 01 ፤ማህተብ መደርደሪያ ብዛት 01 ፤መቀስ መካከለኛ ብዛት 01፤አግራፍ ትሪ ብዛት 01 ፤ ዲቫይደር ብዛት 02 ፤ሪሙቨር ብዛት 01 ፤ማስመሪያ ብዛት 01 ፤ሂተር /ማሞቂያ ብዛት 01፤ ፔን ትሪ ብዛት 02 ፤ የላይብረሪ ቲተር ብዛት 01፤ እንዲሁም ግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ሞባይል አፓራተስ ብዛቱ የማይታወቅ ፤ጠረጴዛ ብዛቱ የማይታወቅ፤ ታብሌት ሳምሰንግ ኮምፒውተር ብዛቱ የማይታወቅ ፤ፕሪንተር ኬብል/ ገመድ ሜትሩ የማይታወቅ ፤ በኤክስፖርት ቼር /ወንበር ብዛቱ የማታወቅ ፤ ኤክስፖርት ቴብል ፤ ኤሌትሪካል ቱል ኪት(የሻይ ማፍያ)ብዛቱ የማይታወቅ ፤... የተቋሙ ንብረቶች ያልሆኑ ንብረቶች የሚገኙ መሆኑ በ2013 የንብረት ቆጠራ ሪፖርት ላይ ለማረጋገጥ ተችላሏል፡፤

ስጋት፤

- በአላቂና ቋሚ እቃ ንብረት ክፍል ውስጥ እንዲሰሩ የሚመደቡ ሰራተኞች ገቢንም ወጪንም ደርበው/ቀላቅለው የሚሰሩ ከሆነ ተጠያቂነትን ማስፈን ካለመቻሉ በተጨማሪ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል።
- ገቢ ያልተደረጉ ንብረቶች ለግለሰብ ጥቅም ሊውሉ ይችላሉ፤ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል።
- ያለአገልግሎት የተቀመጡ ዕቃዎች በጥቅም ላይ ካልዋሉ ለብልሽት ሊዳረጉ ይችላል፤
- የማይሰሩ ንብረቶች ተለይተው ካልተወገዱ ለተጨማሪ ብልሽት ሊዳረጉ ይችላሉ። እንዲሁም ያለአግባብ ቦታ ይዘው ሊቀመጡ ይችላሉ።
- ተመላሽ ንብረቶች ያሉበት ሁኔታ ካልተለየ ያለአግባብ የሚሰራ ንብረት ሊወገድ ይችላለ፤

የማሻሻያ ሀሳብ፤

- በአላቂና ቋሚ እቃ ንብረት ክፍል ውስጥ እንዲሰሩ የሚመደቡ ሰራተኞች ገቢንም ወጪንም ደርበው/ቀላቅለው ከመስራት ይልቅ ተከፋፍለውና ሃለፊነት ወስደው ሊሰሩ ይገባል።
- ለናሙና ቀርበው የነበሩ አልባሳቶች ድርጅቱ መውሰድ ካልቻለ በመመሪያው መሰረት የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሊቆረጥለት ይገባል።
- ስቶር ያሉና ለረዥም አመት ወጪ ያልተደረጉ ንብቶች ለበላይ አመራሩ በማሳወቅ መፍትሄ ሊሰጣቸው ይገባል።

- የማይሰሩ ንበረቶች በሚገባ ተለይተው ተመዝግበው ሊያዙ ይገባል፡፡ በተጨማሪም መወገድ ካለባቸው በመመሪያው በተቀመጠው የማስወገጃ መንገዶች ሊወገዱ ይገባል፡፡
- የእሳት አደጋ መከላከያ በስቶር ክፍሎቹ ሊኖር ይገባል፡፡ አጠቃቀሙንም በሚገባ ማስተማር ያስፈልጋል፡፡
- ተመላሽ የሚደረጉ ንብረቶች ተመላሽ ከመደረጉ በፊት በሚመለከተው ባለሙያ ንብረቶቹ ያሉበትን ሁኔታ ማለትም የሚሰሩ፤ የማይሰሩ እና በቀላል ወጪ የሚጠገኑ፤ በሚል እንዲለዩ በማድረግ መሆን ይኖርበታል፡፡
- በአደራ ያለምንም ማስረጃ የተቀመጠው ንብረት ለምን በአደራ ሊቀመጥ እንደቻለ በማጣራት ስራ ላይ የሚውል ከሆነ ወደ ስራ እንዲገባ ካልሆንም በአደራ መቀመጥ ካለበት የአደራ መረካካቢያ ፎርም/ቅጽ/ ተዘጋጅቶ ሊቀመጥ ይገባል፤፤
- የመ/ቤቱ ያልሆኑ የተለያዩ ንብረቶች የማን እንደሆኑ በሚገባ በማጣራት ለባለንብረቱ የሚመለስበት ሁኔታ ካለ መመለስ፤ ባለቤት የሌላቸው/ ለባለንብረቱ መመለስ የማይቻል ከሆነ ደግሞ የንብረት ገቢ ደረሰኝ/ሞዴል-19/ ተቆርጦላቸው ገቢ ሊደረጉና የመ/ቤቱ ንብረቶች እንዲሆኑ ማድረግ ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

<u>የአላቂና የቋሚ እቃ ግምጃ ቤት</u>

- በቀጣይ የስቶር ክፍሎችን በመክፈል የአላቂ እና የቋሚ ዕቃዎች በመለየት በዚሁ መልክ ሰራተኞችን በመመደብ የማመቻቸት ስራ እየተሰራ ነው፡፡
- ከዚህ ቀደም ለናሙና የቀረቡ ንብረቶች ማለትም 2 የሴትና ወንድ ሙሉ ልብሶች፣ 2 ወንድና 2 የሴት ሸሚዞች፣ 1 ጫማ እና 1 የሴት ኮት ተጫራጮቹ ለድርጅቱ ተመላሽ ተደርጓል፡፡
- መፈተሻ እቃዎች ለስፔር ፓርትነት ለመጠባበቂያ የተቀመጡ ሲሆን ለሚጠቀሙበት የስራ ክፍል ወጪ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡
- የዕሳት ማጥፊያ መሳሪያው ወጪ ሳይደረግ በስቶር ውስጥ በመቆየቱ የተነሳ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈ ቢሆንም አሁን ወጪ የተደርገ ሲሆን በቀጣይ የእሳት ማጥፊያ ኬሚካል ለማስሞላት ጥያቄ የቀረበ ሲሆን ኬሚካሉ ተሞልቶ ሲቀርብ ወጪ በማድረግ በየህንጻው ላይ እንዲገጠሙ ይደረጋል፡፡

- ከመንግስት ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ጋር በመመካከር መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ወደ ገንዘብ ሚኒስቴር ተመላሽ ለማድረግ ቆጠራና ሰነዶቹን የመለየት ስራ ተጀምሯል፡፡
- በወቅቱ ዕቃዎቹ በዕለቱ የገቡ በመሆናቸው በቢን ካርድ ለመመዝገብ ዝግጅት ላይ የነበረ ሲሆን አሁን ሁሉም ዕቃዎች በቢን ካርድ ላይ ተሞልቷል፡፡
- በወቅቱ በስቶር ጥበት ውጭ ተቀምጠው የነበሩ ሲሆን አሁን ሁሉም ተወግደዋል፡፡

6.2 በተመላሽ ግምጃ ቤት

- ያለ ህጋዊ ርክክብ (ጊዜያዊ ንብረት ማስቀመጫ) ቁጥራቸው የማይታወቅ የሚገጣጠሙ 7 ጠረጴዛዎች አሁን ተገጥመው ለተጠቃሚዎች ተሰራጭተዋል፡፡
- 2 የመኪና ጎማዎች በአደራ የተቀመጡ የነበረ ሲሆን አሁን የስራ ክፍል እንዲወስድ ተደርጓል፡፡
- ከዚህ በፊት አገልግሎት ሰጥተው በእርጅና ምክንያት ወደ ስቶር የተመለሱ ሲሆን በቀጣይ መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት ቁጥራቸው እንዲታወቅ ተደርጎ እንዲወገዱ ይደረጋል፡፡
- ስድስት ጥላዎች የነበሩ ሲሆን ቁጥራቸው የሚታወቅ መሆኑ
- 17 የመኪና ፀሐይ መከላከያ ልብሶች እና 244 የባንዲራ መስቀያ ያሉ ሲሆን የሚመጥናቸው መኪኖች የሌሉ በመሆኑ በቀጣይ እንዲወገዱ ይደረጋል፡፡
- የተለያዩ የድንኳን ብረቶች፣ ፍራሾች፣ 1 አልጋ የድንበርና ድንበር ተሻጋሪ ዳ/ጄኔራል ለፊልድ ስራ ሲወጡ ብቻ የሚጠቀሙበት ስለሆነ በአደራ የተቀመጠ መሆኑ በቀጣይ የአደራ ዕቃ መመዝገቢያ የምዘጋጀው ይሆናል፡፡

የሚሰሩና የማይሩ በሚል ያልተለዩ 9 የተለያዩ አይነት ተመላሽ ላፕቶፖች፣ከ7 በላይ ፕሪንተሮች፣1 ፋክስ፣25 የፒኤስ፣ከ8 በላይ የፎቶ ኮፒ ማሽኖች፣ 55 ኢንች ቲቪ፣ብዛት ያላቸው የስልክ ቀፎዎች፣ የውሃ ማጣሪያና፣ የተለያዩ የመኪና ባትሪዎች የሚገኝ መሆኑ፣

ቁጥራቸው የተጠቀሱት ላፕቶፕ፣ፕሪንተሮች፣ፋክስ፣ዮፒኤስ፣ፎቶኮፒ 55 ኢንች ቲቪ፣ የስልክ ቀፎዎች፣ የውሃ ማጣሪያዎች ተመዝግበው በወቅቱ በማስወገድ ሂደት ላይ የነበሩ ሲሆን አሁን ንብረቶቹ እየተወገዱ ይገኛሉ፡፡

6.2 ግኝት፤ ተሽከርካሪን በተመለከተ፤

የፌደራል መንግሥት ንብረት አስተዳደር መመርያ 9/2003 አንቀጽ 16 ቁጥር 2 በመለዋወጫነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ወይም እንዲሸጡ ከተወሰነባቸው ተሽከርካሪዎችና መሳርያዎች ላይ ጠቃሚ አካሎች ፈቶ አግበብ ባለው የዕቃ አስተደደር መሰረት ገቢ እንዲሆንና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ወይም በጨረታ እንዲሸጡ ማድረግ እንደሚችሉ ይገልጻል፡፡ በመሆኑም መ/ቤቱ መኪና ሲያስጠግንና እቃዎች ሲያስቀይር የተቀየረው አሮጌ የመለዋወጫ እቃ ወደ ንብረት ክፍል ተመላሽ የሚደረግ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተለያዩ ቀናትና በተለያዩ የኢንቮይስ ቁጥሮች ተሽከርካሪዎችን ከበላይ አብ ሞተርስ ተጠግነው የተቀየሩት አሮጌ የመለዋወጫ እቃዎች ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ተደረገው የተመላሽ እቃ ገቢ ደረሰኝ/ሞዴል ከወጪ ሰነዱ ጋር መያያዝ ሲገባው ገቢ ያልተደረገ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡
- መ/ቤቱ ዘመናዊ ፓርኪግ /የመኪና ማቆሚያ/ ያዘጋጀ ቢሆንም አገልግሎት ሳይሰጥ ከአንድ አመት በላይ የተቀመጠ መሆኑ፤
- አንድ ላንድ ክሩዘር ተሽከርካሪ በኮድ 2-63258 ታርጋ የሚገኝ/የሚሰራ መሆኑ፤
- አንድ አሽከርካሪ ከአንድ በላይ ተሽከርካሪ ወጪ የሚያደርግ መሆኑ፤ ለምሳሌ አቶ ተፈራ በቀለ 21 ተሽከርካሪዎች፤ አቶ ተስፋየ ግርማይ 7፤ አቶ ታደሰ አክሊሉ 9 ፤ አቶ ደጀኔ ጌታቸው 6፤ አቶ አብዱላዚዝ ሙሃመድ 3፤ እንዲሁም አቶ መልካሙ ከበደ 5 ተሽከርካሪዎች ወጪ ያደረጉ መሆኑን በኦዲት ወቅት ከተሰጠን የተሽከርከሪ ዝርዝር መግለጫ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- ለኮድ 4-24536 በተከፈተ የግል ማህደር ውስጥ የተሽከርካሪው ሊብሬ ያልተያያዘ መሆኑ፤
- የተበላሹና የሚወገዱ ተሽከርካሪዎች አንድ የሞተር ሳይክልን ጨምሮ በተለያየ ቦታ ለተጨማሪ ብልሽት በሚያጋልጥ ሁኔታ ተበታትነው የሚገኙ መሆኑ፤ (ዝርዝሩ በአበሪ 20 ተመለከቷል)
- እስካንያ ቪአይፒ ባስ ኮድ 4-20315 በጥገና ምክንያት ከ21/4/2012 ጀምሮ (ከሁለት አመት በላይ) የቆመ መሆኑ፤
- ቶይታ ያሪስ 4-15866 በጋራጅ ለጥገና ከ25/10/2013 ዓ.ም ጀምሮ የቆመ መሆኑ፤
- ሃይወንዳይ ሳንታፌ ኮድ 4-13453 እና 4-13454 በጋራዥ ለጥገና ከ16/9/2013 ዓ.ም እና ከ21/11/2013 ዓ.ም ጀምሮ የቆመ መሆኑ፤
- ሃይወንዳይ ባስ ኮድ 4-13393 በጋራጅ ከ14/8/2013 ዓ.ም ጀምሮ የተቀመጠ መሆኑ፤
- እስካንያ አውቶብስ ኮድ 4-17956 እና 4-16397 የኪሎ ሜትር ንባቡ የማይሰራ መሆኑ፤

➢ ብዛት ያላቸው የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች የሰርቪስ ጊዜያቸው ያለፈባቸው፤ ጥገና የሚፈልጉና የሰርቪስ ጊዜያቸው የደረሰ ስለመሆናቸው በተሰጠን የተሽከርካሪ ዝርዝር መግለጫ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ስጋት፤

- የሚወገዱም ሆነ የተበላሹ ተሽከርካሪዎች በአግባቡ የማይቀመጡ/የማይያዙ ከሆነ ለተጨማሪ ብልሽት እንዲሁም ለስርቆት ሊዳረጉ ይገባል፡፡
- አንድ አሽከርካሪ ከአንድ በላይ ተሽከርካሪ ወጪ የሚያደርግ ከሆነ ተጠያቂነትን ለማስፈን አስቸጋሪ ሊያደርገው ይችላል፡፡ አሰራሩም የመንግስትን መመሪያ ያልተከተለ በመሆኑ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡
- በጥገና ምክንያት በተለያዩ ጋራጅ የቆሙ ተሽከርካሪዎች ጥገናው ተጠናቀው ወደ ስራ የማይገቡ ከሆነ የመ/ቤቱን ስራ በሚገባ ለመፈጸም እንቅፋት ከመሆኑ በተጨማሪ ለተጨማሪ ወጪ ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፤

- ያለ ስራ የተቀመጠውን የመኪና ፓርኪንግ ስራ እንዲጀምር ማድረግ ይገባል፡፡
- የሚወገዱም ሆነ የተበላሹ ተሽከርካሪዎች በአግባቡ ሊቀመጡና ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ የሚወገዱ ተሽከርካሪዎች ከመወገዳቸው በፊት በሚመለከታቸው አካላት በሚገባ ሊፈተሹና ሊመረመሩ ይገባል፡፡
- በኮድ 2- የሚገኝ/የሚሰራን ተሽከርካሪ ወደ ኮድ 4 ሊቀየር ይገባል፡፡
- አንድ አሽከርካሪ ከአንድ በላይ ተሽከርካሪ ወጪ የሚያደርግ ከሆነ ተጠያቂነትን ለማስፈን አስቸጋሪ ሊያደርገው ስለሚችል በተጨማሪም በአሽከርካሪው ላይ የከፋ ችግር ሊያስከትል ስለሚችል በፍጥንት ሊስተካከል ይገባል፡፡
- በጥገና ምክንያት በተለያዩ ጋራጆች የቆሙ ተሽከርካሪዎች ጥገናቸው ተጠናቆ ወደ ስራ የሚገቡበት ሁኔታ ሊፈጠር ይገባል፡፡
- የኪሎ ሜትር ንባባቸው የማይሰሩ ተሽከርካሪዎች በወቅቱ ማሰራት ይገባል፡፡
- የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች ወቅቱን ጠብቀው ሰርቪስ የማይደረጉና ሲበላሹም በወቅቱ የማይጠገኑ ከሆነ ለተጨማሪ ብልሽት ሊዳረጉ ስለሚችሉ አስቸኳይ ጥገናና ሰርቪስ እንዲያገኙ ማድረግ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

- የመ/ቤታችን ተሽከርካሪዎች የሚጠግኑት የመንግስት ግዥ ኤጀንሲ ዓመታዊ የጥገና ፍቃድ ከተሰጣቸው ድርጅቶች (አስመጪ ኩባንያዎች)ለ 1 አመት የሚፀና የጥገና ውል በመዋዋል ሲሆን ፣ ጥገናውን የሚያካሂደው ድርጅት የመ/ቤቱን ተሽከርካሪዎች ከጥገና በኃላ ተሽከርካሪውን ለተቋማችን ሲያስረክብ የተቀየሩ የመለዋወጫ እቃዎች ከነዝርዝራቸው ፣ የክፍያ ማቅረቢያ ፕሪፎርማ ጋር በማመሳከር በአስረካቢው ባለሙያ ተረጋግጦ ከተረከብን በኃላ በር ላይ የዕቃ ማውጫ ቅፅ ለበር በማሳየት ይዘን እንወጣለን፡፡
- በተቋማችን በኩል ተሽከርካሪውን የሚረከበው አሽከርካሪ፣የስምሪትና የጥገና ባለሞያ ሲረከቡ የእቃዎችን ዝርዝር ከፕሪፎርማው ዋጋ ጋር በማመሳከርና የተገጠሙትን አዲስ እቃዎች መታየት የሚችሉትን በተሽከርካሪው ላይ መገጠማቸውን ታይቶ እና ተረጋግጦ የምንረከብ ሲሆን፣ከተረከብን በኃላ አባሪ 8 ቅፅ በ3 ኮፒ ተሞልቶ በአሽከርካሪው ፣በጠቅላላ አገልግሎት ዳ/ቱና በመ/ቤቱ ግምጃ ቤት ተፈርሞ ወደ ግምጃ ቤት ገቢ ይደረጋል፡፡ከዚህ አንዱ ቅጂ ግምጃ ቤት፣ ሁለተኛው ስምሪትና ጥገና ክፍል ሦስተኛው ደግሞ ከአስረካቢው ሾፌር ጋር የሚቀመጥ ሲሆን ፣ የተፈጠረው ክፍተት የሚቀይሩ አሮጌ እቃዎች ተመላሽ የማይደረጉ መሆናቸው ሳይሆን ሂደቱ ከላይ በተገለፀው መልኩ ስለነበረ ነው፡፡በመሆኑም በኦዲት ማጠቃለያው ላይ የማሻሻያ እርምጃ እንድንወስድ በተሰጠን አቅጣጫ መሰረት በቀጣይ የተመላሽ -ሞዴል 19 በማዘጋጀት ከክፍያ ሰነድ ጋር አያይዘን የምናቀርብ መሆኑን እያሳወቅን ፣ተመላሽ አልተደረጉም በሚል የተዘረዘሩ መለዋወጫዎች ግምጃ ቤት ገቢ ያደረግንባቸው ማስረጃዎች አባሪ አድርገን ማያያዛችንን እንገልጻለን፡፡
- ኮድ 2-63258 ታርጋ የሚጠቀሙ ተሽከርካሪ ቀደም ሲል ከግለሰብ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በስጦታ ተሰጥቶ ሊብሬው ሲወጣ ወደ ውጭ ጉዳይ ሲደረግ በቀጥታ በነበረው ታርጋ ሳይቀየር የወጣለት ሲሆን ሊብሬው እድሳት ሲያልቅ እንዲለወጥ የሚደረግ ይሆናል፡፡ በዚሁ ዓመት መጨረሻም የሚያበቃ ስለሆነ ከነታርጋው ይቀየራል፡፡
- ለኮድ 4-24536 በተከፈተ የግል ማህደር ውስጥ የተሽከርካሪ ሊብሬ ኮፒ አልተያያዘም ለተባለው ኮፒ ተደርጎ የተያያዘ መሆኑ ቢታወቅ፡፡
- የሚወገዱ ተሽከርካሪዎች መበታተናቸው ለተባለው ተሽከርካሪዎችን በተቻለ መጠን ወደ አንድ ቦታ ለማሰባሰብ ጥረት ተደርጓል፡፡ሆኖም ተሽከርካሪዎች መነሳት የማይችሉትን ባሉበት እንዲሆኑ ሆነዋል፡፡
- ኮድ 4-20315 እስካንያ ባስ በጥገና ምክንያት ለረጅም ጊዜ መቆሙ የተባለው ተሽከርካሪውን ባለበት ቦታ ሆኖ ለመጠገን የተለያዩ ባለሞያዎች መጥተው የተመለከቱት

ሲሆን መጠገን ባለመቻላቸው እንደሆነና በቅርቡ ብቸኛ ጠጋኝ ባለሞያ ተመልክቶት መጠገን እንደሚችል አሳውቆን ውሳኔ እንዲሰጥበት ያቀረብን መሆኑ እንዲታወቅ፡፡

- ቶዮታ ያሪስ ኮድ 4-15866 በጥገና ምክንያት የቆመ የተባለው በወቅቱ ለጥገና ሞኤንኮ ካምፓኒ ገብቶ መለዋወጫ በመጠበቅ ቆሞ የነበረ ሆኖ አሁን ግን አስፈላጊውን መለዋወጫ አግኝቶ ወደ ሥራ የገባ መሆኑ ቢታወቅ፡፡
- ሀይወንዳይ ሳንታፌ ኮድ 4-13453 በወቅቱ ከቆመበት ጊዜ መለዋወጫ በመጠበቅ የነበረ ሆኖ የሚፈለገውን መለዋወጫ አግኝቶ ተጠግኖ ወደ ስራ የገባ መሆኑ ቢታወቅ፡፡
- ኮድ 4-13454 አሁንም ጥገናውን በሚሰጠው ክምፓኒ ማለት ማራቶን ሞተርስ የሚገኝ ሲሆን ከካምፓኒው ጋር የገባነው የጥገና ውል ባለመታደሱ ጥገናውን ለማድረግ የሚፈልገውን መለዋወጫ ግምት ዋጋ ለማሳወቅ ድርጅቱ ውሉ እስከሚታደስ እየጠበቅን እንገኛለን፡፡
- ኮድ 4-13393 ሀይወንዳይ ባስ ለጥገና በማራቶን ሞተርስ ካምፓኒ ጥገናው ተደርጎለት ያለቀ ሆኖ ክፍያ በመጠበቅ ላይ ሲሆን ውል እንደታደስ የምንረከብ ይሆናል፡፡
- እስካንያ ባስ ኮድ 4-17956 እና ኮድ 4-16397 ተሽከርክሪዎች የኪሎ ሜትር ንባባቸው እንደማይሰራ የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ ቀደም ሲል ተሽከርካሪዎችን ከሚጠግነው ክምፓኒ ትራንስ ኢትዮጵያ አሳውቀን መለዋወጫ እንደሚፈልግ አሳውቆን ከሀገር ውስጥ የማይገኝና በነሱ በኩል እንደሚያስመጡ ተነግሮን በመጠበቅ ላይ ስንሆን ተሽከርካሪዎቹን በኪሎ ሜትር ምክንያት ማቆም ለበለጠ ጉዳት እንደሚዳርግ አሳውቀውን ቀደም ሲል በሚጠቀሙበት ኪሎ ሜትር ግምት በማስላት በሳምንት አንድ ቀን ነዳጅ እየተሞላላቸው የሠራተኛ ሰርቪስ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡
- ዓመታዊ የተሽከርካሪ የጥገና ውል ባለመታደሱ የሰርቪስ ጊዜያቸው ያለፈባቸውና የቆሙ መሆኑ ቢታወቅ፡፡

<u>የኦዲተር አስተያየት፤</u>

የቀረበው ማስረጃ አንዱ በግኝቱ ከተገለፀው ጋር የማይዛመድና ሌላው ደግሞ የ2012 በጀት አመት በመሆኑ ማስረጃው ተቀባይነት የለውም፡፡ በተጨማሪም የንብረት ምልከታ/ኦዲት/ ባደረግንበት ወቅት የተቀየሩ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች በዕቃዎች ግምጃ ቤት በተገለጸው መጠን ተመላሽ መደረጋቸውን ያልተመለከትን በመሆኑ በምላሹ ላይ እንደተመለከተው በኦዲቱ የተሰጠውን ምክረ-ሃሳብ ተግባራዊ በማድረግ ጉዳዩን ትኩረት በመስጠት ሊሰራበት ይገባል፡፡

ዓመታዊ የተሽከርካሪ የጥገና ውል በወቅቱ እንዲታደስና የተሽከርካሪዎች ጥገና ሊከናወን ይገባል፡፡ በተጨማሪም በሥራ አመራር ምላሽ በተገለጸው መሠረት ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱ በውስጥ ኦዲቱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

7. ልዩ ልዩ፤

7.1 ግኝት፤የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት በሰው ኃይል አለመሟላቱን በተመለከተ፤

የፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀፅ ‘6’ ንዑስ አንቀፅ ‘2’ ፊደል “ለ” የበላይ ሃላፊዎች በመስሪያ ቤቱ የተቋቋመው የውስጥ ኦዲት ስርዓት ተገቢና በቂ የሰለጠነ የሰው ሀይል ያለው መሆኑን፣ የውስጥ ኦዲትን በነፃነት፣ ውጤታማ፣ ፈጣንና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ መከናወኑን ያረገግጣሉ ይላል፤ እንዲሁም የፌደራል መንግሥት ሰራተኞች አዋጅ 1064/2010 ክፍል 3 አንቀጽ 11 የሰው ሃብት እቅድ ከሚለው ስር ንዑስ አንቀጽ 1 የሰው ሃብት እቅድ አላማ ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት በስትራቴጃዊ አቅድ ላይ የጠቀመጡትን አላማዎች ለማሳካት የሰው ሃብት ፍላጎት ለመተንበይ የሚያስፈልገውን የሰው ሃብት በአይነትና በብዛት ለማሟለት፤ ለማልማት፤ በአግባቡ ለመጠቀም የሚያግዙ እርምጃዎችን ለመውሰድና ውጤቱንም በየግዜው እየገመገመ ማሻሻያ ለማድረግ ነው ይላል፡፡ በዚህም በመ/ቤቱ ያለው የውስጥ ኦዲት የሰው ሃይል በተፈቀደለት ልክ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬቱ በመዋቅሩ መሰረት ዳይሬክተሩን ጨምሮ 11 የሰው ሃይል እንደሚያሰፈልገው የተገለጸ ቢሆንም ያለው የሰው ሃይል ግን 1 ተወካይ ዳይሬክተር፤ 1 ቡድን መሪ፤1 ከፍተኛ ኦዲተር እና 2 ጀማሪ ኦዲተር በድምሩ 5(አምስት) የሰው ሃይል /ኦዲተር/ ብቻ ሲሆን ቀሪው 6 የሰው ሃይል ያልተሟላ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማረገገጥ ተችሏል፡፡

ስጋት፤

የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት በበቂና በሰለጠነ የሰው ሃይል ካልተደራጀ የተቋሙ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ጠንካራ እንዳይሆን ከማድረጉ በተጨማሪ በተቋሙ ለሚፈጠሩ ስህተቶችና ማጭበርበሮች በወቅቱና በአግባቡ ማስተካከያ እንዳይደረግ እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፤

የውስጥ ቁጥጥሩ የተጠናከረ ይሆን የጎደለው የሰው ሃይል መሟላት ይኖርበታል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

- በኢፌድሪ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በደረጃ *ሀ* ለተመደቡ ተቋማት የውስጥ ኦዲት ሰራተኞች ዳይሬክተሩን ጨምሮ 11 የሰው ሀይል የተፈቀደ ቢሆንም አሁን ያለው የሰው ሀይል ዳይሬክተሩን ጨምሮ 5 ሰራተኛ ሲሆን ክፍት የስወራ መደቦችን ለማሟላት አንድ ቡድን መሪ በደረጃ እድገት እንዲሟላ ተጠይቆ በገንዘብ ሚኒስቴር ተፈቅዶ ማስታወቂያ ወጥቶ ምዝገባ ከተከናወነ በኃላ ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ባልታወቀ ምክንያት የደረጃ አድገት ሂደቱ እንዲቋረጥ በመደረጉ መደቡ ክፍት ሆኖ እንዲቆይ ሆኗል፡፡
- በቀሪ ሰባት ክፍት የስራ መደቦች ላይ በቅጥር እንዲሟላ በውስጥ ኦዲት በኩል ገንዘብ ሚኒስቴር ተጠይቆ በውክልና ውጪ ጉዳይ ሚስትር ቅጥሩን እንዲፈጽም በተፈቀደው መሰረት ማስታወቂያ ወጥቶ በወቅቱ 3 ባለሙያዎች ብቻ ተፈላጊ ችሎታውን አሟልተው ተቀጥረው የነበረ ቢሆንም አንድ ከፍተኛ ባለሙያ ከተጠሪነት ጋር በተያያዘ ባለው ችግር ምክንያት የለቀቀ ሲሆን አንድ ጀማሪ ባለሙያ ከተጠባባቂ እንዲጠራ ተደርጓል፡፡
- ሌሎች 2 መደቦች በወቅቱ አሸናፊ የነበሩ አመልካቾች ለመቀጠር ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ክፍት ሆኖ ቆይቷል፡፡
- የስራ ክፍሉ አጋዥ፣ የመንግስት ሀብት እና ንብረት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት የስራ ክፍል ስለሆነ ትኩረት ተሰጥቶት ሊያጠናክርና ለስራ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች እንዲሟሉ፣ ምቹ የስራ አካባቢ እንዲፈጠርና በበቂ የሰው ሃይል እንዲደራጅ ሊያደርግ ይገባል፡፡

<u>የኦዲተር አስተያየት</u>

በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

7.2 <u>ግኝት</u>፤<u>ዋስትና ወይም ተያዥ ያላቀረቡ ሰራተኞችን በተመለከተ፤</u>

የፌደራል መንግሥት ሠራተኞች የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 11/2003 አንቀጽ 6 የመንግስት መ/ቤቶች ሃላፊነት ንዑስ አንቀጽ 1 ማንኛዉም የመንግሥት መስሪያ ቤት ከሚለው ስር፤ የፌደራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር እና የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ እና እነዚህን አዋጆች ለማስፈጸም በወጡ፣ ደንቦች እንዲሁም መመሪያዎች ስለመንግሥት ገንዘብና ንብረት አጠባበቅ፣አመዘጋገብና አያያዝ፣ ስለወጪ አከፋፈልና ጥቃቅን

ወጪዎች የተወሰነ ገንዘብ እንዲሁም በግዥ ላይ ሊወሰዱ ስለሚገባቸዉ ጥንቃቄዎች የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በገንዘብ ያዥነትና ሰብሳቢነት ወይም ንብረት ያዥነት ወይም በጥበቃ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ሰራተኞች ሁሉ ለተሰጣቸዉ ኃላፊነት የሚሆን ዋስትና ወይም ተያዥ እንዲሰጡ እንዲያቀርቡ ማድረግ ይኖርበታል በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሰረት ዋስትና የሚያስፈልጋቸዉ የስራ መደቦች ዋስትና ማስያዛቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በመ/ቤቱ 4 ገንዘብ ሰብሳቢዎች እና 9 የንብረት ሰራተኞች በመመሪያው መሰረት በቂ ዋስትና ማቅረብ ሲገባቸው ያላቀረቡ መሆናቸው ከተሰጠን ዝርዝር መግለጫ እና የሰራተኛውን ማህደር ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ስጋት፤

መ/ቤቱ ዋስተና በሚያስፈልጋቸዉ የሥራ መደቦች ላይ ዋስትና እንዲቀርብ የማያደርግ ከሆነ በመንግሥት ገንዘብ ወይም ንብረት ላይ ለሚደርሰዉ አደጋ፤ ጉድለት እና ጥፋት ተጠያቂ ባለመኖሩ የመንግስት ንብረት ለምዝበራና ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፤

የሰው ሃብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ለሁሉም ዋስትና ለሚያስፈልጋቸው የሥራ መደቦች በአፋጣኝ ዋስትና እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

በተገለፀው መሰረት በቦታው የተመደቡ ሰራተኞች በአጭር ጊዜ ውስጥ ዋስትና እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡

8. ክትትል ኦዲት፤

8.1 ግኝት፤ በሚ/ር መ/ቤቱ ባለፉት ዓመታት በተደረጉት ኦዲቶች በተሰጠው አስተያየት መሰረት እርምጃ መወሰዱን በተመለከተ፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምስት አንቀጽ 17/3 መሰረት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ከፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡ የወሰዱትን እርምጃ እና ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ

ማሳወቅ እንዳለባቸው ይገልፃል፡፡ በዚሁ መሰረት ሲጣራ በአሁንም ወቅት እርምጃ ያልተወሰደበት ግኝት እንዳለ ለማወቅ ተችሏል ፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ኦዲት የተደረገው በጀት ዓመት	እርምጃ ለወሰድበት የሚገባ		እርምጃ የተወሰደበት			እርምጃ ያልተወሰደበት		
	በገንዘብ መጠን	በቁጥር	በገንዘብ መጠን	በቁጥር	በመቶኛ (በ%)	በገንዘብ መጠን	በቁጥር	በመቶኛ (በ%)
2012	169,459,187.49	100	22,466,651.28		13.24	146,992,536.21		86.76
2011	12,771,991.92		94,160.30		0.74	12,677,831.62		99.26
2010	21,656,480.23		1,277,600.23		5.89	20,378,880.00		94.1
2009	57,732,344.60		0.00		0	57,732,344.60		100
2008	62,737,511.49		0.00		0	62,737,511.49		100
2007	94,478.15		0.00		0	94,478.15		100
ድምር	324,719,386.49		23,838,411.81			300,880,974.68		100

ስጋት፤

በኦዲት ግኝቶች ላይ ክትትል ላይደረግ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ፤

በኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊው እርምጃ መውሰድ እንዳለበት በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

በመጨረሻም በኦዲት ወቅት ለተደረገልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን::